## ምዕራፍ 11

## የባህል ልብስና የቁንጅና ውድድር ሥነ ጽሑፍ!

ተፈራ ኃይለ ሥላሴ፤ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 27 “ግማሽ አካል ብቻ የሚሸፍነውን የኢትዮጵያን የአለባበስ ባህል፤በእጅ ጠባብና በሱሪ እንዲተካ አድርገዋል” ሲሉ የእንግሊዝ ቆንስል ፕላውዴ ለአገራቸው መንግሥት የጻፉትን ደብዳቤ ጉዳይ ፈጻሚ (አምባሳደር) ተፈራ ኃይለ ሥላሴ ወደ አማርኛ ተርጉመው ጽፈውታል።

ከዚህ በፊት ስለ አጤ ቴዎድሮስ ብዙ መጻሕፍትን ሳነብ “ግማሽ አካል ብቻ የሚሸፍነውን የኢትዮጵያን የአለባበስ ባህል በእጅ ጠባብና በሱሪ እንዲተካ አድርገዋል” የሚለውን ፈጽሞ አንብቤ አላውቅም።

አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያውያን ከአለባበስ ጀምሮ ዛሬ በዓለም ላይ የሚያደንቀውን የተለያዩ የእስፖርት ውድድሮች ማድረጋቸው ተገልጧል። ከዚህ ላይ ሌላ አንድ አስቂኝ ተግባር ተፈጸመ። ያም አጤ ቴዎድሮስ ከመኳንንቶቻቸው ጋር ጉድብ ለመሥራት በቁፋሮ ላይ ሳሉ አንድ ወታደር ያመልጠውና ሌሎች መሳቅ ጀመሩ።

አጤ ቴዎድሮስ ግን የሚወዱት ወታደር ስላመለጠው እንዳያፍር ብለው “እርሱ ጠንክሮ በመሥራት ላይ ሳለ ያመለጠው ከአቅሙ በላይ በመሥራቱ ስለሆነ ሽልማት ይገባዋል ብለው” ሸልመውታል።

አጤ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 134 “በጎንደር ከተማ አቅራቢያ ቀሃ ወንዝ አጠገብ አጤ ሰቀላ ከተባለው ኮረብታ ላይ አጤ ቴዎድሮስ የቁንጅና ውድድር እንዲደረግ አዘዙ። የምርጫው ወይም የቁንጅና ውድድሩ ሊቃነ መናብርት ኢትዮጵያዊው ፈታውራሪ ገብርዬና እንግሊዛዊው ጆን (ዮሐንስ) ቤል ነበሩ። ራሳቸው አጤ ቴዎድሮስ ባሉበት የቁንጅናው ውድድር ተካሄደ።”



“1ኛ ጣይቱ ይልማ ሆነች። ጣይቱ ይልማ ለውድድር የቀረበችው ከሰቀልት ወረዳ ከመቋሚያ ማርያም ሲሆን የደጃዝማች ይልማ አስፋ ልጅ ናት።”

“2ኛ የወጣችው ወይዘሮ ተዋበች የተባለች ናት። ተዋበች እስላም ስትሆን ባልዋም መሐመድ ኩርማን ይባል ነበር። ተዋበች 2ኛ ለመውጣት የቻለችው በጠጉርዋ ማማር በቁንዳላዋ አወራረድና በሹርባዋ አረዛዘም ነበር” ሲሉ ጽፈዋል።

የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር በተባለው መጽሐፍ ገጽ 264 “የሴቶች ቁንጅና ውድድር እንዳደረጉ” ሲሉ ጽፈዋል። በኢትዮጵያ የሰውነት ማጠንከሪያ (እስፖርት)ከጥንት ጀምሮ ያለ ሲሆን ብዛት ያላቸውን የሰውነት ማጠንከሪያ ነገሥታቱ መመልከት ብቻ ሳይሆን ይጫወቱአቸው ነበር።

በተለይ የፈረስ ጉግስና ዋና ገበጣን መኳንንቱ ይጫወቱአቸው እንደነበር የታሪክ ሰነድ ምስክር ሲሆን ምክቶሽና ገና ጨዋታን፤ ንጥቂያንና ትግልን ሌሎችንም አዝናኝ ጨዋታዎች ታላላቅ ሰዎች እየተመለከቱ ወጣቶቹ ይጫወቱ ነበር። ዘመናዊው ደራስያን አጤ ልጅ ኢያሱን ከሚነቅፉበት አንዱ ፈረስ ግልቢያ ያዘወትራሉ እያሉ ነው። ሌሎችንም የሰውነት ማጠንከሪያ ዛሬ በአውሮፓ የሚደረገው ውድድር በኢትዮጵያ የነበረ ነው። በተለይ ነጻ ትግል የሚባለው ጨዋታ ዛሬ የአውሮፓ የሰውነት ማጠንከሪያ ተደርጎ የሚወሰደው ብሀገሬ ላም ጠባቂው የሚጫወታቸው ጨዋታዎች ነበር።

ዛሬ በአሜሪካ (ቤዝ ቦል)ተብሎ የሚጠራው ግፊያ የሚበዛበት ጨዋታ ከኢትዮጵያ ዘላን ላም ጠባቂዎች ተኮርጆ የመጣ ነው። ላም ጠባቂው ማታ ከብቱን ከበረቱ ካስገባ በኋላ ራቱን በልቶ ዳኛው በቡድን በቡድን ለይቶ ያሰልፋቸዋል። ከዚያም የጋለውን ደንጊያ በእርጥብ የእንጨት ልላጭ ይዞ ይወረውረዋል። ሁሉም የጋለው ደንጊያ ወደ ሄደበት እየሮጠ ይሄዳል። ደንጊያውን ያገኘው ሰው የሚፈልግ መስሎ ሩጦ ለዳኛው ያስረክባል።

ከነቁበት ግን ይይዙታል ሌላው ሲያነሣ አንዱ እጁን ሲበላ ሲጥለው ያኛው ሲቀበል ሲታገሉ አንዱ ቡድን አጥቅቶ ለዳኛው ያስረክባል ይህ ጨዋታ በሌሎች አገር የሌለ በኢትዮጵያ ብቻ ያለ ነው። ይህ

ጸሐፊ ይሆን ጨዋታ በጎንደር ክፍለ ሀገር ጎንደር ዙሪያ አውራጃ ታች አርማጭሆ ተመልክቶአል:: በኢትዮጵያ የተለያዩ የሰውነት ማጠንከሪያ የአካል ማጎልመሻ ጨዋታዎች ብዙ ናቸው:: ሌላው ቀርቶ በአብነት ትምህርት ቤት ውስጥ እንኳን የተለያዩ ጨዋታ ይጫወት እንደነበር የአብነት ተማሪ የነበሩት እንዲህ ሲሉ ገልጸዋል::

መንግሥቱ ለማ <u>መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 21 "ስድስት ሰዓት ሲሆን ይወጡና የተደላደለ ቦታ አለ እዚያ ላይ ሁነው ተማሪውን ትግል ያታግላሉ መምህሩ እንዲማር ትግል ገና ጨዋታም አለ ኳስም አለ:: ሰዓት አላቸው ወርደው ያጫውታሉ" ሲሉ አለቃ ለማ መናገራቸውን ጽፈዋል::

በዘመናችንም መምህር ጌጡ ተሰማ፤ በጳጉሜ ተማሪዎቻቸውን ውኃ ዋና ያስተምሩ እንደነበር ተማሪያቸው ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ነግረውኛል::

ኢትዮጵያ ውስጥ ብዛት ያላቸው የሰውነት ማጠንከሪያ ውድድሮች ይካሂዱ ነበር:: በአጤ ቴዎድሮስ ዘመንም የተለያዩ የሰውነት ማጠንከሪያ የአካል መገንቢያ የአእምሮ ማንቂያ እስፖርቶች ይካሄዱ ነበር:: ይህ በአደባባይ ሕዝብ እየተመለከተ ዳኞች ተመድበው የሚያጫውቱበት ሲሆን ከሚገርመው ነገር ውድድሩ ሴቶች ዛሬ በሰከንድ በቅጽበት እንደምንለው እየሮጡ ክሩን ከመርፌው ማስገባት ውድድር ነበር::

በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ቀጭን ፈትሎ ጋቢ፤ኩታ ሌላም ሌላ ልብስ ለሚሠሩ ሁሉ እርሳቸው ለማጠናከር ሲሉ ይሸልሙ ነበር:: እርሳቸው የተመለከቱት በልማት መልክ ሴቶችን ማጠናከሪያ በማድረግ ነበር:: አንዷ መልከ ጥፉ ጥሩ ኩታ ፈትላ ለአጤ ቴዎድሮስ በመስጠቷ ተሸለመች:: መልከ ጥፉዋ መሸለሟ ጉድ ተባለና መልከ ቀናዋ "ይች ጉዳጉድ በአጤ ቴዎድሮስ ከተሸለመች እኔይቱ ልጅትማ ብዙ ልሸለም እችላለሁ ብላ" ወደ አጤ ቴዎድሮስ ቀረበች::

አጤ ቴዎድሮስ "የኔ እኅት ሙያሽ የታለ? ሲሉአት መልካም ጥርሶቿን ገልጣ ልትማርክ ስትፈልግ አጤ ቴዎድሮስ "ታዲያ ይህን መልክና ቁንጅና ይዘሽው ሰነፍ ከሆንሽ መቸም አልሠራችበት ንሳ



ቀኝ እጇን ቁረጥልኝ" ብለው አስቆረጧት:: የዚችን ሴትዮ ተግባር አስመልክቶ መጋቤ አእላፍ መክብብ አጥናው፤ በግጥም መጽሐፋቸው እንዲህ ሲሉ ገልጠውታል::

መጋቤ አእላፍ መክብብ አጥናው <u>ሁለ-ገብ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 69-70 "ተከብራ ስትኖር በውበቷ ኮርታ
ሙሽራም በመምሰል የምትለብሰው ኩታ
የጌጣ ጌጥ ብዛት የሸቶው ጋጋታ
ልብ የሚያስኮበልል ራስ የሚመታ
በአጤ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ገብታ
እጅ መንሣት ፈለገች መልካም ከበሬታ::"

"ታዲያ ቴዎድሮስ አደገኛ ፍጥረት
ለማወቅ ፈልገው ምን ሙያ እንዳላት
ለዚያ ሁሉ ውበት ዋጋ ባለመስጠት
በዐይነት ወጥ መሥራት መፍተል ወይስ ስፌት
ምን ሥራ ታውቂያለሽ?ብለው ሲጠይቋት
መልስ አላገኘችም ጭራሽ ግራ ገባት
ጥያቄው ቀጥሎ ሲደጋገምባት
አማራጭ ብታጣ ትምክህት ሙያ መስሏት
ዕድሜ ለገረዶች የአባት የእናቴ ሀብት
ለአራዊት ይተርፋል እንኳን ለሰው ፍጥረት
እያለች ስትፎክር ንግግሯ ሳያልቅ
ወደ ቁጣ አመራ የቴዎድሮስ ሳቅ::"

"ሌላውስ ይቅርና አሉ ቴዎድሮስ
በአቴኩሮት እያዩ የጣትዋን መለስለስ
ሌላውስ ይቅርና ይኸው የለበስሽው
አይምሰልሽ አንች ፈትለሽ ያሠራሽው
ታዲያ የሌሎቹ ትጉሆች መታጫ
ለመሆን አይችልም የሰነፍ ማጌጫ
ያምሻል?ንገሪኝ ምን በሽታ አለብሽ?
እንጃ አይመስለኝም ሙሉ ጤነኛ ነሽ::"

"ሁለት እጆች አሉሽ ምን ያደርግልሻል
ለምግብ ከሆነ አንዱ ይበቃሻል

ንሣ ቁረጥላት አንዱን ጎምደህ ጣለው
ለማይሠራ ሰነፍ መቀጣጫው ይህ ነው
ብለው ትእዛዝ ሰጡ በሥራ ላይ ዋለ
አንድ እጇ ተጎምዶ ተቆምጦ ተጣለ" ሲሉ ጽፈዋል::

ይቺ ሰነፍ ሴት ተቅለብልባ ባትሄድ ኑሮ አንድ እጇን አጥታ አትመለስም ነበር:: ይህ ሰነፍ ካልሠራ አይብላ ያሉ ይመስላል አጤ ቴዎድሮስ፤ አንዴ ደግሞ የዋና ውድድር ሁኖ የአጠቃውን ሲሸልሙ የተመለከተ፤ ወታደር ዋና ሳያውቅ ዋና ከሚያውቀው ወታደር ጋር ይገባል::

አጤ ቴዎድሮስ ሲመለከቱት ዋና እንደማይችል ገብቶአቸው አንዱን ወታደር ይጠሩና "አጥልመህ ልቀቀው" ብለው አዘዙት:: ያም ወታደር እንደታዘዘው አጥልሞ ሲለቀው ውሃ ሞልቶበት እየሳበ አውጥቶ ከመሬት ሲጥለው ሆዱ ቅምጫና አክሎ የጠጣውን ውሃ እየረገጡ አፈሰሱለት:: ነፍሱን ሲያውቅ አጤ ቴዎድሮስ አስቀረቡና "ወጡ እንውጣ አቅምህን እወቅ" ሲሉ ለቀውታል:: የሴቶችን ቁንጅና ውድድር በተመለከተ አቶ ገሪማ ታፈረ የዘገቡትን::

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 87 "የንጉሠ ነገሥቱ ሽራ ድንኳን ተተከለ:: ከጧቱ ከ3 ሰዓት ጀምሮ በዓሉ ወደሚከበርበት ሜዳ የከተማውና የገጠሩ ሕዝብ ይጎርፍ ጀመር:: 4 ሰዓት ሲሆን ምርጥ መሣሪያ የያዙ ወታደሮችና አጋፋሪዎች ሰልፈኛውን ለማስተናበር ጸጥታውን ለማስከበር በበዓሉ ሜዳ ተሰማሩ:: ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ፊታውራሪ ገብርዬ በሠራዊቱ ታጅቦ ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለበ አጤ ሰቀላ ደረሰና የዙፋኑን አቀማመጥ ተመለከተ::"

"እንዲሁም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በፈረሶች በሚሳብ ሠረገላ ተቀምጠው ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ቤል ባሠለጠናቸው ወታደሮች እየታጀቡ መጥተው በዙፋናቸው ላይ እንደተቀመጡ እምቢልታና መለከቱ፤ተብላላ ነጋሪት አጅብር፤አጅብር ውጋው ውጋው እያለ ይጎሰም ጀመር! ዘፋኞች ይዘፍናሉ:: አዝማሪዎች ይዘምራሉ፥ ወታደሮች ይጨፍራሉ፥ በዚህ ዓይነት ይዞታ ተድላ ደስታ ሆኖ ሲደባለቅ በመካከሉ ለውድድሩ የታጩት ወይዛዝርት



ጥልፍ ቀሚሳቸውን እያንሰረተቱ፥ ተቀብተው ተኩለው፥ ወደተዘጋጀላቸው ቦታ ያልፋሉ::"

"ቀጥሎም ምርጫው በሚፈጸምበት ጎል እየገቡ ውበታቸውና ደም ግባታቸው የላሕየ ገጻቸው አወራረድ የጸጉራቸው ስሬት፥ የቁንዳላቸው ርዝመት፥ሽንጣቸው ዳሌና ተረከዛቸው እየተመረመረ የምርጫው ሥነ ሥርዓት ይጀምራል በመካከሉ በሰቀልት ወረዳ ከመቋሚያ ማርያም የመጣችው ትውልዷ ከመቄት አዝማች ወገን የሆነ የደጃዝማች ይልማ አሰፋ ልጅ ጣይቱ ይልማ አንደኛ ስትሆን እንዲሁም በጎንደር አዲስ ዓለም የመጣችው የመሐመድ ኩርማን ሚስት የሸኽ መሐመድ ጌታ ልጅ ተዋበች የተባለችው እስላሚቱ በጠጉሯ ማማር በቁንዳላዋ አወራረድና መርዘም ሁለተኛነትን አግታለች::"

"ከዚህ በኋላ ዮሐንስ ቤልና ፊታውራሪ ገብርዬ የምርጫውን ውጤት ለንጉሠ ነገሥቱ ለመንገር ወደ ዙፋን ይቀርባሉ:: ወዲያውም ጣይቱ ይልማ አንደኛ ተዋበች መሐመድ ጌታ ሁለተኛ መሆናቸውን ከገለጹ በኋላ ተመራጮች ከዙፋን ፊት በመቅረብ እጅ እየነሡ ሽልማታቸውን ተቀብለው የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖ በ7 ሰዓት እንደተለመደው ለመሳፍንት ለሊቃውንት ለመኳንንትና ለካህናት የምሳ ግብዣ ተደረገ" ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ ለባህል ልብስና ለቁንጅና ውድድር ብሎም ለሥነ ጽሑፍ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ለምሳሌ ሥነ ቃል ማለት ራሱ ሀብት ነው:: ሥነ ቃል ባለብዙ ሐረግ ነው:: ሥነ ቃል ስለ ኀዘን ስለ ደስታ ስለ ሽለላ፤ስለ ሥነ ጽሑፍ፤ስለ ግጥም ስለ ፍልስፍና፤ስለ ጀግንነትና ቀረርቶ ስለ ፍከራ ስለ መዝሙር ብዙ ትርጉም አለው::

ሥነ ቃል የአንድ ማኅበረሰብ ለዘመናት ባህል የአስተሳሰብ የእምነት ፍልስፍና ወግ ታሪክ ወዘተ መግለጫ ቅርስ ሲሆን በተለይም ደግሞ መረጃን በጽሑፍ ማስተላለፍ በማይቻልበት ጊዜ በመረጃነትና በመልእክት ምንጭነት ከፍተኛ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ የኢትዮጵያ ሀብት ሥነ ቃል ባህላዊ ስኬት የነበረ ነው::

ሥነ ቃል በትረካ አልያም ደግሞ በግጥም ስሜትን ማስተላለፍ ይቻላል:: ለምሳሌ በዛሬው ወቅት የተረሳው አንዱ ሥነ ቃል

“እንቆቅልሽ”ነው። እንቆቅልሽ በጣም ከባድ የሥነ ቃል አንዱና መሠረታዊ ታሪክን የሚዳስስ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በዜና መዋዕልና በነገሥት ላይ ተጠቅሶ የምናገኘው “ንግሥተ አዜብ ንጉሥ ሰሎሞንን በእንቆቅልሽ ልትፈትነው ሄደች” የሚለው ይሆናል።

ለዚህም ነው ንጉሥ ሰሎምን የእስራኤል ንጉሥ እንጂ የዓለም ንጉሥ አለመሆኑን በእንቆቅልሽ የተረዳችው። እንቆቅልሽ እንዲሁ በሥነ ቃል የነበረ የኢትዮጵያ ሀብት ነበር። ዛሬ ግን ተረስቷል ጠፍቷል። ምንም እንኳን ይህ መጽሐፍ የሚያወራው ሌላ ቢሆንም ስለ እንቆቅልሽ እንዳይረሳ ሁለት መጠይቆች ልጠይቃችሁ ፍቿን ክፍል 13 ምዕራፍ 1 ከመጨረሻው ላይ ጽፌዋለሁ።

1ኛ እንቆቅልሽ--ድሃ የሚጥላት ሀብታም በኪሱ የሚይዛትን እወቅልኝ?
2ኛ እንቆቅልሽ--ከድሃ ቤት ተሎ የምትገኝ ከሀብታም ቤት ተሎ የማትገኝ እወቅልኝ?

አንባብያን ሥነ ቃል እንቆቅልሽም ነው። ሥለ ሥነ ቃል ይህን ካልኩኝ በኋላ ደግሞ ወደ ምዕራፉ መነሻ ልመለስ። አጤ ቴዎድሮስ በዚህ በሥነ ቃል የፈጸሙአቸውን ተግባራት ዘርዝር አድርጎ መግለጽ አስፈላጊ ይመስለኛል። ለዚህም በዘመኑ ከነበሩት የተለየ ስጦታ በሥነቃል የታወቁ ናቸው። በሥነ ግጥም በመጀመሪያ ደንቢያ ላይ ከደጃዝማች ጎሹ ጋር በነበረው ጦርነት ላይ ደጃዝማች ገልሞ በጦር ሲወጉና ደሙ አስከሬቸው ሲውረገረጉ የተመለከቱ የደጃዝማች ጎሹ አዋጊ እንዲህ ሲሉ ገጠሙ።

“አይሸሽም ያልከው ገልሞከ ሸሼ
የደንቢያን ሜዳ እያበላሼ”

ብለው በሥነ ቃል ግጥም ሲያሰሙ ደጃዝማች ካሣ አጤ ቴዎድሮስ በጦርነቱ ሰዓት በሥነ ቃል በግጥም እንዲህ ሲሉ መለሱ።

“አብለሽ ነው እንጂ አልተናገርሽም
በዙበት እንጂ ገልሞስ አልሸሸም”

ብለው መልሰዋል። ሥነ ቃል ለኀዘንም እንዲሁ ይውላል። በዚህ ሥነ ቃል አጤ ቴዎድሮስ ተጠቅመውበታል። ረዳታቸውና መካሪያቸው ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች በማረፋቸው ምክንያት ኀዘናቸው ከባድ



ነበር። አስከሬን ሳይቀብሩ ሽፍታ ለማደን አገር ለአገር ሲዞሩ ቆይተው ከቀበሩ በኋላ እንዲህ ብለው ገጥመዋል።

“ብዙ ሥራ አዋቂ ትናንት ተቀበረች!
መድኃኒቱን ምሳ ታበላኝ ነበረች!
እስኪ ጠይቁልኝ እርቃ ሳትሄድ!
እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ወይ ገረድ” አሉ።

በማለት ገጥመዋል። እንዲሁም ጀግንነትን አስመልክቶ ፈጣን በሥነ ቃል ግጥም ይመልሱ ነበር። ለምሳሌ ትግራይ ከተሻገሩ ይሞታሉ እያሉ የትግራይ ሽፍቶች ያስወሩ ስለነበር ተከዜ ደርሰው በጎሽ ዋንጫ ውሃውን ከጠጡ በኋላ እንዲህ የሚል በሥነ ቃል ግጥም አዝማሪ አብተውን አስጠርተው ገጥመዋል።

“ተከዜን ሲሻገር ይሞታል እያሉ
መጽሐፉ ታጠበ ያባይ ጠንቋይ ሁሉ
ወርሒን ስንደግመው እንግዲህ ምን ይሉ

በማለት ገጥመዋል። ወርሒን ማለት ትግራይ ውስጥ ያለ ወንዝ መሆኑን ገሪማ ታፈረ አባ ታጠቅ ካሣ ከተባለው መጽሐፋቸው ላይ ገልጸዋል። እንዲሁም በጦርነት ሰዓት አንድ ቄስ የመነኩሴ ቆብ ደፍቶ “በለው የዚህን ንጉሥ ጦር”እያለ ሲያዋጋ ተማረከና ከእርሳቸው ቀርቦ ሲወሸክት ተመልክተው እንዳትዋሽ አሉት። ቄሱ ሓልዋሽም ካለ በኋላ ከፍርሀቱ የመጣ አመለጠውና ልብሱ መበስበሱን ከተመለከቱ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ እንዲህ ሲሉ በሥነ ቃል ግጥም ገጠሙበት።

“አልዋሽም ያልከው ምነው ቄሱ ዋሸህ
ልብስህን ተመልከት እንዳ ተበላሸተህ”
ብለውታል።

አጤ ቴዎድሮስ ቅድሚያ ቸንከር ተክለ ሃይማኖት ኋላም ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ያደጉ በመሆናቸው ጥሩ የሥነ ቃል እውቀት ነበራቸው። ሥነ ቃል ሥነ ጽሑፍን ይወልዳል። ሥነ ጹሑፍ ደግሞ ለታሪክ ዋናው መሠረት ነው።

አጤ ቴዎድሮስ በሥነ ቃል የበለጸጉ በመሆናቸው ለሥነ ጽሑፍም አስተዋጽኦ አድርገዋል። ቀን ተሌት የሚያደርጉትን ተከታትለው እንዲጽፉ ሰዎችን አዘጋጅተዋል ለዚህም ነው ዛሬ "እገሌ የጻፈው"እያልን ለምርምር የምንጠቀምበት ሥነ ጽሑፍ እንዲዳብር ስላደረጉ ነው። ትምህርት ቤት መከፈቱ የሥነ ጽሑፍ እድገት እንዲበለፀግ ጥረዋል።

በኢትዮጵያ ፊደላት በውጭ አገር የተጻፉትን መጻሕፍት ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ አስደርገዋል። ይህን ታሪክ በተከታታይ በሩሕ መጽሔት ከታሪካችን በተሰኘው ዓምድ ላይ ከፈለ ማሞ "የኅትመት ኢንዱስትሪ ታሪክ በኢትዮጵያ ከመርሐ ጥበብ ምሥረታ እስከ ውርሰ ዘመቻ"በሚል ደጋግመው ታሪክ ጠቅሰው ለንባብ አብቅተዋል። ረጅሙን ታሪክ ተወት አድርጌ ከአጤ ቴዎድሮስ ላይ ሲደርሱ የጠቀሱትን አጠር በማድረግ ጥቅስ ልውሰድ።

ከፈለ ማሞ <u>ሩሕ መጽሔት</u> 1986 ዓም ገጽ 31 "በ19ኛው ምዕት ዓመት መግቢያ ላይ ሁለት ሌሎች ለኅትመት ኢንዱስትሪ መስፋፋት አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ክስተቶች ነበሩ። ለሥልጣኔ አንጎሉ ክፍት የነበረውና ከዘመኑ ሰዎች በምዕተ ዓመት ቀድሞ አሳቢ የነበረው የቋራው ቴዎድሮስ ሊወለድ ሁለት ዓመት ሲቀረው ከ1818-1820 ባለው ጊዜ አባ አብርሃ በተባሉ ኢትዮጵያዊ ሊቅ የተተረጎመው የተሟላ መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ ፊደላት በአማርኛ ቋንቋ ታተመ። ያስተረጎመው በካይሮ የፈረንሳይ ቆንስል ነበር።"

"ቆንስሉ ያንን ክቡር ትርጉም ለእንግሊዝ የባሕር ማዶ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ሸጠው። የተባለው ድርጅት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እያተመ መሸጥን ቀጠለ። ሁለተኛ ሥልጣኔ አገራቸው እንዲገባ ሌት ተቀን አሳቢና ዓላሚ የነበሩት ቴዎድሮስ ለአገሩ መሪነት በበቁበት ዕድሜ በሚሲዮናውያን አማካይነት የመጽሐፍ ቅዱስን በአማርኛ መታተም ስለተረዱ በብዛት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባና በመነኮሳትና በካህናት ሳይቀር እንዲነበብ መፍቀድ ብቻ ሳይሆን አተጋጉ"።

"አጤ ቴዎድሮስ የገጠማቸው የሥልጣኔ እንቅፋት ለቁጥር የሚያታክትና እርሳቸውንም የሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ



ቢያደርጋቸውም በሕይወት እስካሉ ድረስ ያላለሙት በዓይን ሕሊና ያልነደፉት ጅምር አልነበረም።"

"በተለይ ርእሰ ጉዳያችንን በሚመለከት በመቅደላ ላይ የከፈቱት የመጀመሪያ ቤተ መጻሕፍት በኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ ውስጥ ኢንፎርሜሽን ወይንም እውቀት አብሪ ዜና የማከማቻት፤ የመጠቀም ለትውልድ የማስለታተፍና በአንድ ሥፍራ የማማከልን ተግባራት በበኩርነት የመሠረቱ መሪ ያደርጋቸዋል።"

"ከዚህም በቀር ንጉሠ ነገሥቱ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሌላቸው ሕዝቦች እንደባቢሎኑ ግንብ ሕዝቦች እየተናገሩ የማይግባቡ ሕዝቦች እንዳይሆኑ በማወቅ በዘመኑ ሊጻፍ የበቃውንና የሚጻፉበት ፊደላትም የነበሩትን አማርኛን የመንግሥት ሥራ ማካሄጃ የጋራ መግባቢያና የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ሆኖ እንዲዳብር የሞከሩ ንጉሠ ነገሥት ናቸው።"

"አጤ ቴዎድሮስ አዋጅ አውጥተው አማርኛ የጽሑፍ ቋንቋ ይሁን ብለው ሳያስነግሩ ግዕዝን ተክቶ የሥራ ጽሑፍ ቋንቋ እንዲሆን ለማብቃት በማሰባቸው በጸሐፌ ትእዛዛቸው በደብተራ ዘነብ የተዘጋጀውን የራሳቸውን ታሪክ በአማርኛ እንዲጻፍ አደረጉ።"

"ቴዎድሮስ የአካባቢውን ግፊትና ተፅዕኖ በመቋቋም በውጭ አገር በኢትዮጵያ ፊደላትና ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስና ሌሎችም መንፈሳዊ መጻሕፍት ኢትዮጵያ እንዲገቡና እንዲነበቡ ያደረጉትኮ ለሕዝባቸው አንድ የሥልጣኔ ፍንጭ እንደሚያስገኝላቸው ስለተገነዘቡ ነበር። ይህንንም ግንዛቤያቸውን እ.ኤ.አ.በ1856 ዓም ማርቲን ፍላድ የተባለው ሚሲዮናዊ 300 የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ አምጥቶ ሲያስረክባቸው ከሰጡት መግለጫቻው እንረዳለን።"

"መጽሐፍ ቅዱስ የሰጡንና አሁን መንደሩ ባለመጽሐፍ ቅዱስ እንዲሆን ሲሉ ደስታቸውንና ባለውለታነታቸውን ገልጸዋል። ስለዚህም ቴዎድሮስ በውጭ አገር በኢትዮጵያ ፊደላትና ቋንቋ የተዘጋጁ መጻሕፍት ወደአገራቸው እንዲገቡ የመግባቢያ የሥነ ጹሑፍና የመንግሥት ሥራ ማካሄጃ ቋንቋ እንዲደረጅ አርአያ በመሆን እውቀት ተወራራሽ ባህልና ሥነ ጥበባት በአንድ" ይቀጥላል ሲሉ ጽፈዋል።

# ክፍል አምስት

## ምዕራፍ 1

### እቴጌ ተዋበችና እቴጌ ጥሩወርቅ!

<u>መጽሐፈ ምሳሌ</u> ም÷12 ቁ÷4 "ልባም ሴት ለባልዋ ዘውድ ናት"ይላል። ልባም ሴት ለባልዋ ዘውድ ናት የተባለው ትክክል ነው። የአበው አነጋገር ደግሞ "የውጭ ቀጋ የባል አልጋ" አልያም ደግሞ የቤት አልጋ የውጭ ቀጋ" ይላሉ።

አንዳንድ ሴቶች ለተመልካች ክፉ ሲሆኑ ለባላቸው ደግሞ እጅግ መልካም ናቸው። ከተፈጥሮአቸው ባለቤታቸውን የሚያከብሩ ሴቶች ባለቤታቸው ሰነፍ ቢሆን እንኳን እየመከሩ ጀግና ያደርጉታል። የአበው አባባል "ሴት የላከው ጅብ አይፈራም" ይላሉ። ይህን የሚያደርጉ ሴቶች ልባሞች ናቸው። ልባም ሴቶች ባላቸውን ብቻም ሳይሆን ለአገራቸው ጥቅም የሚጥሩ ናቸው። የአጤ ቴዎድሮስ ባለቤት እቴጌ ተዋበች አሊ ለባለቤታቸው መኩሪያና አለኝታ ነበሩ።

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 45 "ተዋበች ተመልክተው" መጥቶልኻል ታጠቅ የሚል ድምፅ አሰሙ። በዚህ ጊዜ አባ ታጠቅ ብለው ፎከሩና ወደስልፋቸው አለፉ" ሲሉ ጽፈዋል። እቴጌ ተዋበች "ታጠቅ" ስላሉአቸው ልጅ ካሳም "አባ ታጠቅ" በማለታቸው የአጤ ቴዎድሮስ የፈረስ ስም ሆነ። በመጀመሪያ የሚፈክሩት" መይሳው" ካሳ እያሉ ነበር እቴጌ ተዋበች በደጃዝማች ወንድ ይራድ የሚመራው ጦር ካጠገባቸው ደርሶ በማየታቸው "ታጠቅ" ስላሉ ፈረሳቸው ሁኖ ይጠሩበታል። እድለ መልካም ሴቶች ለባሎቻቸው ዘውድ ናቸው።

በኢትዮጵያ የሥነ መንግሥት ፖለቲካ አስተዳደር ከባሎቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር ሁነው አገር የመሩና ያስተባበሩ ብዛት ያላቸው እናቶቻችን ነበሩ ዛሬም ባይበዙም ከባልንጀሮቻቸው ጋር ሁነው



ለአገር አንድነት የሚታገሉ አሉ። ለምሳሌ ዳኛ ብርቱካን ሜደቅሳን መጥቀስ ይቻላል።

ቀደም ሲል ከንግሥተ ነገሥታት ሳባ በፊት ጀምሮ የኢትዮጵያ ሴቶች አገር በመምራት ደረጃ ቁጥራቸው ብዙ ነበሩ። በ1013 ዓመተ ዓለም የነገሡት ንግሥተ ነገሥታት ሳባ ከሕገ አበው መምህራን ሲነገር የመጣው "የዓለም መድኃኒት በኢየሩሳሌም ይወለዳል"ሲባል ይሰሙ ስለነበር ነጋድራስ ታምሪን 73 የንግድ መርከብ በላይ የነበረው ነጋዴ በቻይናና በህንድ ኑሮ በኢየሩሳሌም ሲመጣ የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብ በማየቱ ለንግሥተ ነገሥታት ሳባ ያበስራል እርሳቸውም የዓለም መድኃኒት የተወለደ መስሏቸው ወደ ኢየሩሳሌም በብዙ ንጉሦችና ንግሥቶች ታጅበው ሄዱ።

ብልህነታቸውም በእንቆቅልሽ ፈተኑት እርሱም የዓለም መድኃኒት አለመሆኑን ነገራቸው እርሳቸውም ሆኑ የአዘቦ ንግሥት ሳሆዬ ከእርሱ አርግዘው ተመለሱ። ንግሥተ ነገሥታት ሳባ ቀዳማዊ ምኒልክን ንግሥት ሳሆዬ ዛገን ወለዱ። በዚህ ምክንያት ኦሪት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ሆነ። እንዲሁም ከክርስቶስ ልደት በኋላ የንግሥት ሕንደኬ በጆሮንድ ባኮስ ወይም ጃንደረባው ኢየሩሳሌም በሐዋርያው ፊልጶስ ተጠምቆ የመጣው የንብረት ሹም ነበር።

ኋላም ሐዋርያው ማቴዎስን አስተናግደው ክርስትና የተነሡት ንግሥት ሕንደኬም ሆኑ ሌሎችም ብዛት ያላቸው ጀግኖች አገር ለማስተዳደርና ሃይማኖት ለማስፋፋት ጥረት አድርገዋል። በ330 ዓም ላይ በኢትዮጵያ ክርስትና ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ሁኖ እንዲታወጅ ካደረጉት መካከል ልጆቻቸውን በመርዳት አብረው የቆሙት የአጤ አብርሃ ወአጽብሃ እናት እቴጌ ሶፍያ÷ ናቸው።

ምንም እንኳን የክርስቲያኑን መዋቅር ይደምስሱ እንጂ ንግሥት ዮዲት ጌዴዎን አንዷ ጀግና ሲሆኑ በ1515 ዓም ጀምረው በኢትዮጵያ ሊፈነዳ ያለውን የሃይማኖት ጦርነት ለመቅጨት ከውጭ ኃይሎች ጋር ግንኙነት ሲያደርጉ የነበሩት እስላም ሃይማኖት አማኝ ኋላ ክርስትና የተነሡት የሃዲያ ተወላጅ እቴጌ እሌኒ ናቸው።

አጤ ልብነ ድንግል በንዝህላልነት ሲንዘላዘሉ እናታቸው ብዙ ጥረት አድርገዋል። ኋላም ላይ አጤ ልብነ ድንግል ሲሞቱ ሚስታቸው

ትግሬዋ የመቀሌ ተወላጅ እቴጌ ሰብለ ወንጌል ልጃቸውን አጤ ገላውዴስን ለመርዳት የመጡትን ፖርቱጋሎች በማጠናከር ከፍተኛ ጀብድ የሠሩ ሲሆኑ በሌላው አንጻር የአጤ ግራኝ አህመድ ባለቤት እቴጌ ድል ወንበራ ጀግና ሴት ነበሩ።

በተለይም ራሱን ችሎ ስለ ሁለቱ እቴጌዎች ጥናት ቢደረግ በድርድር ወይም በፈረንጅ ቋንቋ በዲፕሎማሲ ተግባብተው ልጆቻቸውን እንዴት በእየጃቸው እንዳስገቡ ያስመሰግናቸዋል። ለምሳሌ አጤ አህመድ ግራኝ የማረኩትን ክርስቲያን ለዐረብ ባርያ ይሸጡ ስለነበር የአጤ ልብነ ድንግል ልጅ አቤቶ ሚናስ የኋላው አጤ ሚናስ፤ አቡዘቢብ ለባርነት ተሸጡ።

በአንጻሩ የአጤ ግራኝ አህመድ ልጅ ወገራ በአጤ ገላውዴዎስ እጅ ወደቁ። በዚህ ሰዓት ሁለቱ እቴጌዎች ተላልከው ልጆቻቸውን ተመላልሰዋል። በጎንደር ከተማ ራሱን ችሎ የሚገኘኝ ቁስቋም ቤተ ክርስቲያንን ያሠሩት እቴጌ ምንትዋብ የንጉሠ ነገሥት አጤ በካፋ ባለቤት ሲሆኑ ባላቸው ሲሞቱ ከልጃቸው ከአጤ ኢያሱ ጋር ሁነው የኢትዮጵያን መንግሥት ሲመሩ ቆይተዋል።

ኋላም ልጃቸው አጤ ኢያሱ በካፋ ሲሞቱ ከልጃቸው ልጅ ከአጤ ኢዮአስ ጋር ሁነው የአገር መምራቱን ተግባር ተረክበው ሲያስተዳድሩ ኑረዋል። በዚህ ወቅት የአጤ ኢዮአስ እናት እቴጌ ቤርሳቤህ "ዛሬስ የአገር የማስተዳደሩ ተግባር ለእርስዎ ሳይሆን ለእኔ ይገባል ብለው" አማታቸውን ከሥራው አስወግደው እርሳቸው ከወሎ ኦሮሞዎች ቤተሰቦቻቸው ብዙ ጦር አስመጥተው መንግሥት መምራት ጀምረው ነበር።

ምንም እንኳን የዘመነ መሳፍንቱ አስተዳደር ይሁን እንጂ የትንሹ ራስ አሊ እናት እቴጌ መነን ጀግና መሆናቸውን የሚያሳየው ደጃዝማች ካሣን ለመግጠም ራሳቸው ጦር መርተው የሄዱ ናቸው። የልጃቸው ልጅ የአጤ ቴዎድሮስ ሚስት እቴጌ ተዋበች አሊም ለልጅ ካሣ አንድ የብልት ሥጋ አያታቸው እቴጌ መነን በመላካቸው በመበሳጨት ሲያነቃቁአቸው እንዲህ ብለው ነበር።

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 43 "የትግሉ ተካፋይ የሆነችውና የሚወዷት ሚስታቸው ወይዘሮ ተዋበች



በሁኔታው ከርሳቸው ይልቅ አጥብቃ ስለተቆጣች ልክ ካሣ ወደተኛበት ክፍል ገብታ ከአጠገባቸው ቆም ብላ እንዲህ እያለች ታንቃቃቸው ጀመር። ሲሆን መጥኑ ተግበስብሶ በተቀበሉን ነበር? በቀርስ ድልብ ፍሪዳ ቀሚስ ለብሶ ሥጋው በመልከኛ ጠጁ በገንቦኛ በተላከልን ነበር? እንዴት እንደምን ብንናቅ ነው አንድ ብልት ሥጋ የተላከልን ከአለች በኋላ በተጨማሪ ጀግኖችን እወዳቸዋለሁ፥ አከብራቸውአለሁ ፥ፈሪዎችን ግን እንቃቸዋለሁ አብሬአቸው ለመኖርም አልፈቅድም፥ የሚል ኃይለ ቃል ታሰማ ጀመር" ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ከካህናቱ ጋር አታካሮ ከገቡ በኋላ ቀሳውስቱ እርሳቸውን ለመጣል ያልተቆጠበ ጥረት አደረጉ። ከሥልጣን ለመጣል ብቻ ሳይሆን አጤውን ለመግደል ሞክረዋል። ካህናቱ አጤ ቴዎድሮስ ሥጋ ወደሙ ለመቀበል ሲቀርቡ መርዝ ጠቅቅለው ሊያቆርቧቸው ሲሉ ነቁባቸውና "በመጀመሪያ አንተ ቁረብና እኔን አቁርበኝ" ብለው ሲያፈጡበት ራሱ ቀምሶ ፍግም ብሏል።

አንድ ወዳጄ በግእዝ የተጻፈ መጽሐፍ ያላቸው "ስሜን አትጥቀስ ካህናቱ በሕይዎት እያለሁ ከኅብረተሰቡ ጋር እንድኖር አያደርጉኝም። ታሪኩን ግን እየተረጎምኩኝ እነግርሃለሁ" ሲሉ ቃል አስገብተውኛል። እኔም ትክክለኛ ስማቸውን አልገልጽም። እርሳቸው በዚህ ስም ተጠቀም ሲሉ በሰጡኝ ስም አሰግድ ድሌ እያልኩኝ እጽፋለሁ። እኔ የሰማሁትን ታሪክ ቁሶችን ፈርቼ ሳልጽፈው አልቀርም።

አቶ አሰግድ ድሌ <u>በግእዝ የተጻፈ መጽሐፍ</u> ያላቸው "አጤ ቴዎድሮስ ከካህናቱ ጋር እየተካረሩ ስለመጡ እነሱም አልተኙላቸውም። አጤው ከቦታ ቦታ ሲንከራተቱ ደብረታቦር ላይ ካህናቱ እቴጌ ተዋበች ሲቆርቡ መርዝ አቅምሰዋቸው በዚሁ ምክንያት ታመው ሞቱ" ሲሉ ነግረውኛል። አጤ ቴዎድሮስ የአገራቸው ፍቅር እያንገበገባቸው ባለበት ወቅት ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች አሊ ነሐሴ 13 ቀን 1850 ዓም ሞቱ። ከፍቅራቸው ብዛት የተነሣ አስከሬን ይዘው እስከ ጥቅምት 11 ቀን 1851 ዓም አልቀበሩአቸውም ነበር። ሬሳ ተሸክመው አገር ለአገር ሽፍታ ለማደን ይዞሩ ነበር። መቅበራቸው አልቀረምና ከቀበሩ በኋላ ይህን ሲሉ አንጎራጎሩ።

"ብዙ ሥራ አዋቂ ትናንት ተቀበረች፤
መድኃኒቱን ምሳ ታበላኝ ነበረች፤
እስኪ ጠይቁልኝ እርቃ ሳትሄድ፤
እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ወይ ገረድ" አሉ።

አጤ ቴዎድሮስ ተበሳጭተው ሲመጡ ቁጣቸውን አብርደው ለሚቀጥለው ቀን በሰላም ወደ ሥራቸው እንዲሄዱ ያደርጓቸው ነበር። መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት፤ የሚባለው ልክ እንደ እቴጌ ተዋበች ማለት ነው። ይህ አባባል ትክክለኛ መሆኑ አጤ ቴዎድሮስ ላይ የደረሰው ሁለት ዓይነት ጠባይን መመልከት ይቻላል። ምናልባት እቴጌ ተዋበች ኑረው ቢሆን ኑሮ አጤ ቴዎድሮስ ብዙ ጠቃሚ ተግባር ለኢትዮጵያ ይፈጽሙ ነበር። እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ የደጃዝማች ውቤ ኃይለ ማርያም ልጅ ናቸው።

እቴጌ ጥሩወርቅ፤ በእድሜ ልጅ ቢሆኑም አባታቸውን ከእስር ቤት ለመጠየቅ ወደ አጤ ቴዎድሮስ መጥተው ተዋወቁ። አጤ ቴዎድሮስ፤ እቴጌ ጥሩወርቅን፤ ሲመለከቱአቸው ደስ ስላሉአቸው በቤተ ክርሥቲያን ሥርዓት በሥጋ ወደሙ አገቡአቸው። ታዲያ እቴጌ ጥሩወርቅ አጤ ቴዎድሮስን አያከብሩአቸውም ነበር። ከውጭ ውለው ሲገቡ እንኳን እንደ እቴጌ ተዋበች የሚበላና የሚጠጣ ማቅረቡ ቀርቶ ቀና ብለው አይመለከቱአቸውም ነበር። እቴጌ ጥሩወርቅ ዳዊት ደጋሚ በመሆናቸው አጤ ቴዎድሮስ ውለው ሲገቡ ዳዊታቸውን አንሥተው መድገም ይጀምራሉ። በዚህ ሰዓት አጤ ቴዎድሮስ ይበሳጫሉ።

<u>መጽሐፈ ምሳሌ</u> ም/9 ቁ 13 "ሰነፍ ሴት ሁከተኛ ናት፤አሳብ የላትም አንዳችም አታውቅም" ይልና እንዲሁም ደግሞ 12 ቁ÷4 "አሳፋሪ ሴት ግን በአጥንቱ ውስጥ እንደ ቅንቅን ናት" ይልና ደግሞ 21 ቁ÷9 ከጠበኛ ሴት ጋር በአንድ ቤት ከመቀመጥ በውጭ በቤት ማዕዘን ላይ መቀመጥ ይሻላል" ይላል። ስለ እውነቱ ይህ ምዕራፍ ስለ እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ ብቻ ሳይሆን ዛሬ ድረስ በትዳር ላሉ ይህን መጽሐፍ ለሚያነቡ ሁሉ ራሳቸውን እንዲመረምሩ። ይህን ስል ወንዶች መጥፎዎች የለነም ለማለት ሳይሆን ባለቤታቸውን አክብረው የሚያስከብሩ ሴቶች ቁጥራቸው ትንሽ ይመስለኛል።



በጣም የሚገርመኝ ጉዳይ ቢኖር በዚህ በአሜሪካ አገር ብዙዎቻችን ትዳሩ አልሠምርልን የሚለው እንደ እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ ተጨቃጫቂ ሴቶች በዝተው ሊሆን ይችላል። ችሎታቸው ትዕግሥትና ምክር ከበዛበት ሌላው ቀርቶ ሴሰኛው ወንድ እንኳን ሳይቀር ሁሉን ነገር ጠብ እርግፍ አድርጎ በባለቤቱ ቁጥጥር ውስጥ ይገባል። ደግሞም እንደ ወንድ የዋህ ፍጡር የለም። ነገር ግን ጥንቁቅ ሴት ካልሆነች ሲገባ ሲወጣ ከጨቀጨቀችው ያልነበረውን ዓመል አውጥቶ ለእሱም ለቤተሰቡም ሰላም አይኖረውም።

ሻለቃ ግርማ ይልማ፤ <u>ሐዋርያ ጋዜጣ</u> ቅጽ 7 ቁ 11 ሰኔ 1994 ዓም ገጽ 17 "እቴጌ ተዋበች ከሞቱ በኋላ ሁለተኛው ጋብቻቸው የተዋጣለት አልነበረም" ሲሉ ጽፈዋል። እቴጌ ጥሩወቅር ውቤ በጣም አስቸጋሪ ሴት ነበሩ። አንዳንዴስ እንዲያውም ከካህናቱ ጋር ስለ ባለቤታቸው የሚያወጉ ነበሩ። በእርግጥ ማንኛውም ሰው ከሚቀርበው ጋር በቤቱም ሆነ በማንኛውም መወያየቱ ግልጥ ሲሆን እርሳቸው ግን አልፈው ተርፈው ከሰው ፊት እንኳን ሳይቀር ይገለፍጧቸው ነበር።

አጤ ቴዎድሮስ አንዴ ጎጃም ደጃዝማች ተድላ ጓሉን ለመያዝ ቀን ከሌት ሲለፉ ሰንብተው ይመጣሉ። በሌላ ግዜ ደግሞ ጎንደር ወልቃይት ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜን ለማደን ይሄዳሉ እንዲሁም ወሎ ደጃዝማች አሕመድ በሽርን ለማደን ይዘምታሉ ብሎም ትግራይ ደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤልን አባረው ለመድፋት ይሄዳሉ። እንግሊዞች በንቀት ስላዩአቸው ከውጭ አገር መንግሥት ጋር ጠብ ገጥመዋል። ባለቤታቸው እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ ከቤት ያሉ አንዷ የሆድ ሕመም ናቸው። በዚህ ወቅት አጤ ቴዎድሮስ ብሶታቸውን ለማን ይነግሩታል። ጭንቅ ብሎአቸው እንቅልፍ አጥተው አድረው ጥዋቱ ሥራ ሲገቡ ጭንቅላታቸው ሰላም ስለለላቸው ይጨክናሉ።

በውጭ ውላችሁ ርቧችሁ ምሳችሁን ለመብላት እየገሰገሳችሁ ስትመጡ ከቤት በታች ካለው አቀበት ስትደርሱ አቀበቱን በማየት ትደክማላችሁ። ምክንያቱም ረኃብ ውሎባችሁ ደረስን ብላችሁ ቤታችሁን በአሻጋሪ እየተመለከታችሁ አቀበት ሲያጋጥማችሁ ጉድ ነው። ይህ አባባል ውጭ አገር ያላችሁትን አይመለከትም። ምክንያቱም መኪና አለና ነው።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አባባል ከውጭ ውላችሁ ተርባችሁ ከቤት ለመድረስ እየሮጣችሁ ስትመጡ ከጓሮ ስትደርሱ ትዝ የሚላችሁ ጭቅጭቅ ከሆነ ራባችሁ ትቶአችሁ ይሄዳል:: አንጀታችሁ እጥፍ ብሎ ጭቅጭቅ ፈርታችሁ ጓሮ ለጓሮ ስትዞሩ ታመሻላችሁ:: እውን እንዳይሆን ሕልም ያድርግላችሁ:: ደግነቱ አሁን በምግብ ቤት በልቶ ለምኝታ ይመጣል:: ይህ ደግሞ ያለው በከተማው እንጂ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ወንዶች ይህን እድል አያገኙትም::

አጤ ቴዎድሮስ የገጠማቸው ይህ ዓይነት ችግር ነበር:: እርሳቸው በእቴጌ ተዋበች የለመዱት ከቤት ሲገቡ ቀን የዋሉበትን ጭቅጭቅ የሚረሱበት ደስታ እንጂ ሌላ ጭቅጭቅ የለባቸውም ነበር:: እቴጌ ጥሩወርቅ ግን ካልተጨቃጨቁ ምግብ የማያቀርቡ ነበሩ::

አጤ ቴዎድሮስ የጨከኑበት ምክንያት የሚወዱአቸው ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች ዓሊ ከሞቱ በኋላ እቴጌ ጥሩወርቅን ከአገቡ ወዲህ ነው:: እኒህ እቴጌ ጥሩወርቅ ጠባያቸው አስቸጋሪና አናዳጅ ሆኑባቸው:: እንኳን አሜሪካና አውሮፓ ኢትዮጵያ ያላችሁም ብትሆኑ ርእሰ ብሔር ክሊንተን ከወይዘሪት ሞኒካ ጋር መማገጣቸውን በተመለከተ በዓለም ጋዜጠኞችና ቀላጆች ተውኔት መጫወቻ ሁነው ነበር:: በዚህ ወቅት ወይዘሮ ሒላሪ ክሊንተን ስለ ባለቤታቸው ምንም ዓይነት ቅይምታ ሳያሳዩ ቀርተዋል:: በዚህ ምክንያት ርእሰ ብሔሩን የሚጠሉ ሰዎች ያሉ ቢሉም ከሥልጣናቸው ሳይወርዱ ቀናቸውን ጨርሰው ለቀዋል::

በዚህ ወቅት ባለቤታቸው ከሕዝብ መገናኛውና ከሪፓፐሊካኑ ጋር ቁመው ቢሆን ኑሮ ርእሰ ብሔሩ የቀራቸውን ዓመት አይጨርሱም ነበር:: ይህ ሁሉ የሚሆነው ወይዘሮ ሒለሪ ወይም (ፈርስት ሌዲ) አስተዋይ በመሆናቸው ነው:: አንባብያን ልብ በሉ በተለይ ትዳር ያላችሁ ሁሉ ከሥራ ውላችሁ ከቤት ስትገቡ በትዳራችሁ ውስጥ ያለው መልካም ገጽታ ከሆነ እናንተም ቀን ተበሳጭታችሁ ብትውሉ እንኳን ከቤት ስትገቡ የሚጠብቃችሁ ጉምጉምታ የዓይን ግልምጫ ከሆነ እንቅልፍ ሳትተኙ ታድሩና ጧዋት ሥራ ስትገቡ ምን ዓይነት ስሜት እንዳላችሁ በራሳችሁ ታዘቡ:: ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ የአበው ንግግር ልውሰዳችሁና "ከቤቱ በታች አቀበት ያለበት ሰውና ተጨቃጫቂ ሚስት ያለው ሰው አንድ ናቸው" ይላሉ::



# ምዕራፍ 2

## አጤ ቴዎድሮስ የጨከኑበት ምክንያት!

"ይሉኛል ይልኛል ጨካኝ
ሀሳቤን ሳያውቁ ምክሬን ሳይሰሙኝ"
ይሉ ነበር:: አጤ ቴዎድሮስ በገና ሲደረድሩ::

አጤ ቴዎድሮስ ከመጨከናቸው በፊት የምሕረት አዋጅ ያወጣሉ:: ከዚያም ምሕረት ማድረጋቸውን ያስነግራሉ:: የተናቀውንና የተጠላውን ሥራ ራሳቸው ከሕዝቡ ጋር ሁነው ይሠራሉ:: ዶማና መጥረቢያ ይዘው መንገድ ሲሠሩ ይውላሉ::

የወጣውን አዋጅ ቅድሚያ ራሳቸው ተግባራዊ ያደርጋሉ:: ከዚያም ወታደሩና የመንግሥት ሠራተኛው ተግባራዊ እንዲያደርግ ያዛሉ:: ለምሳሌ ቁባቶቻቸውን ትተው ከእቴጌ ተዋበች ጋር በሥጋ ወደሙ እንደተወሰኑት ዓይነት ማንኛውንም ራሳቸው ቅድሚያ ያደርጋሉ:: ሌላው ቀርቶ መንገድ ሥራ ሳይቀር እርሳቸው ተሰልፈው ሠርተዋል::

ኢትዮጵያና ዕድሏ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 120 "የብረታ ብረት ሥራ!የእጅ ሙያ ሁሉ በኢትዮጵያ ልምድ እንደነውር ይቆጠር ስለነበር ቴዎድሮስ ያንን መጥፎ ልምድ ሰብረው እራሳቸው እንደ አንድ ወዛደር ዶማና መዶሻ ይዘው ሙሉ ቀን ከሕዝቡ ጋር በመቆፈርና በመቀጥቀጥ የመጀመሪያውን ዘመናዊ መንገድ በኢትዮጵያ ያሠሩ እሳቸው ናቸው::"

"ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ የመንገድ ሥራ አልተለመደም ነበር በማለት አገር ጎብኚ የነበሩት አቶ ኤሚል ዮንቮ የተሰኙት ፈረንሳዊ ሲመሰክሩ የቴዎድሮስ እስረኛ የነበሩት ዶ/ር (አቶ) ሄንሪ ደግሞ ቴዎድሮስ ራሳቸው ከሕዝቡ ጋር ሆነው ጀንበር ወጥታ እስክትጠልቅ ድረስ ድንጋይ በመሸከም መሬት በመደልደል ይሠሩ ስለነበሩ ሕዝቡም ምግብና መጠጥ ሳያምረው ሙሉ ቀን ሲሠራ ይውል ነበር

ብለው ጽፈዋል" ሲሉ ኮሎኔል አስራት ቦጋለ ጽፈዋል:: ይህን ተግባር እርሳቸው ሲፈጽሙ መሳፍንትና ካህናት ሕዝቡን አስተባብረው ተግባራቸውን ሲያጥላሉት አጤ ቴዎድሮስ ተበሳጩ::

አንባብያን እንድትረዱልኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር አጤ ቴዎድሮስን ከወቀሳ ለማዳን ብዬ አይደለም ይህን እያልኩኝ የምጽፈው:: ደግሞም አንድን ሰው የምንተቸው በወቅቱና በዘመኑ ሥርዓት ተመሥርተን መሆን ይኖርበታል:: ይህ ከሆነ አጤ ቴዎድሮስ ያን ያህል ያንገበገባቸው ምክንያት አገራቸው ኢትዮጵያ ከነበራት ታላቅነት ወርዳ በማየታቸው ምክንያት አስቆጭቷቸው ነው::

ደግሞም የእርሳቸውን ቁጭትና ብስጭት ከተወሰኑ ባልንጀሮቻቸው በቀር የተረዳላቸው ባለማግኘታቸው ተሰምቷቸዋል:: አጤ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን ታሪክ በማወቃቸው ምክንያት የአገሪቱን አንድነት ለመታደግ ጥረት ሲያደርጉ የቀረቧቸው የተወሰኑ ናቸው::

1ኛ የቤተ ክህነቱ ሰዎች ከአፍራሽ ጋር አብረው በመቆማቸው::
2ኛ ያወጡትን ሕግ በሥራ ላይ ለማዋል ሲሉ::
3ኛ መኳንንቶች የእርሳቸውን ዓላማ ባለመቀበላቸው::
4ኛ የውጭ ኃይሎች ኢትዮጵያን በመናቃቸው::
5ኛ ከአገራቸው ውስጥ የሚሠራ የጦር መሣሪያ ባለመኖሩ::
6ኛ የአገራቸውን ታሪክ እርሳቸው ብቻ አውቀው በመገኘታቸው::
7ኛ መካሪና ረዳት ባለቤታቸው ስለሞቱባቸው::
8ኛ ወታደሩ እየከዳ በማስቸገሩ
9ኛ ዓላማቸው በመጨናገፉ::
10ኛ እርሶ አደሩ በወሬኛ የቤተ ክህነት ሰዎች ሴራ በመስማማቱ፤
11ኛ 2ኛ ባለቤታቸው ሰላም ስለነሷቸው::
12ኛ መሳፍንቶች አገር እየሸጡባቸው፡ ሌላም ሌላ...ችግሮች ነበሩ::

አጤ ቴዎድሮስ አገር ለማበልጸግ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ዓላማን ከግቡ ለማድረስ ታጥቀዉ ሲነሡ የተባበራቸው በጣም ትንሽ ሰው ነር ማለት ይቻላል:: በወታደር በኩል ፊታውራሪ ገብርዬና በሃይማኖት አባቶች በኩል መምህር አካለ ወልድና ሸህ ሁሴን ጅብሪል ሌሎችም ተባባሪ ቢሆኑም ይህ የበስማም ቄስ ተብትቦ ተብትቦ ከመኳንንቱ ጋር አብሮ ተባብሮ ተነሣባቸው::



በዚህም ምክንያት የተጀመረው የልማትና የብልጽግና ጅመራ ጨንግፎ ቀረ:: ለአጤ ቴዎድሮስ ጭካኔ መሠረቱ የመሳፍንቱና የካህናቱ አድመኝነት በዋናነት የሚጠቀስ ጉዳይ ነው:: አጤ ቴዎድሮስ አስቀድመው ከመንገሣቸው በፊት ሆነ ከነገሡ በኋላ "ተወኝ ሽፍታ? ተወኝ ቀማኛ? ግባ"እያሉ አውጀው ነበር:: ነገር ግን ሰሚ አልነበራቸውም እንኳን የወጣውን አዋጅ ሊያከብሩ ቀርቶ እንዲያውም ውንብድናው ባሰባቸው::

<u>ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሊትማን ያሳተመው ገጽ 26 "የንጉሡን መምጣት በሰማ ጊዜ አገው ተዋግቶ ዋግሹም ገብረ መድኅንን ቢትወደድ ብሩን አባ ጫጎን ከነባርያቸው ያዙዋቸው:: ንጉሡ ገና ሳይደርሱ ብዙ ሰው ተያዘ ንጉሥ ቴዎድሮስ ስንቱን መኳንንት አሰረው ስለ መድኃኔዓለም ብለው ማሩት" ሲሉ ጽፈዋል::

**Reidulfk.Molvaer <u>Black Lions</u> page 151 modern spirit of nationalism was created by Tewodros,**አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ዘመናዊ ለማድረግ ታጥቀው የተነሡ ነበሩ:: ታዲያ ምን ያደርጋል ተባባሪ በማጣታቸው ሳይሳካ ሲቀር ብስጭቱና የአገር ፍቅሩ ብቻቸውን ሲያቃጥላቸው ያድርና ጥዋት የከዳቸውን ሲያገኙት ጨከኑበት::

ሌላው ቀርቶ በሃይማኖት ሳይቀር ቀይረዋል እያሉ መነኩሳቱ ያሟቸው ጀመር:: አምቶም አልቀረም ከፊታቸው ቀርበው ሃይማኖታቸውን መቀየራቸውን ደፍረው ነገሯቸው:: ታዲያ አጤ ቴዎድሮስን ያህል ሃይማኖቱን የሚያከብር "ሃይማኖትህን ቀይርሃል" ተብሎ ሲነገረው እንዴት አይበሳጭና አይጨክን::

አለቃ ወልደ ማርያም <u>የቴዎድሮስ</u> መጣጥፍ ገጽ 48 "አባ ገብረ ሚካኤል የትግሬ ሰው ከካህናቱ ጋራ ነበሩና ጃንሆይ በእስክንድርያ ሃይማኖት ይጽኑልን አሉ:: ንጉሡም ከእስክንድርያ ሌላ የማነን ይገፍአለሁ ቢሉ የፈረንጅ ሃይማኖት ይዘዋል ይሉናል አሉዎ" ይሉና ገጽ 50 "ከዚህ በኋላ ካህናቱ ሲፈርዱ ንጉሥን ያማ ይቀጣ ባሉ ጊዜ አባ ገብረ ሚካኤል የፈረንጅን ሃይማኖት ይዘዋል ብለው ተናግረዋልና ከንጉሡ ግረፈው የሚል ቃል ሲወጣ ዙሪያውን ቆሞ የነበረው ወታደር የአንገት ማተብ ሳይቀር ተገፈው ራስ ቢሠውርን የመቅደላ ጠባቂ ነበሩና አስጠርተው ይህን መነኩሴ አስረህ አኑረው

ራብ ይግደለው ሲሉ ተቀብለው አስረው መቅደላ ገቡ በማግሥቱ ዓርብ አምጡ ብለው መነኩሴውን ፈትተው ሰደዱ" ሲሉ ጽፈዋል:: የዚህ ዓይነት አሚኪላ ሞለቶባቸው ነው የጨከኑት::

<u>ኢትዮጵያ ሰድሷ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 121 "ጥረታቸው ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ያልሆነበርን ምክንያት አንድ አቶ ቴዎፍሎስ ዋልድ ማዩር የተሰኘ የሱዊስ ተወላጅ ሚሲዮናዊ ባቀረቡት ገለጻ ÷ ቴዎድሮስ እንደገለጹት ይሉና የሥራ ጓደኞቻቸው ያልሰለጠኑ ያልተማሩ ደደቦች እንደ አህያ የታወሩ ስለሆኑ ችሎታ ያላቸው የውጭ አገር የእደጥበብ ባለሙያዎች እንዲላኩላቸው ለአውሮፓ መንግሥታት ጥያቄ አቅርበው ነበር ብለዋል÷ ጥያቄያቸው መልስ ባለማግኘቱ ተቆጥተው በውጭ አገር ዜጎች ላይ የወሰዱት እርምጃ የውጭ ፖለቲካቸውን አበላሸባቸው::"

"እሳቸውም ፈረንጆቹን እንዲጠሉ ካደረጋቸው ነገር አንዱ አቶ እስተርን የተባለ እንግሊዛዊ ሚሲዮናዊ በአውሮፓ አቆጣጠር በ1862 ዓም ሎንደን ባሳተመው መጽሐፍ ቴዎድሮስን በማናናቅ የቴዎድሮስ እናት መንገድ ላይ ተቀምጣ ኮሶ ትሸጥ ስለነበር የቴዎድሮስን ስሙ ልጅ ኮሶ ነበረ:: ልጅ ኮሶ ማለትም ትል የሚያጠፋ መድኀኒት ማለት ነው ብሎ ከጻፈ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ በመግባቱ አቶ እስተርን ተይዞ ከተገረፈ በኋላ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ነበር" ሲሉ ጽፈዋል::

## ምዕራፍ 3

## አጤ ቴዎድሮስ ሕግ በጣሱት ላይ ጨክነዋል!

<u>ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሊትማን ባሳተመው ገጽ 26 "በግንቦት ገረገራ ላይ ዋግሹም ገብረመድኅን ቢትወደድ ብሩ አባጫን ተጎጃም ተያዙ:: ደግሞ እሰኔ ደረስን ጎለም ወልደሚካኤልን ማሩ ሰሎሞንን ደግሞ 4 ሰዎች እነዚህን ዘጠኝ ረጅም ግራር ከሚባለው ሰቀሉአዋቸው እጅ እግራቸውን ቆርጠው በፍትሐ ነገሥት በፍርድ ዋግሹም ገብረመድኅን ንጉሡ ከራስ አሊ በተዋጉ ጊዜ ቆስለው ነበር:: ከራስ ጋር ሁነው ሳሉ ንጉሥም እይዞዎ ብለው መቶ ነፍጥ ሰጥተው አገራቸውን አገውን ሹመው ሰደዋቸው ከሸዋ በተመለሱ ጊዜ ነው



አገራቸውን የሰደዱአቸው ከዚያ ከዱ:: እግዚአብሔርም ክዳታቸውን አይቶ ከንጉሡ እጅ ጣላቸው ከረጅም ግራር ሰቀሉአቸው" ሲሉ ጽፈዋል::

ደጃዝማች ዋግሹም ገብረ መድኅን ማለት የአጤ ተክለ ጊዮርጊስ አባት ናቸው:: ቅድሚያ ከራስ አሊ ጋር ሁነው አጤ ቴዎድሮስን ወግተው ቆስለው ተማርከው ነበር:: ከዚያም ግዛታቸው ተፈቅዶላቸው ተሸልመው ከተመለሱ በኋላ ሸፈቱና ሲማረኩ ተገደሉ:: ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መጽሐፍ በተለያዩ ገጾች ላይ ገና ደጃዝማች ሳሉ ጀምሮ ቃል ያፈረሰውንና የወጣውን አዋጅ የጣሰውን መግደላቸውን እየደጋገሙ ጽፈዋል::

<u>ስማቸው ያልታወቀ የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት</u> ደራሲ በ55 ገጽ መጣጥፋቸው ውስጥ ገጽ 14-15-25-ማወጃቸውን ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ ቅድሚያ አዋጅ ማወጃቸውንና እርሳቸው ቃል ለመጠበቅ ሲሞክሩ ሕዝቡ ሊሰማ ቀርቶ እንዲያውም ለሌብነት ተደራጅቶ መጣ:: አጤ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ አንድነት ምልክት የሆነውን ዘውድ ጭነው አንዲት ኢትዮጵያ አንድ አመራር ብለው ገበሬ በግብርናው ነጋዴም በንግዱ÷ሁሉም እንደ ችሎታው በየሞያው ተሰማርቶ በሰላም ይኑር ብለው አወጁ:: በዘመነ መሳፍንት ሥር የሰደደው ሌብነት ሞያ ሆኗልና እንዲያውም ሌቦች ተሰባስበው መጥተው ጃንሆይ ሁሉም በየሞያው ሠርቶ ይኑር ካሉ የኛ ሞያ ሌብነት ነውና ይፍቀዱልን ብለው አመለከቱ::

አጤ ቴዎድሮስ በኋላ የሚያደርጉትን እናንተማ ለግል አሽከርነት የምትጠቅሙኝ ናችሁ እናንተ ብቻ አትበቁም ሂዱና እንደናንተ የመሰሉትን ሰብስባችሁ ተመልሳችሁ ኑ:: ግን በሌብነት ሞያ ያላስመሰከረ ከሆነ ይዛችሁ እንዳትመጡ ብለው መለሷቸው:: ሌቦቹ መሰሎቻቸውን ሰብስበው ወደ አጤ ቴዎድሮስ ቀርበው ይኸው መጥተናል ሜዳውን ሞልተውታል ብለው አመለከቱ:: አጤ ቴዎድሮስም በል ፍጀልኝ ብለው አስፈጇቸው:: አቶ ገሪማ ታፈረ ጥፋቱ የሕዝብ ነው ብለዋል::

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 169 "በአጤ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የተፈጸመው የወንጀለኞች ቅጣት ሲመዛዘን ጥፋቱ የሕዝቡ እንደነበር የአፈጻጸሙ ዝርዝር ሁኔታ

ያስረዳል። በታሪኩ አቀራረብ እንደተገለጸው እገሌ የአካል ቅጣት ተፈጸመበት ወይም ታሠረ፣ተገረፈ ሲባል ከኃጢአት ንጹሕ ነበርኩ ወይም ጥፋት ሳይገኝብኝ ነው የተቀጣሁ ከኃጢአት ንጹሕ ነኝ ሲል እንደ ጲላጦስ እጁን የታጠበ አይታይበትም ብቻ የተቀጡት አማፅያን ጥፋታቸውን አምነው ምሕረት ጠያቂዎች ሁነው ተገኝተዋል። እንግዲህ ከዚህ ላይ ጥፋቱ የሕዝቡ እንደነበር ማመዛዘንና መመራመር የሕሊና ዳኝነት አስፈልጎታል" ይሉና።

170 "አጤ ቴዎድሮስ ከእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ዜጋ ላይ የሚፈልጉት ገጸ በረከት ታማኝነትንና ተገዥነትን ብቻ እንጅ በሌላው በኩል መብቱ ተጠብቆለት ሀብቱ ተጠብቆ የኑሮ ደረጃውን በሥራ ኃይል እያጠነከረ ወደ አዲስ ሕይወት እንዲመራላቸው በበለጠ ይመኙለት እንደነበር የተጀመረው የሥራ ውጥንና ንድፍ ምስክርነቱን አሳይቷል" ሲሉ ጽፈዋል። ከዚህ ከፍ ብሎ የተነበበው ጥቅስ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር አጤ ቴዎድሮስ የገደሉት በፍርድ ነው እያሉ ነው። የእኔ እምነት ሕዝቡ ለብዙ ዘመናት ሕግ አልባ የሽፍቶች ኃይል በዝቶ በመኖሩ የእርሳቸውን ሕግ ሊያከብርላቸው ባለመቻሉና ሌላው ደግሞ የካህናቱ ቀስቃሽነት በሕዝቡ መሀል ገብቶ አጣልቷቸዋል።

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 243 "ነገር ግን አጤ ቴዎድሮስ ዘመነ መሳፍንትን በማስወገድ የባርያ አገዛዝን ሲሽሩ፣የካህናትን ቁጥር ሲወስኑ መሬት የመንግሥት ነው ብለው በዚያ ባለጉልተኛ በሰፈነበት ዘመን ማወጃቸው የሚያስመሰግን ሲሆን ከአካባቢው የተነሣባቸው ተቃውሞ በጎ ሐሣባቸውን ከፍጻሜ ለማድረስ አላስቻላቸውም። ስለዚህ ሐሣባቸውን አልቀበልም ባለው ወገን ላይ ቁርጠኛ እርምጃ ለመውሰድ አስገድዷቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል።

ይህ ሰውን እንደከብት ይሸጥ የነበረ ምድረ መኳንንትና ካህናት ጥቅማቸው በመነካቱ ምክንያት በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ተነሡ። እርሳቸውም ተደጋግሞ እንደተገለጸው ያወጡትን አዋጅ ለመተግበር ስለፈለጉ ሕጉን የጣሱትን ፍትሐ ነገሥት እየተነበበ በጥፋታቸው ቅጣታቸውን ተቀብለዋል።



አታኽልቲ ሐጎስ <u>ሐቅ ሐቁን ለሕፃናት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 115 "ስለ አጤ ቴዎድሮስ ጭካኔ የሚቀርቡት መላምቶች በሙሉ መሠረት የሌላቸው ምክንያቶች ናቸው። ይህ ሁሉ መላምት መምጣትና እንደ ምክንያት መመርመር የሚችለው አጤ ቴዎድሮስ ከመጀመሪያው አነሣሣቸው በርኅራኄአቸው የሚታወቁ ቢሆኑ እንደ ምክንያት ሊቀርብ ይችል ነበር። ጭካኔ የጀመሩት የሆነ የሚያስጨክን ገጥሞአቸው ከዛ በሁዋላ የተዳበላቸው ሳይሆን አንድ ብለው ሽፍትነት ሲጀምሩ ጨካኝነታቸው ጎልቶ ይታይ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

አዎ ልክ ነው አጤ ቴዎድሮስ ጨክነዋል ብዙ ሰው ገድለዋል። እጅ እግሩን ቆርጠዋል! ብዙም ሰው ቤት ውስጥ ዘግተው በእሳት አቃጥለዋል። እኔ አጤ ቴዎድሮስ መጨከናቸውን ደብቄ አላውቅም። ነገር ግን ብዙ ኢትዮጵያውያን አጤ ቴዎድሮስ ጨካኝ ናቸው ይላሉ እንጂ የጨከኑበትን ምክንያት ዘርዝረው አያቀርቡም።

አጤ ቴዎድሮስ ለምን ሰውን እጅና እግሩን ቆረጡ? ለምን ቤት ዘግተው በእሳት አቃጠሉ?ለምን ጨከኑ ብሎ የሚጠይቅ የለም ማለት ይቻላል። ብዙ ሰዎች ሲጽፉ እያለሁ መልካም ተግባራቸውን ሳይገልጡ የሚያተኩሩ ከተገደሉት ላይ ነው።

አንዳንድ ግለሰቦች አንድን መንግሥት ሲጠሉት የሠራውን ሁሉ ይክዳሉ። ይህ ሊሆን አይችልም በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሥልጣን የነበራቸው ግለሰብ ከ200 ገጽ በላይ ክፉታቸውን ሲዘረዝሩ መልካም ሥራቸው 2 ገጽ ብቻ ሁኖ ሳነበው ገረመኝ። ይህን ታሪክ ለመለወጥ የታሪክ ትክክለኝነትን የሚመረምር አብዮት መነሣት ያለበት ይመስለኛል። የአንድን ግለሰብ ታሪክ በታሪክነቱ መልካም ተግባሩ በመልካምነቱ መጥፎው ተግባሩ በመጥፎውነቱ እውነቱን ይዞ ከተቀመጠ ጥሩ ይሆናል። የአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ በ2 ተከፍሎ ይጻፋል።

1ኛ መልካም ተግባራቸውን ደብቆ መጥፎ ተግባራቸውን አብዝቶ የሚጽፈው ኃይል አጤ ቴዎድሮስ በሕይወት ሳሉ ጀምሮ ያለ ሲሆን ዛሬ ያነን በመያዝ ትውልዱን ለማሳሳት ጥረት እየተደረገ ነው።

2ኛው ትክክለኛውን ታሪክ የሚገመግሙ መጥፎ ተግባራቸውን መጥፎ ብሎ መልካም ተግባራቸውን መልካም ብሎ እውነቱን መጻፍ ነው:: በእኔ እምነት አጤ ቴዎድሮስ ለአገር አንድነት ሲሉ ጨክነዋል አዎ ሰው ገድለዋል! ነገር ግን የተገደሉት ሰዎች በምን ምክንያት ነው:: እኔ ካነበብኳቸው የተለያዩ መጽሐፍትና መጣጥፍ በአፍም ከሚነገረው ታሪክ በመነሣት አጤ ቴዎድሮስ ከበርሃ ዘመን ጀምረው የሚከዷቸውን ሲገድሉና እጅ እግሩን ሲቆርጡ መቆየታቸው አይዘነጋም::

ይህን ማድረጋቸው ትክክል ናቸው ለማለት ሳይሆን ከላይ የተዘረዘሩትን አገር ለመገንባት ያወጡትን እቅድ ከውጭ ኃይሎች ጋር አገር ውስጥ ከነበሩ መኳንንት መሳፍንት ሽፍቶች ጋር ተመሣጥረው የወጉአቸውን ምሕረት አድርገውላቸው ከተለቀቁ በኋላ 2ኛ ሲያዙ ተገለዋል:: ለምሳሌ በጎጃም ደጃዝማች ተድላ ጓሉን ሲያሳድዱ ሳለ የተማረኩት ምሕረት ተደርጎላቸው ተለቀው ነበር ነገር ግን በሌላ ጊዜ ሲያዙ ራሳቸው ሞት ይገባናል ብለው በመናገራቸው ተገደሉ::

ደብተራ ዘነብ <u>የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሊትማን ያሳተመው ገጽ 25"ወደ ተልባ ውሃ ባቀኑ ጊዜ ተባራሪው ሽፍታ ሲዋጋ ተያዘ::ቀድሞ ከማሩዋቸው 20 የሚሆኑ ተያዙ:: ምሬያችሁ ወጋችሁኝ (በኋላቸው) ባሏቸው ጊዜ ሞት ይገባናል ብለው ፈረዱ:: አስደበደቡዋቸው ሞቱ" ሲሉ ጽፈዋል:: በዚህ ወቅት የዐይን ምስክሩ ያዩትን ጽፈዋል:: እንዲሁም በወሎ አንዴ ከደጃዝማች በሽር ጋር ሁነው የወጓቸውን ማረኩና ምሕረት አድርገው ለቀቋቸው:: በሌላው ቀን እነዚያ ምሕረት የተደረገላቸው በመያዛቸው እጅ እግራቸውን ተቆረጡ::

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 173-174 " አንኮበር ላይ (ጎረቤላ) ከአፋፉ ሆነው ለዚህ ንጉሥ ለቴዎድሮስ ዕንጨት የሰበረ ውሃ የቀዳ ሣር ያጨደ የተከተለውም ውጉዝ ይሁን:: ይህ ቃል የአቡነ ሰላማና የዕጨጌ ወልደ ማርያም ነው እያሉ ገዘቱ:: በዚህ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ብዙ ሠንጋ ታርዶ ግብር ሊበላ ሲል ግማሹ ወደ ግብር ተጠርቶ የቀረው ቀለብ እንዲያመጣ ወደ ሐራምቦ ሂድ የተባለ ጊዜ እግዞኦ!እግዚኦ! እያለ በመጮህ እምቢታውን ሲያሰማ ቴዎድሮስ ወደ ጫፍ ወርደው ጠበንጃና ጦራቸውን እንደያዙ ከፈረሳቸው ላይ ወጥተው::"



"የኔ የሆንክ ብለው ታማኙንና ታዛገቡን ከለዩ በኋላ በቁጣና በብስጭት ከሠራዊታቸው ውስጥ በጠበንጃ ሰደፍ የመቱት ጦር ወርውረው ጠበንጃ ተኩሰው የሳቱት እንዳለና በዚህም የትርምስ ጊዜ ግማሹ ሲመታ የቀረውም ሲሸሽ በመካከሉ አቡነ ሰላማና ዕጨጌ ወልደ ማርያም እንደ ገላገሉ ከዚያም ንጉሡ እንደ ተበሳጩ ወደ ቶራ መስክ መውጣታቸውን ያመለክታል::"

"እነዚህን በጳጳሱና በዕጨጌው ስም ሲገዝቱ የነበሩት ወይም በዚህ የግዝት ዐድማ የተገኙት ንጉሡ ቶራ መስክ ከወጡ በኋላ በሰላይ ተይዘው ቀርበው በአደባባይ የተፈረደባቸውን ዐርባ ስምንቱን ሰዎች በጥይትና በጎራዴ እያስመቱ አስገደሉአቸው" ሲሉ ጽፈዋል:: በአቡነ ሰላማ እና በዕጨጌው ስም ውግዘት ያደረጉት ካህናት ወታደር መስለው ከተቀላቀሉ በኋላ ነው:: በዚህ ምክንያት ውግዘቱን የፈራው ሕዝብ እነሱን ተከትሎ በመንቀሳቀሱ 48 ሰዎች ተገለዋል:: በዚህ ጊዜ:: "አጤ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ
የሸዋን መኳንንት እጅ ነሥተው ሔዱ"

በማለት ተገጥሟል:: ዛሬ ድረስ በተለይም በአንዳንድ አካባቢ ይህ ግጥም ተደጋግሞ ሲገጠም ይሰማል:: አጤ ቴዎድሮስ ያወጡትን ሕግ ባልጠበቁት ላይ መጨከናቸው አይዘነጋም:: አጤ ቴዎድሮስ ብዙ ሰው ገድለዋል:: ብዙም ሰው ቤት ዘግተው በሣት አቃጥለዋል:: ብዙም ሰው እጅና እግር እየተቆረጠ ተጥሏል::

በዚህ ምንም ጥያቄ የለውም:: የምለው አጤው ለምን ገደሉ? ሲባል ቅድሚያ የምሕረት አዋጅ ካወጁ በኋላ ሲሆን ሌላው ደግሞ ከጦርነት መካከል ተማርከው የተለቀቁ ሁለተኛ ሲያዙ የተገደሉ መሆናቸው በብዛት የተመዘገበ ሲሆን ጎንደርን ከደብተራው ጋር ተጣልተው ሕዝቡ በማስቸገሩ ከተማውን ማቃጠላቸውና የጎንደርን ቤተ ክርስቲያን ደወል ሰብስበው መድፍ ሊያሠሩበት መውሰዳቸው አይዘነጋም::
የአጤ ቴዎድሮስን መግደል ትክክል መሆኑን አቶ ገሪማ ታፈረ በሕግ የሆነ መሆኑን ቅጣቱ በአግባብ የተፈጸመ ነው:: በሚል የጻፉትን ጥቅስ ከምወስድ እንዳለ ሙሉውን በአባሪነት ባስቀምጠው መልካም ይሆናል:: ገሪማ ታፈረ አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ ገጽ 168-171 <u>አባሪ ቁጥር 2 ይመልከቱ::</u>

# ምዕራፍ 4

## የአጤ ቴዎድሮስ የማይዛባ ፍርድ

<u>ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሊትማን ያሳተመው ገጽ 25 "በየካቲት ከጋይንት ተሡሪ አግብተው ሳለ ወታደር ባላገሩን ገደለው የሞተበት ሰው ከንጉሡ መጥቶ ጮኸ፡፡ ንጉሥ ቴዎድሮስ ወታደሩን ሁሳ አፍርሳታ አውጣ አሉት፡፡ ወታደርም አልገደልነም አላየነም ብሎ በተገዘተ ጊዜ ለንጉሥ ቴዎድሮስ ይህ ነገር ጭንቅ ሆነ፡፡ አሰበውም ኋላ እንዲህ አሉ፤ ወታደር ብላ ባላገር፤ያልሁ እኔ ነኝና ደመኛህ እኔን ግደል ባሉት ጊዜ ባለደሙም እኔ ንጉሥ መግደል አልችልም አለ፡፡ ንጉሡም ብዙ ብር ሰጥተው ሰደዱት" ሲሉ ጽፈዋል፡፡

<u>የኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 26 "የድሃ ገበሬዎችን አቤቱታ እራሳቸው ይሰማሉ፥ጉቦ መቀበልና መስጠት ከልክለዋል" ይሉና" ቋንቋቸው ግልጽ፥ ማመናታት የሚባል ነገር የማያውቁ አማካሪና አማላጅ የማይቀበሉ" ናቸው ሲሉ ቆንስል ፕላውዲን ለአገራቸው መንግሥት ጽፈው ነበር፡፡ አጤ ቴዎድሮስ ትክክለኛ ፍርድ ፈርደው ነበር ብዬ ከመጻፌ በፊት ብዙ የኢትዮጵያ ነገሥታት አስደናቂ ፍርድ ፈርደው ነበር፡፡ ከዚያ በፊት ግን አስቸጋሪ ፍርድ አጋጥሞት በብልሃት የተወጣው የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን ነበር፡፡ ያም አንዷ ይህ ልጅ የኔ ነው ብላ ከሰሰች፡፡ ወላጅ እናቱም ልጁ የኔ ነው ብላ ትቀርባለች ንጉሥ ሰሎሞን ይቸገራል፡፡

በዚህ ወቅት ሰሎሞን ልፈርድ ነኝ ሲል ከሳሽና ተከሳሽ ፍረድ አሉት፡፡ ንጉሥ ሰሎሞን "ልጁ ይገደልና ለሁለት ይከፈል" አለ፡፡ ወላጅ እናቱ "አልፈልግም ልጁን ትውሰደው አለች፡፡ ልጇ ያልሆነው ሴት ደግሞ ይከፈልና ድርሻዬን ልውሰድ አለች፡፡ በዚህ ወቅት ንጉሥ ሰሎሞን ልጁን ትውሰደው ያለችው ትክክለኛ እናት መሆንዋን በመረዳት ለእርሷ ይሰጥ በማለት ፈረደላት፡፡ እንደዚህ አይነት ብዛት ያላቸው ፍርዶች በኢትዮጵያውያን ነገሥታት ዘንድ ተፈርደዋል፡፡



በአጤ ፋሲል ዘመን ክርስቲያንና እስላም ተካሰው ከመጡ ፍርዱን የሚያዩ ራሳቸው አጤው ብቻ ነበሩ፡፡ በዚህ ወቅት እስላም ነጋዴ ክርስቲያን ቀጥሮ ሲያስነግድ ክርስቲያኑ በአላፊነት የተሰጠውን ንብረት ተዘረፍኩ ብሎ ይደብቀዋል፡፡ እስላሙ ንብረቱ እንዳልተዘረፈ ስላወቀ በሕግ ለመጠየቅ ይነሣል፡፡ አጤው ሁኔታውን ካዳመጡ በኋላ ከሳሽና ተከሳሽ እርሳቸው በሚያዘጋጁላቸው ቤት እንዲያድሩ ወሰኑና ጧዋት ፍርዱን እንደሚፈርዱ ተናግረው ችሎቱን ዘጉ፡፡ ከሳሽና ተከሳሽ በተዘጋጀላቸው ቤት ገብተው እንዲያድሩ ዘበኞች ይነገራቸዋል፡፡

ሁለቱም ምኝታ ከመግባታቸው በፊት ሰላዮች ገብተው የሚሉትን እንዲያዳምጡ ድምፃቸው እንዳይሰማ ተነገራቸው፡፡ ከሳሹ "አላህ ለፍቼ ያመጣሁት ንብረት በመሆኑ ያለአግባብ እንዳይወሰድብኝ ንጉሠ ነገሥቱ እንዲፈርዱልኝ እርዳኝ" እያለ ይጸልያል፡፡ ተከሳሹ ደግሞ "ሌባ ረዳቱ ጊዮርጊስ ንጉሠ ነገሥቱ ለእኔ ከፈረዱ ግማሹ የአንተ ነው" እያለ ይጸልያል፡፡ ጧዋት አጤ ፋሲል ችሎት ሲቀመጡ ከሳሽና ተከሳሽ ግራና ቀኝ ቆሙ፡፡ ምስክር የሆኑት ሁለቱ ሰላዮች በያደሩበት የሰሙትን ለአጤው ተናገሩ ፍርዱም ለባለንብረቱ ለእስላሙ ተሰጥቶ ክርስቲያኑ ወኅኒ ቤት ወረደ፡፡

ንጉሠ ነገሥት አጤ ዮሐንስ የከፋው ሰው አቤት የሚልበት ከአደባባዩ ደወል ይተክላሉ፡፡ ከዚህ አደባባይ የከፋው ሰው ሁሉ ያለ ገደብ ያን ደወል ደውሎ ችግሩን ለአጤው ያስረዳ ነበር፡፡ የበዓል ቀን ቢሆንም ደወሉ ከተደወለ ችግረኛውን ለማዳመጥ ጊዜ ይሰጣሉ፡፡ ታዲያ የአንድ ነጋዴ አህያ ወገቡ የተገጠበ፣ ኑሮ በአካባቢው ካለው አጧራ ሲንከባለል ቆይቶ ያንን ደወል የተሰቀለበትን ሰንሰለት ሲነካው ደወሉ ይጮኻል፡፡ ንጉሠ ነገሥት አጤ ዮሐንስ ዘበኞች ሲልኩ ሰው የለም፡፡ አጤው ለምን ደወሉ ጮኸ? ብለው ሲጠይቁ ዘበኞች ሰው ሳይሆን ያለው አህያ ነው ሲሉ መለሱላቸው፡፡

አጤው አህያውም ፍጡር ነው አምጡት ሲሉ አዘዙ፡፡ አህያው መጥቶ ሲመለከቱት ወገቡ ገጣባ ነው፡፡ ባለቤቱን ጠርተው ይህ አህያ እስኪድን ድረስ ሌላ አህያ ወስደህ ሥራ ይህ አህያ ሲድን ትወስዳለህ ብለው ለውጥ ሰጥተው አህያው ተቀልቦ ሲድን ወደ ባለቤቱ ተመልሶአል፡፡ በዚህና በሌላውም ተግባራቸው "ጻድቁ ዮሐንስ"ይባላሉ፡፡

በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት እንዲሁ የትግራይ ተወላጅ ራስ ወልደ ሥላሴ ልጃቸው የአንድ የድሃ ልጅ ገድሎአል:: ዳኞች የትልቅ ሰው ልጅ ሊፈርዱበት ስላልፈለጉ ከሳሽቱን "ጥፋተኛው ልጅሽ ነው" አሏት:: ስለዚህ የሟች እናት ጥዋት ጥዋት ራስ ወልደ ሥላሴ ከቤተ ክርስቲያን አርፍደው ወደ ቤት ሲገቡ ስታለቅስ ይመለከታሉ:: አንድ ቀን ለምን እንደምታለቅስ ጠርተው ሲጠይቋት ልጃቸው የእርሷን ልጅ የገደለው መሆኑን ተናገረች:: ራስም በፍርድ መታየት አለበት ሲሉ ዳኞች የሞተው ልጅሽ ነው ጥፋተኛ ብለውኛል ብላ ተናገረች:: ራስ የፈረዱትን ዳኞች ጠርተው ሲጠይቁ ነገሩአቸው::

ራስ የሟችን እናት የአንች ልጅ አንዴ ሙቶአል የእኔ ልጅ ቢሞት ልጅሽ አይመለስም ስለዚህ ገንዘብ ልስጥሽና እንታረቅ ሲሏት የልጄን ደም አልበላም አለቻቸው:: ከዚያም በቤተ ክርስቲያን አባቶች ቢያስጠይቋት አሻፈረኝ አለች:: ራስ ወደ ቤታቸው ጠሯትና ልጃቸውንም እርሷንም ጥሩ ምግብ አብልተው ሲያበቁ በእግራችን እንሀድ ብለው ወደ ተራራ ተጓዙ:: እልም ካለው ገደል ሲደርሱ ልጃቸውን ሳሙትና ወደ ገደል ገፍተው ጣሉት ሴቲቱንም ሂጂ ልጅሽን ታገኚዋለሽ አሉአት:: የፍርድ ጉዳይ ሲነሣ ፍርድ እንዳይጓደል ሲሉ ራስ ወልደ ሥላሴ ልጃቸውን ገደል ሰደዋል::

ለምሳሌ በኢትዮጵያ ታሪክ ሰው የገደለ ሰው እስኪፈረድበት ጊዜ ድረስ የሟች ወንድም ከገዳዩ ጋር ተቆራኝቶ ይታሰር ነበር:: አንዳንዴ የሟች ወንድም ከወንድሙ ገዳይ ጋር ተቆራኝቶ ባለበት ወቅት በበሽታ ይሁን በሌላ ምክንያት ሲሞት ሌላው ወንድም ተተክቶ ይቆራኝ ነበር:: ይህ "ሕግ ተቀይሮ ገዳዩን መንግሥት ይጠብቅ የሟች ቤተሰቦች በፍርድ ቤት ቀጠሮ ቀን መምጣትና ፍርዱን መከታተል ይገባቸዋል" ብለው:: "አጤ" ልጅ ኢያሱ ሚካኤል አወጁ:: ይህን ነባር ሕግ ብቻ ሳይሆን ሌላም ሕግ እንዲሁ የቀየሩ ናቸው::

ለምሳሌ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ገበሬው ክምሩን የሚወቃው ቅድሚያ ሹማምቶች ከፈቀዱለት በኋላ ነበር:: ታዲያ አንዳንዴ ሹማምቱ አይሄዱለትም ለአርሶ አደሩ:: ጥሩ ድግስ ካልበሉ ብዙ እህል ክፈሉ ማለታቸው ብቻ ሳይሆን ከአውድማ የማይመጡ እየሆኑ አርሶ አደሩ በመቸገሩ ይህ ኅብረተሰቡን ያስቸገረ መሆኑን ተረድተው "ይህ ሕግ



ገበሬውን የጎዳ በመሆኑ ይህን ያህል ማድጋ ክፈል ይባል"ብለው የደነገጉ (አጤ) ልጅ ኢያሱ ናቸው::

ልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ካየሁት ከማስታውሰው በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 73" ንጉሥ ሚካኤል በስንሰለት ባለመታሰራቸውና እዚያው እግቢም በመሆናቸው ሰው ስላልወደደና ማንጎራጎርም ስለጀመረ በስንለት ከቀኛዝማች ወልደሥላሴ ከራስ መኮንን ወንድም ጋር ተቆራኝተው ከግቢው ወጥተው ወደኛው ወደሐረርጌዎች ሰፈር ሄደው በኛ ሰው ዘበኝነት ተጠበቁ" ይሉና አጤ ልጅ ኢያሱ ሲያዙ የሆነውን ሲመዘግቡ ገጽ 112 "ከዚያ በኋላ ልጅ ኢያሱ የስማነው ደጃዝማች ወልደሥላሴ የሚባለዉ ያልጋወራሽ አጎት ተቆራኝቷቸው በሐረር ሡራዊትና በሸዋውም በነደጃች ወሰኔ ክፍል ባለው ጦር ዘበኝነት ከደሴ አስተላልፈዋቸውና አስቀድመዋቸው ዶባ እሚባለው አንባ እንዲቆዩ አድርገው አዘዙ" ሲሉ ጽፈዋል:: እኔ ልጅ ኢያሱን አጤ እያልኩኝ የምጽፋቸው ኢትዮጵያን 3 ዓመት አስተዳድረዋል::

ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይጠቅምም ብለው ያስተውት ሕግ እርሳቸውን ባይተዋቸውም አዋጁ ግን በሥራ ላይ ውሏል:: የዚህ ምዕራፍ መነሻ ወደሆነው ልመለስና አጤ ቴዎድሮስ ጎጃም ጦርነት ላይ የአንድ ትልቅ ቤተሰብ ያልቃል:: ከሞት የተረፉት ወይዘሮ ምንትዋብ አባታቸውና ወንድሞቻቸው ባለቤታቸው ሁሉም ስላለቁባቸው በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥላቻ አደረባቸው:: ወይዘሮ ምንትዋብ በየልቅሶውና በየቤተ ክርስቲያኑ አጤ ቴዎድሮስን ከዚህ ዝቅ ብሎ የተጠቀሰውን ግጥም እየገጠሙ ይሰድቧቸው ጀመር:: የአጤው ሰላዮች ክብራቸውን የነካ ሰው አመጣን ብለው ወደ ፍርድ አደባባይ አቀረቡአቸው::

"ጠጅም እንዳያምረኝ ቀደም ጠጥቻለሁ፤
ሥጋም እንዳይርበኝ ቋንጣ ሰቅያለሁ፤
ቢሻኝ ከወንድሜ ካባቴ እበላለሁ፤
ይህን ስትነግሩት ያጓራል ሳመሉ፤
ማናትም ቢላችሁ ምንትዋብ ናት በሉ::
ሺህ ብረት ከኋላው ሺህ ብረት ከፊቱ፤
ይህን ሳታይ ሄደች ከሶ ሻጭ እናቱ፤
አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ፤
አቃጥሎ ለብልቦ አንድዶ ይፍጃችሁ"

በማለት ይሳደቡ የነበሩት ወይዘሮ ምንትዋብ ተከሰሱና ከአጤ ቴዎድሮስ ችሎት ቀረቡ። ወይዘሮ ምንትዋብን ማንነት አጤ ቴዎድሮስ ጠይቀው ካወቁ በኋላ "ቤተሰቦችዋን ገድየባት ልታመሰግነኝ ኑሯል? ከዛሬ ጀምሮ የፈለገችውን ትበል አትንኳት የምትበላውና የምትጠጣው ስጧት አይጓደልባት" ሲሉ ፈቀዱላት። ወይዘሮ ምንትዋብ እስከ ዕለተ ሞታቸው አብራ ሳትለይ ትሰድባቸው ነበር። አንድ ቀን አጤ ቴዎድሮስን እቴጌ ጥሩወርቅ አበሳጭተዋቸው ከቤት ሲወጡ ወይዘሮ ምንትዋብ የተለመደውን ስድባቸውን ሲጀምሩ አጤ ቴዎድሮስ ቆጢት ብለው "ምንትዋብ ለአንች ስል ልሙትልሽ"ሲሏቸው ወይዘሮ ምንትዋብ ቀበል አድርገው "ጃንሆይ አያስጎምጁኝ" ሲሉ መለሱላቸው።

"ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከአንዲት ሴት ሌላ አግብቶ ቢገኝ ሀብቱን ሁሉ እንዳለ ለመጀመሪያ ሚስቱ ጥሎ እንዲወጣና ርስትም ሆነ ሹመት እንዳይሰጠው" በሚለው አንቀጽ ሥር ማንም ሰው ቁባት ማስቀመጥ መባለግ የተከለከለ መሆኑን የሚያውቅ ተማሪ ነበር። ታዲያ ከትምህርት በኋላ ለልመና መንደር ሲሄድ አንድ ጠብደል የሰው ሚስት እንደሚያባልግ ሰምቷል። ይህ ተማሪ ሆነ ብሎ በአኮፋዳው ተልባ ይዞ መሄድ ከጀመረ ውሎ አድሯል።

ታዲያ አንድ ቀን ያ ባለጌ ሰው ሲገባ ተማሪው ሲደርስ እኩል ይሆናሉ። ተማሪው ቁራሽ ቢሰጠው ቁራሹን አልፈልግም ነገር ግን ይችን ተልባ ይቁሉልኝ ሲል ሴትዮይቱን ለመናት። ሴቲቱም ተልባውን ተቀብላ መቁላት ስትጀምር ተሜ ተንደርድሮ ከቤት ሲገባ ተካ ዘሎ ማጀት ገባ። ሴትዮይቱም ተሜ ለምን ገባህ ስትለው ተልባው ሲቆላ መከደን የለበትም ብዬ ስላልነገርኩዎት ነው። ስለዚህ አይክደኑብኝ ሲላት ያለ ክዳን ተልባ ሲቆላ ተፈናጥሮ ያልቃል።

ከብረት ምጣዱ የተረፈችውን ተልባ ስጥታ ሂድ ብትለው ተሜ ተልባዬን መልቀም አለብኝ ብሎ እግሮቹን ዘርግቶ ወረንጠውን ይዞ ቁጭ አለ። ተካ ማጀት ገብቶ መውጫ ቀዳዳ ሲፈልግ ሴትዮይቱ ብትለፈልፍ ተሜ የሆዱን በሆዱ አድርጎ አደብ ይግዙ ብሎ መልቀሙን ትቶት ቁጭ ይላል። አባወራው ከሥራ ውሎ ከቤት ሲገባ ተሜ ቁጭ ብሏል። አባወራው "ምነው ተሜ" ሲለው ተሜ "ከማጀት ያለውን ድመት ለማሰር የሚረዳኝ እየጠበኩ ስለሆነ ይህን



የመንደር ድመት አስረን ወደ አጤ ቴዎድሮስ እንውሰደው" አለ። በተሜ ምክር ለሁለት ይይዙና ወደ አጤ ቴዎድሮስ ወሰዱት።

አጤ ቴዎድሮስ ችሎት ሲቀመጡ ከሳሹ ተማሪ ሁኖ ቁጭ ይላል። ይመስክርበትና ተካ "ብልቱ ይቆረጥ" ተብሎ ተፈረደበት። አጤ ቴዎድሮስ " ወንድ ነው ባይሆን ያቀፈበት ቀኝ እጁ እንዲቆረጥ ቤቱን ንብረቱን ለሚስቱ አስረክቦ አካባቢውን ለቆ እንዲሄድ" ሲሉ ፈረዱበት። ያች ሴት ተማሪውን ትክ ብላ ታይና ደሟ ፈልቶ ተሜ ለናትህ አይበልህ ስትለው ተሜ ለአባቴ እሆናለሁ። ሴቲቱ ገደል ግባ ስትለው ተሜ ሜዳ ሜዳውን እሄዳለሁ። ሴቲቱ ይነቅህ ስትለው ተማሪው ፍትፍት እበላለሁ ብሎ አበሸቃት።

ፍርዱ በተካም ብቻ አልቀረም አጤ ቴዎድሮስ ወደ ሴቲቱ ዘወር ብለው "ይህን ብልግና ስለፈጸምሽ ያለ ምንም ንብረት ከቤት እንድትዎጪ አካባቢውን እንዳትበክዪ ትለቂያለሽ" ካሏት በኋላ ግምኛ ስታለቅስ ባሏን ጠሩና "ምን ታስባለህ ሲሉት ባል "ልጆቼን በእንጀራ እናት ማሳደግ አልፈልግም ባይሆን እንዳትደግም ጃንሆይ ያስፈራሩልኝ አላቸው። አጤ ቴዎድሮስ ጠሯትና ፍርዱ ተስማማሽን ሲሏት ጃንሆይ ጥሩቴ በመሆኑ አይለምደኝም ልጆቼን ላሳድግ ሁለተኛ በዚህ ዓይነት ብልግና ብገኝ መላ አካላቴን ቆራርጠው ይጣሉት ከዛሬ ጀምሮ ሚስቱ ሳልሆን ገረዱ ሁኜ ልጆቼን ላሳድግ ብላ አለቀሰች። አጤ ቴዎድሮስ የነፍስ አባታቸውን አስጠርተው ንስሐ እንዲሰጡ አድርገው ወደ ቤቷ መልሰዋታል። ያ ተማሪ በአጤ ቴዎድሮስ ተሸልሟል። ከዚህ ወዲህ ጨለማ ለብሶ የሚሰርቅ ተካ ሁላ ፈርቶ ኑሮአል።

"የአጤ ቴዎድሮስ ሕግ ጠብደል አትፈራም፤
የመንደር አውራ ቀልዶ አልቀረም"

ሲሉ ተመልካቾች ገጥመዋል ቀደም ሲል ግብጾች የኢትዮጵያን ሕዝብ ሠርቶ እንዳይበላ በዓላቱን አብዝተው አርሶ አደሩ በሥራ ቀን ቁጭ ብሎ እንዲውል የበዓላት ጋጋታ ማብዛታቸው አይዘነጋም። የወር በዓል የሚባለው ቀለል ያለ ሥራ ይሠራበታል። በተለይ ድሃ አርሶ አደሮች በሥራ ቀን ከሀብታም ሲያርሱ ይስነብቱና በወር በዓል በሬ ተሰጥቶአቸው ያርሳሉ።

በዚህ ቀን ይህ የበስማም ቄስ "ውጉዝ ከመአርዮስ" እያለ ከጠመደበት በሮችን ያስፈተዋል። እምቢ አልፈታም ሲል ደግሞ መስቀል አያሳልሙት ልጅ ቢወልድ ክርስትና አያነሡለት ድህውን ብጥብጥ አድርገውታል። ነገር ግን ሀብታሙ ሦስትና ሁለት ሚስት ያለውን ቃል አይተነፍሱበትም። ይህ በዚህ ባለበት ወቅት አንድ አርሶ አደር ድሃ ከሀብታም ሲያርስ ሰንብቶ በጊዮርጊስ ቀን በሬዎች ተፈቅደውለት እያረሰ ሳለ አንድ የበስማም ቄስ ይሄድና "ዛሬ ጊዮርጊስ ስለሆነ ማረስ አትችልም። ካልፈታህ ውጉዝ ከመአርዮስ" ይለዋል።

አርሶ አደሩ ያለበትን ችግር ቢያስረዳው ይህ የበስማም ቄስ አልሰማ ይላል። ይህ አርሶ አደር ይህን የበስማም ቄስ በጅራፍ ያጣድፈውና "አንዱን በሬ ፈቶ ቄሱን ከአንድ በሬው ጋር ጠምዶ ሲያርሰው ይውላል። ቄሱ ደከም ሲል ተንጠራርቶ በጅራፍ ያቀምሰዋል። ማታ ፈቶ ይለቀዋል። ካህኑም አጤ ቴዎድሮስ ደብረታቦር ነበሩና ሂዶ "ንጉሠ ነገሥቱና አባ ሰላማ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ትጠንክር ቅባት ሃይማኖት ትድከም ብለው ያወጁትን ሃይማኖት ጥሶ በማግኘቴ ብገዝተው እንደበሬ ጠምዶ ሲያርሰኝ ዋለ"። ብሎ አርሶ አደሩን ከሰሱ። አጤ ቴዎድሮስ ወታደር አስልከው ያነን አርሶ አደር አስመጡት። እንደቀረበም "የሰው ልጅ እንደበሬ ጠምደህ ማረስህ ብቻ ሳይሆን በአዋጅ የወጣውን ሃይማኖት ሽረሃል። ለዚህ ምን መልስ አለህ?" ሲሉ ጠየቁት።

አርሶ አደሩ "የመጣሁት ከአሪንጎ አቦ ነው። የደብራችን በዓል አቦንና ቅድስት ማርያም ቅዱስ ሚካኤልንና ባለ እግዚአብሔርን እንደ ሰንበት አከብራለሁ። በዚህ ላይ እኔ ድሃ ስሆን ልጆች አሉኝ። በሬ ካላቸው ወገኖች በሥራ ቀን ሳርስላቸው እውላለሁ። በወር በዓል ቀን በሬዎችን ይሰጡኛል እንዲህ እያደረኩ እያረስኩ ነው ልጆቼን የማሳድጋቸው። በዚህ በጊዮርጊስ ቀን እያረስኩ ሳለ ቄሱ መጥቶ ፍታ ሲለኝ ያለብኝን ችግር ባስረዳው ከመስማት ይልቅ ውጉዝ ከመአርዮስ እያለ ከበሬው ግንባር ቀድሞ በመቆሙ ጃንሆይ ጥሩ አድርጌ ገርፌ ደከም ያለውን በሬ ፈትቼ ቄሱን ጠምጄ ሳርሰው ውያለሁ። ብታሰርም አይቆጨኝም ለልጆቼ ምግብ ዘሬን ዘርቻለሁ" በማለት የእምነት ቃሉን ተናገረ።



የአጤ ቴዎድሮስ ፍርድ በሥራ ቀን አርሰህ ለሌሎች ጉልበትህን ደክመህ በወር በዓል በሬ አግኝተህ ስታርስ መዋልህ ሃይማኖትህን አልካድህም። ብቻ ቄሱን እንደበሬ ጠምደህ ማረስህ ስህተት ቢሆንም ያደረከውን ሳትክድ በመናገርህ መልካም አድርገሃል።" ይሉና ካህኑንም ያነን የተለመደውን መጽሐፍ ቅዱስ በስንት ይከፈላል፤ ብሉይ ኪዳንን፤ማነው የጻፈው? ሐዲስ ኪዳንን ማን ነው የጻፈው! ብለው ጥያቄ ቢያቀርቡለት አንድም የማያውቅ በመሆኑ እንደገና "አንተ ሳይገባህ ሰዎች ሠርተው እንዳይበሉ ለማድረግ በመነሣትህ አንተ ገበሬ ና ይህን ቄስ 20 ጅራፍ ግረፍልኝ" ብለው አስገረፉት።

አጤ ቴዎድሮስ መለኮታዊውን ትእዛዝ የመጽሐፍ ቅዱስ ሕግ "አንድ ወንድ ላንዲት ሴት" የሚለውን በማጠንከር ብዙ የሡሩ በመሆናቸው መኳንንቱ አልተደሰቱም። ቀደም ሲል በቅዳሴ ሰዓት እንደዛሬ ተሰጥዎ የሚቀበል ምእመን አልነበረም። የማያነበው ይበዛ ስለነበር ሆዱ ቅንባ ቅንግ የሚያከለው መኳንንት ሰብሰብ ብሎ ይቆምና አድር ባይ ደብተራውን ዳዊት እንዲያነቡላቸው ያደርጉ ነበር። ዳዊት ሲነበብ ለመስማት ሲያነብና ሲተረጉም ጩኸቱ የቅዳሴውን ፍሬ ቃል በጥሞና የሚያዳምጥ ምእመን ይረብሽ ነበር። ይህን አይተው አጤ ቴዎድሮስ በቅዳሴ ወቅት የግላቸውን ዳዊት እንዳያነቡ ዳዊታቸውን የሚደግሙ ጥዋት ቀደም ብለው ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ከቅዳሴ በፊት አልያም ደግሞ ቅዳሴ ከተወጣ በኋላ እንዲደግሙ አዘዙ። ለዚህ ዋና ተባባሪያቸው መምህር አካለወልድ አንዱና ዋና ነበሩ።

የአለቃ አካለ ወልድ ተማሪ የነበሩት የትግራይ ተወላጅ አለቃ ገብረ መድኅን በተለያዩ ክፍለ ሀገራት እየተዘዋወሩ ይህን የአጤ ቴዎድሮስን ዓላማ አስፋፉት። ኋላም በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ከፍ ብሎ እነሆ ዛሬ ተራው ምእመን በቅዳሴ ወቅት ሌላ የጸሎት መጽሐፍ መድገም ትቶ የቅዳሴውን ተሰጥኦ ይቀበላል። በተለይ ሴቶች በከፍተኛ ፍጥነት እድገት አሳይተዋል። ስለዚህ አጤ ቴዎድሮስ የጀመሩት ጅምር እስካሁን በተግባር ያልዋለው የጦር መሣሪያ ባገር ቤት ለመሥራት አለመጀመሩ ብቻ ነው። በነገራችን ላይ በርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ጥረት መሣሪያ ለማምረት ተጀምሮ እንደነበር ይታወሳል። አጤ ቴዎድሮስ በፍርድ ወቅት ብዙ ጠንካራ የሆኑ ፍርዶች መፍረዳቸው ታሪክ ጠቅሶ መጻፍ ይቻላል።

አንዴ አንድ ነጋዴ ካደረበት አህዮችን ሲጭን አንዱን ከረጢት ይረሰዋል:: ይህ ከረጢት 3 መቶ ብር ሲሆን አንድ መንገደኛ አግኝቶ ይወስደዋል:: ያ ነጋዴ ብሩ መጥፋቱ ትዝ ሲለው ቤተ ክርስቲያን ሂዶ 300 ብር ስለጠፋኝ ሳገኝልኝ ሰው አንድ መቶ ብር እሰጠዋለሁ" ብሎ ይናገራል:: ገንዘቡን ያገኘው ሰው ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበረው በመሆኑ "እኔ ነኝ ያገኘሁት" ብሎ ሲወስድለት ያ ነጋዴ "የጠፋኝ አንድ ሽህ ብር ነው" ብሎ ከአጤ ቴዎድሮስ ክሶ ይወስደዋል::

አጤ ቴዎድሮስ ከሳሹን ከሰሙ በኋላ "ቤተ ክርስቲያን ጠፋኝ ብለህ የለፈፍከው ስንት ብለህ ነው" ብለው ሲጠይቁት ነጋዴው፣ "ቅድሚያ ገንዘቤን ያገኘውን ሰው ለማወቅ ስል 300 ብር ብዬ ነው" ብሎ ሲነግራቸው:: አጤ ቴዎድሮስ ፍርድ ሲሰጡ "ወንድሜ አንተ የጠፋህ አንድ ሽህ ብር ስለሆነ ያንተን ገንዘብ ያገኘው ሰው እስኪመጣ ድረስ ጠብቅ፤ አንተም ሐቀኛ ሰው ያገኘኸውን 300 ብር ይዘህ ወደ ቤትህ ሂድ" ብለው ፈረዱ::

<u>ምኒልክ መጽሔት</u> ቅጽ 1 ቁጥር 7 ጥቅምት 1992 ዓም ገጽ 40 "አጤ ቴዎድሮስ ተዚያ ሁሉ ለጋስነታቸው ለዚህ ሸፋጭ ነጋዴ ሺህ ብር እንዲያ ጠፍቶኛል ሲል አንድ 40 ጅራፍ እንደልማዳቸው ሳይረጥቡት መስደዳቸው ጉድ አደረጉ" ሲል ጽፏል::

ለነገሩ ጅራፍ መቅመስስ ነበረበት:: መጽሔቱ የፈረደው ትክክል ነበር:: አጤ ሌላም ፍርድ ፈርደዋል:: አንዲት ድሃ ሴት አንድ በጣም የሚያምር ወይፈን ነበራት:: ታዲያ ጎረቤቶቿን "እባካችሁ ቀጥቅጡልኝ" ብላ ብትለምናቸው የእነሱ ላሞች አውራ እንዲሆንላቸው ስለፈለጉ "ነገ ዛሬ" እያሉ እንቢ ብለዋት ሳለ ይህ ወይፈን በጣም ትልቅ አውራ ይሆንና አንዴ በተራራ ላይ ከብቱ ተሰማርቶ ሣር በሚበላበት ወግቶ ብዙ ከብት ገደል አስገባቸው:: በዚህ ወቅት እነዚህ የላሞቻቸው አውራ እንዲሆን ነገ ዛሬ እያሉ እምቢ ያሉት አርሶ አደሮች ሂደው ከአጤ ቴዎድሮስ ሴቷን ከሰሱ::

አጤ ቴዎድሮስ ተከሳሿን ሴት አቅርበው "ተናካሽ ውሻህን ተዋጊ በሬህን እሰር" የሚል ሕግ መኖሩን እያወቅሽ ለምን አውራ በሬሽን አልጠበቅሽም" ብለው ጠየቋት:: እርሷም ቀደም እኔ ዛሬ የከሰሱኝን



ጎረቤቶቼን እባካችሁ አዳብሩልኝ በማለት ለምኛቸው ነበር:: ነገር ግን እነሱ የላሞቻቸው አውራ እንዲሆንላቸው ስለፈለጉ እምቢ አሉኝ:: ታዲያ የላሞቻቸው አውራ ሲሆን ለምን አልከሰሱኝም" ስትላቸው አጤ ቴዎድሮስ" የአውራሽን ጥጆች ታውቂያቸዋለሽን" ብለው ቢጠይቋት "አውቃቸዋለሁ" ብላ መለሰችላቸው:: እርሳቸውም "በይ ከከብቶቻቸው መሐል ገብተሽ የአንችን አውራ የመሰሉትን እየመረጥሽ ውሰጅ" ብለው ፈረዱላት:: አተርፍ ባይ አጉዳይ ሁነው ሌሎች ከሰሩ::

አንድ ድሃ ሰው ብዙ ልጆች አሉት:: በዚህ ወቅት ባለቤቱ ትሞትበታለች:: ታዲያ ይህ ሰው ያለው አንድ በሬ ነው:: በዚህ ወቅት የነፍስ አባቱ "የባለቤትህን ተስካር አውጣ"ብሎ ደጋግሞ ይመክረዋል:: ያ ድሃ ሰው ደግሞ ልጆቼን በምን ላሳድጋቸው ብሎ ቢማፀን ቄሱ አልሰማ ይላል:: ይህ ድሀ ሰው ሲጨንቀው ወደ አጤ ቴዎድሮስ ይሄድና የሆነውን ሁሉ ዘርዝሮ ነገራቸው:: በዚህ ወቅት እርሳቸው ይህን ቄስ አስጠርተው በል "ለዚህ ድሃ ሰው አስር ማድጋ እህል ሁለት በሬ ቅቤም ሆነ እህል ስጠውና የባለቤቱን ተስካር ያውጣ" ብለው አዘዙት::

ይህ ቄስም ምርጫ ስለሌለው የድሃውን ሰው ሚስት ተስካር በራሱ ገንዘብ እንዲያወጣ አድርገውታል:: አንድ ሌባ ሲሰርቅ ይሰማና ባለቤቱ ሊይዘው ሲሞክር ሩጦ አመለጠው:: ነገር ግን "በቴዎድሮስ አምላክ ቁም" ሲለው ይቆማል:: ቁሞ ሲገኝ ሌባውን በጦር ወግቶ ይጥለዋል:: ያ የተወጋ ሰው ወጊውን ካጤ ቴዎድሮስ ፊት በሕግ አቀረበው:: ከሳሹ ሌላው ሰው ማለት ነው::

<u>ምኒልክ መጽሔት</u> ቅጽ 1 ቁጥር 7 ጥቅምት 1992 ዓም ገጽ 40 "እግዚአብሔር ያሳይዎ ጃንሆይ!አለ:: አጤ ቴዎድሮስ ግን ይሄን ሁሉ ነገር ዝም ብለው አድምጠው በመጨረሻ በጨለማ ተሰው በረት ገብቶ ከብት የሚወስድ ጅብ እንጂ ሰው አይደለም:: አሁን ጅብ ለምን ወጋ ብለህ ነው መክሰስህ? አበጀ እንኳን ወጋህ!አሉና ተቆጡት:: ወዲያውም ወጊውን ዘወር አሉና ነገሩን የዋጡለት አስመስለው አንተስ ከሳሽ የተናገረው ሁሉ የእውነት ነውን? ብለው እየሳቁ ጠየቁት::"

“ተከሳሹ በዚህ ጊዜ አድራጎቱ የተወደደለት መስሎት አዎን እርግጥ ነው ብሎ መለሰ:: አጤ ቴዎድሮስ አዎንታን በሰሙ ጊዜ በዚያ ሁሉ ሰው መሃል ካሣ የመይሳው ልጅ ብለው ፎከሩና አያችሁ በኔ ስም አራዊት ጅብ ሳይቀር ሲገዛና ሲዳኝ የሌት ሌባ ጅብናአውሬ ነው:: ይሄው አውሬ በቴዎድሮስ አምላክ ሲባል ቀጥ ብሎ ቆመ፡ ብለው ለመኳንንቱ ሁሉ አሰሙ::”

“ቀጥለው ግን ተከሳሹን ተበረትህ ምን ያህል ከብት አለህ? አሉና ጠየቁት:: እሱም ተጥጃውም ተምኑም ብዬ አምስት መቶ ያህል የቁም ከብት አለኝ አለ:: ስንት ልጆች አሉህሳ? አሉት:: ምሽቴ መካን ናትና ልጅ የለኝም ብሎ መለሰ:: እንዲህ ተሆነ መልካም አንተ በቴዎድሮስ አምላክ ቁም ብትለው ታመለጠህ ወዲያ ተዳኝቶ እሱ ሌባው ቢቆምልህ አንተ ሳትዳኝ ወግተህ ጣልኸው፤እንዲህ ተሆነ እኔን የኔን ስም ነው እንጂ የወጋህ እሱን አይደለም፤ ስለዚህ ከሳሽህ እኔ ነኝና መኳንንቱ ይፍረዱን፤ፍርድ ቢሰጥህ ዳን፤ቢነሳህ ተቀጣ፤ ብለው ንጉሡ ራሳቸው ከሰሱት:: መኳንንቱም ሊቃውንቱም አንድ ሆነው እንዲህ ብለው ፈረዱበት:: በሩጫ ተፈታትነው በጉልበት ተሞካከረው አባራሪው ከተባራሪው ለመድረስ ሰንፎ ባይሆንለት ባምላኩ ብሎ ያመለጠውን ከሰሰ:: እኔም ተከሰሰኝ ለሥርዓት እንጂ ለመወጋት አላሰበኝም ብሎ ተዳኝቶ ቆመለት::”

“እሱ ከሳሹ ግን ሥርዓቱን ትቶ ወደ ጉልበቱ ተመልሶ ወጋውና ጣለው:: ይሄን ታደረገ ቀኝና ግራ ተካሶ ቁሞ ተዳኛ ፊት ተሙግት መሃል አንዱን አንዱ መግደል ያለ ነውና አደባባይ ወጥቶ ተዛፍ ላይ ይሰቀል በቃ ብለው ፈረዱበት:: አጤ ቴዎድሮስ ግን ብቅል ይመስል እሱን ተመስቀል ይልቅ በሱ ንብረት ያ የተወጋው ይግባበት::”

“ወጊውም እስር ቤት ገብቶ በጅቦ (የእግር ብረት) ይታሰርና ዕድሜው ይፍታው:: ምሽቱ ግን በሱ አበሳ አትወረስምና ጣማ ገንዘቧን (የደከመችበትን ገንዘብ) ተወራሹ ጋር ተካፍላ ትሂድ ብለው ፈረዱ” ሲሉ ጽፈዋል:: በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ብዙ ፍርድ ተፈርዶአል:: ሁሉንም ፍርድ ከዚህ ምዕራፍ ላይ ማስቀመጥ ባይቻልም ለወደፊቱ ሌላው ትውልድና ጸሐፊ ሁሉንም ሰብስብ አድርጎ ራሱን የቻለ መጽሐፍ እንደሚያወጣው ተስፋ አለኝ::



# ምዕራፍ 5

## የአጤ ቴዎድሮስ ደግነት

ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ ሊትማን ያሳተመው ገጽ 13 “ደጃች ብሩም ተያዙ በግንቦት 19 ቀን ነፍጥ ሳይተኩስ ጦርም ሳይወረውር ደጃች ብሩም ድንጋይ ተሸክመው ወደቁ:: ደጃዝማች ካሣም ደንጋው ይነሣለት አሉ:: ደጃች ብሩን ሸማ አስነጥፈው አስቀመጡአቸው:: ደጃዝማች ካሣ እንዲህ ብለው ጠየቋቸው፤ አሁን እኔን ይዘውኝ ቢሆን (ምድን) ምንድን ባደረጉኝ አሉአቸው:: ደጃች ብሩም እንዲህ አሉ:: እርስዎን ብይዝዎ ለማየት አላደርስዎም ነበር:: (አስገድለዋል)አስገድልዎት ነበር እንጂ አሉ” ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን ታሪክ አቶ ገሪማ ታፈረም ጽፈውታል::

አባ ታጠቅ ካሳ የቋራው አንበሳ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 50 “ደጃዝማች ካሣ ተማራኪውን ብሩ ጎሹን አሁን ድሉ የርስዎ ቢሆንና እኔን ቢማርኩኝ ምን ባደረጉኝ ነበር አሉዋቸው:: ደጃዝማች ብሩ ሲመልሱ እርስዎን ብይዝ ኖሮ ለማየትም አላደርስዎም አስገድልዎት ነበር አሉ:: ደጃዝማች ካሣም እንዴት አድርጎ ለጠላቴ አሳልፎ ይሰጠኛል ብለው እግዚአብሔርን አመሰገኑ” ሲሉ ጽፈዋል::

ከዚህ በላይ የተነበበው ጥቅስ በሁለቱም በኩል ያለው እውነታ ግልጽ ነው:: ደጃዝማች ብሩ በትክክል ደጃዝማች ካሣን ቢማርኩ ኑሮ የሚያደርጉትን የሆዳቸውን ተናገሩ:: ደጃዝማች ካሣ ደግሞ ይህን የመሰለ መልስ ሲሰሙ ሳይበሳጩ መቅረታቸው ደግነታቸውን የሚገልጽ ነው:: ደብተራ ዘነብ ከጻፉት የሚያስረዳው ነገር ቢኖር አጤ ቴዎድሮስ ከጦርነት ላይ የማረኩአቸውን ሰዎች መልቀቃቸውን ነው:: ከደብተራ ዘነብ አተራረክ ጋር የሚመስል ቆንስል ፕላውዴ ለአገሩ መንግሥት የጻፈው ደብዳቤ የደብተራን ዘገባ አጠናካሪ ነው::

የኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታኒያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 26 “የተሸነፉ ጠላቶችን አካል ማጉደል ከልክለዋል:: ሊጋስነታቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ወደር የሌለው ነው:: ድል

ሲያደርጉ መሐሪ መሆናቸውን ከአንደበታቸውና ከተግባራቸው በጥንቃቄ ተመልክቻለሁ” ይሉና

ገጽ 27 “ከመጠን በላይ ለጋስና ከማናቸውም ፍቅረ ንዋይ የጸዱ ናቸው:: ለወታደሮቻቸው የጦር መሣሪያ እንደማግኘት የሚያስደስታቸው አንዳችም ነገር የለም:: እስከ ዛሬ ድረስ ድል ያደረጓቸውን ሁሉ ከመማረካቸውም በላይ እንደ ጠላት ሳይሆን እንደ ወዳጅ ያዩአቸዋል:: የእምነታቸው ጽኑነት የሚደንቅ ነው” ሲሉ ጽፈዋል::

ነጋ ወልደ ሥላሴ ባለታሪክ ኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 175 “ቴዎድሮስ በዚህ በነገሡበት ወቅት ታላቅ ዝናን አግኝተው ነበሩ:: ቂም የማይይዙ ይቅር ባይ በተለይም ያሸነፏቸውን ጠላቶቻቸውን መሐሪ ጽኑ የሃይማኖት አማኒነት የሠፈረባቸው ንጉሥ ነበሩ:: የዕውቀትና የትምህርት ፍቅር ያደረባቸውና አብረዋቸው ከነበሩ ሰዎች ሁሉ በማናቸውም ረገድ የላቁና ለአስተዳደርም ልዩ ተሰጥዎ የነበራቸው በመሆናቸው ሰዎች የሚያደንቋቸውና የሚከተሏቸው ነበሩ:: እንዲሁም ልዩ ቁመና የነበራቸው ሲራመዱም እንደ ደቦል አንበሳ የንጉሥ አረማመድ የሚራመዱ ማናቸውም ዓይነት ድካም የማይበግራቸው ሰው ነበሩ” ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ ማታ ማታ አንዳንዴ ብቻቸውን በሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ ወይም ሁለት ወታደር አስከትለው ሰፈር ለሰፈር ይገቡና የሚባለውን ሲሰሙ ያመሻሉ::

ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፈው ገጽ 17 “አንድ ቀን የሚያምኑትን ዘበኛ ይዘው አልባሌ መስለው አዳፋ ጋቢ መሳይ ለበሱና ከጨለመ በኋላ በሰፈሩ ይዞሩ ጀመር:: በየጎጆውም እየተጠጉ ያዳምጡ ነበር:: እኩሉ ያልተኛ እኩሉም ተኝቶ ከዝያ ወድያ ካንድ ወታደር ጎጆ ተጠግተው ቢያዳምጡ ባልና ምሽት በግብረ ሥጋ ሲጣሉ ሰሙ:: ወንድ ይለምናል ሴቲቱም አይሆንም ትላለች::”

“ከዝያ ወድያ ወንድየው በማርያም እያለ ቢለምን በጻድቃን፤በቅዱሳን እያለ ቢቀባጥር እምቢ አለችውና በይ በቴዎድሮስ ሞት እንድትሰጭኝ አላት:: እሷዋም ቴዎድሮስ ከሚሞት ጎንደር አይታረስም አለችና ሰጠችው” ሲሉ ጽፈዋል::



ጥቅሱን ሙሉ በሙሉ ሳይሆን ላሳጥረውና ጥዋት ባልና ሚስቱ ተጠርተው ከአጤው ሲቀርቡ ጥፋት አጥፍተናል ብለው ሲፈሩ ሽልማት ተሸልመዋል:: አንዴ ደግሞ ጎጃም ደጀዝማች ተድላ ጓሉን ለማደን ዘምተው ሳለ ማታ ብቻቸውን ያደረጉት ይህን ነው::

ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት ገጽ 18 “አጤ ቴዎድሮስ ብቻቸውን አንድ ወታደር መስለው አዳፋ ልብስ ለብሰው ሆኑራቸው ሹርቤው እንደ ተንጨበረረ ጨሬያቸው በትክሻቸው እንዳደረጉ ከአንዲት ባላገር ሴት ቤት ገቡና እንዴት ዋልሽ አልዋት እሷም እግዜር ይመስገን እንዴት ውልሃል አለቻቸው::”

“መልሰው እባክሽ ርቦኛልና እንጀራ ስጭኝ አልዋት:: እሷም የማነህ ወታደር አለቻቸው፤የተድላ ጓሉ እንጂ የማን ብለሽኝ አልዋት ይህን ተነጋገሩና እንጀራ በርጎ አቀረበችላቸው: ውሃም አስታጠበችና መብላት ሲጀምሩ ተቀመጠች:: ከዝያ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ እንዲህ ብለው ጠየቁዋት፤ ያ እብድ ንጉሥ ወዴት ደረሰ ይባላል ወሬውን አልሰማችሁም?”

“አልዋት እርስዋም መለሰችና እብዶችስ የተድላ ጓሉ ወታደሮች ናችሁ እንጅ የተቀባ ንጉሥ እብድ አይባልም አለችና መልሳም አሁን ሸዋ ሂዶ ብትሰሙ አገር ስለማጥፋት ደስ ብሏችኋል ያእብድ የምትሉት ንጉሥ ቢዘልቅባችሁ ደግሞ ድምባችሁን አጥፍታችሁ ከአምባ ለመሸሸግ ነው አለቻቸው” ሲሉ ጽፈዋል::

እርሳቸው የተቆጡ መስለው የቀረበውን ምግብ ሳይበሉት ወደ ሠራዊታቸው ተመለሱ:: ጥዋት ያች ሴት ተጠርታ ተጠየቀች የሆነውን ሁሉ ተናገረች የአካባቢው ቤት በእሳት ሲለበለብ የእርሷ ቤት ሳይበላባትና ሳይዘረፍባት ቀርቶ ሌላም መጠወሪያ ተቀብላለች::

አንዴ አጤ ቴዎድሮስ መንገድ ሲሄዱ ብዙ ልጆች የነበሩአቸው ገበሬ አገኙ:: ስንት ልጅ አለህ ሲሉት 10 አላቸው እርሳቸውም በየዓመቱ ነው የምትወልደው ሲሉት አርሶ አደሩ“ ጃንሆይ መንታ መንታ እየሆኑ ነው የተወለዱት አላቸው እርሳቸውም ታዲያ በሬ አለህን ሲሉት የለኝም ቆፍሬ ነው የማሳድጋቸው ሲላቸው ሁለት በሬ ሰጡት:: ይህን ሁለት በሬ መቀበል የሰማ የ16 ልጆች አባት አርሶ

አደር እየተከተለ ይመጣና ጃንሆይ 16 ልጆች አሉኝ በሬ የለኝም ሲላቸው አራት በሬዎች ሰጡት። ባመቱ በዚያ ሰፈር ሲያልፉ ሁለት በሬ የተቀበለው ገበሬ ጓሮው ጎተራ በጎተራ ሁኖ በሬዎች ከስተው ውሻው ወፍሮ ልጆች አለምልመው ተመለከቱ።

16 ልጅ የነበረው 4 በሬ የተቀበለው ገበሬ በሬዎች ወፍረው ውሻዎች ከስተው ልጆቹ አመድ ወርሷቸው ተመለከቱና "በል አንተ ይዞ ሚች እነዚህን በሬዎች ለዚህ ለሚያርሰው አስረክብ አንተ በእርሱ ታዘዝና እደር። ልጆችህ ከሚራቡ ይህ ጠንካራው ገበሬ አርሶ ያብላቸው ምናልባት ያንተ ልጆች ከዚህ ገበሬ ጥንክርና ሊማሩ ይችሉ ይሆናል" በማለት ቀምተው ለጠንካራው ገበሬ ሰጥተውታል። አጤ ቴዎድሮስ ደፋር ልበ ሙሉ ጀግና ሴት ሆነ ወንድ ይወዳሉ። ትክ ብለው ሲመለከቱት ትክ ብሎ የሚያያቸው ሰው ይወዳሉ። አንገቱን የሚደፋ ወይም የማይከራከራቸው ዝም የሚላቸው ሰው አይወዱም ነበር።

በተፈጥሮአቸው አጤ ቴዎድሮስ አስከሬን ካዩ ከበቅሎ ወርደው አስከሬኑ ወደሚሄድበት ቤተ ክርስቲያን ሂደው አስከሬኑ ግብአተመሬት እስኪሆን ቆመው ይቆያሉ። ለቤተሰቦችም አጽናንተው ይሄዳሉ። ሌላው እርሳቸው ከሚያከብሩት ታላቁ ሙሽራ ሲሆን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሙሽራ ሲሄድ ሚዜው ብዙ ነው። ጥሩንባ እየተነፋ ጃሎ እየተባለ ይኬዳል።

ታዲያ በአንዱ ወቅት ዲያቆን ተድሮ ሚዜዎቹ ዲያቆናትና ወጣት ካህናት ስለሚሆኑ ከብዛታቸው የተነሣ ልብሳቸው ነጭ የጠመጠሙት ሻሻቸው ተራራ መስሎ ሲመጡ ያዩአቸውና አጤ ቴዎድሮስ እንደልማዳቸው ከበቅሎ ወርደው እለፉ አሉ። ሲመለከቱአቸው ንድድ አላቸውና "ሁላችሁ ቄሶችና ዲያቆናት ናችሁ ብለው ሲጠይቁ ሁሉም የሚመስገኑ መስሏቸው አዎ ጃንሆይ" አሉ።

አጤ ቴዎድሮስ ቀበል አድርገው "መጽሐፍ ቅዱስ በስንት ይከፈላል"ብለው ሲጠይቁ። እንኳን ከጠላ ጋር የዋለ የበስማም ቄስ በውሃ ቀንም ይህን ጥያቄ መመለስ አይችልምና መፋጠጥ ጀመረ። ለካ ሙሽራው ልበ ሙሉ ጎበዝ ተማሪ ኑሮ "እኔ ልመልስ ይፈቀድልኝ" ሲል ጠየቃቸው።



አጤ ቴዎድሮስም መልስ ሲሉት ጃንሆይ መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት የሚከፈል ሲሆን እያንዳንዱ በምን እንደሚለይ አስረዳቸው። አጤ ቴዎድሮስ መልሱ ስላስደሰታቸው "ይህ ነው የአካልዬ ልጅ" ብለው ከዚህ በፊት ለማንም አድርገውት የማያውቁትን ለዚህ ዲያቆን ሙሽራ በቅሎአቸውን ሰጥተውታል።

አጤ ቴዎድሮስ አንዴ አልባሌ ልብስ ለብሰው ከወታደሮቻቸው መካከል ገብተው የሚሉትን ሁሉ ማዳመጥ ጀመሩ። ታዲያ አንድ ወታደር ምርር ብሎ ሲያማቸው ይሰሙና ወደ ድንኳናቸው ተመለሱ። ጥዋት አንድ አገልግል ባዶውን ሌላው አገልግል ብር ሞልቶ እንዲቀመጥ አደረጉ። የሁለቱም አገልግል አንድ አይነት ነው። ታዲያ ከሠራዊቱ መካከል ያንን ወታደር ወደ እሳቸው አስመጡትና እንዲህ አሉት። "ትናትና ምርር ብለህ ማማትህን አውቃለሁ።"

"አሁን ከፊትህ ሁለት አገልግል ተቀምጧል አንዱ ባዶ ነው፤ ሁለተኛው አገልግል ሙሉ ብር ይዞአል። ብር የያዘውን አገልግል ካነሳህ እግዚአብሔር ሰጥቶሃልና ትወስዳለህ። ባዶውን አገልግል ካነሳህ ግን በድልህ እዘን ስለዚህ ምረጥ" አሉት። ያ ወታደርም ቁሞ ሁለቱ አገልግሎች በጽሞና ከተመለከተ በኋላ "ይህን መርጫለሁ" ይላል። እርሳቸውም በሉ ክፈቱት ሲሉ አዘዙ። ነገር ግን ወታደሩ የመረጠው ባዶውን ነበር።

አጤ ቴዎድሮስ ሁለተኛውን አገልግል እንዲከፈት አደረጉ። "እኔ እግዚአብሔር በሚያውቀው ሰጥቼህ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አልፈቀደልህምና ሁለተኛ እንዳታማኝ" ብለው አሰናበቱት። የዚህን የአገልግል ታሪክ ብዙ ደራስያን ጽፈውታል።

# ክፍል ስድስት

## ምዕራፍ 1

### የግብፁ ፓትርያርክ መታሰር!

አክሊሉ ታደሰ ክህነትና ካህን በቤቱ በእስራ ምእት 2000 ዓም በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 41 "የግብጹም ፓትርያርክ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ለመሰብሰብ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ሳለ በቱርክና በኢትዮጵያ መካከል በነበረው ፖለቲካ ነክ በሆነ ነገር እየገባ ስለ አስቸገራቸው ፥አንተ የክርስቲያን መሪ ስትሆን እኔን ክርስቲያኑን ንጉሥ መርዳት ነበረብህ እንጂ ከዚህ ውስጥ ምን አገባህ፥ ብለው ተቆጥተው የኢትዮጵያንና የግብፅን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አሰሯቸው:: እንዲህ ያለው ውርደት በግብፃውያን ላይ ሲወርድ የመጀመሪያ ጊዜ ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

የዚህ ክፍል መጀመሪያ ምዕራፍ ያደረኩት የግብጽ ፓትርያርክ የታሰሩበት ምክንያት የሚል ሲሆን አንዳንድ ሰነድ ደግሞ አጤ ቴዎድሮስ ሱዳንን ልቀቁልኝ ብለው በመጠየቃቸው ምክንያት ለሽምግልና ነው የመጡ ተብሏል::

የኔሰው አስረስ ትቤ አክሱም መኑ አንተ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 302 "አጤ ቴዎድሮስ ስናርን ካርቱምን ልቀቅ ያባቶቼ መንግሥት ነበረ፤አለዚያስ ሰፊ ሜዳ ይዘህ ቆየኝ ብለው ልከው ነበረ:: የምስር ንጉሥ ፈርቶ አስታራቂ የምስርን ጳጳስ ወይም በትረክ አባ ዳውድን ወደ ንጉሥ ቴዎድሮስ ሰደደ"ሲሉ ጽፈዋል::

አለቃ የኔሰው አስረስ "አባ ዳውድ ያሉአቸው አቡነ ቄርሎስን ሲሆን ጳጳስ ከመሆናቸው በፊት ስማቸው ዳውድ ይባሉ ስለነበር ነው:: አለቃ የነሴው አስረስ የታወቁ የአንድ ሊቀ ጠበብት አባት ናቸው:: ሊቀ ጠበብቱ በአባትነት ባይቀበሉና ቢክዱም የታወቀ መሆኑን ቀደሰ ዓለማየሁ ሞገስ ጽፈዋል::



(ቀደሰ) ዓለማየሁ ሞገስ ምኒልክ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 15 ሐምሌ 1992 ዓም ገጽ 23 አሳምረው አቅርበውታል:: ሊቀ ጠበብቱም "ትክክል አይደለም" በማለት እስከዛሬ ድረስ መልስ አልሰጡም:: ወደ ነበርኩበት ልመለስና የግብጹ ፓትርያርክ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ለሽምግልና ነበር:: ለሽምግልና መምጣታቸው የጦር መሣሪያም እንዳይሠሩ ለማድረግና ለሌላም መሆኑ አይዘነጋም:: ከዚህ ዝቅ ብሎ ታሪክ እየጠቀስኩኝ ለማስረዳት እሞክራለሁ:: ወደ ነበርኩበት ልመለስና የእኛን ካህናት ያበላሿቸው እነዚህ ዲዳ ከግብጽ በገንዘብ ተገዝተው የሚመጡት ጳጳሳት ናቸው::

ሊቀ ሊቃውንት ተግባሩ አዳነ ንጉሥ አዕላፍ ሰገድ ከ2 ሺህ ዓመት የታሪክ ማስታወሻዎች ጋር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 99 "አጤ ቴዎድሮስ 2ኛ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ:: ከነገሡም በኋላ መሳፍንቱ በጎጥ፤በወንዝ፤በጎሳ፤በነገድ፤ በሃይማኖት፤ከፋፍለው ለድህነት እና ለሁከት ለውጭ ተስፋፊዎች የዳረጓትን ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ በመጣራቸው እና ቴክኖሎጂ እንዲስፋፋ በማወጃቸው በተጨማሪም የግብፅ ቱርኮችን የውጭ አገር ተስፋፊዎችን ለማቆም ያደረጉት ታላቅ ጥረት ነበር" ሲሉ ጽፈዋል::

ግብጻውያን ጳጳሳት ከ330 ዓም ወዲህ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የውሸት ሰነድ በማቅረብ ሲመሩ ኑረዋል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ካገኘሁት ሰነድ የተረዳሁት እውነታ ቢኖር ሕዳር 29 ቀን በ325 ዓም ከተረቀቀው ሕግ ውስጥ "ኒቅያ 42 የኢትዮጵያ ሰዎች ከዐዋቂዎቻቸው ወገን በራሳቸው ፈቃድ ሊቀ ጳጳሳትን ለራሳቸው አይሹሙ:: ጳጳሳቸው ከእስክንድርያው በዓለ መንበር በታች ነውና::

ከሊቀ ጳጳስ በታች የሆነውን ሊቀ ጳጳስ ከእርሱ ወገን ሊሾምላቸው የሚገባውም እርሱ ነው":: የሚለው በሕዳር 29 ቀን 325 ዓም ከዛሬው ቱርክ ኒቅያ ተብላ ከምትጠራ ቦታ ላይ የተጻፈ አስመስለው ግብጾች በ330 ዓም ስደተኛው አባ ሰላማ ተብለው የሚከበሩት አንዳንዴ የግሪክ ተወላጅ ናቸው የሚሉ ሌሎች ደግሞ የሶሪያ ተወላጅ የሚያደርጓቸው ግለሰብ ከግብጾች ተረቆ የተሰጣቸውን ጽሑፍ ተቀብለው ወደ ኢትዮጵያ ይዘውት መጥተዋል::

የኢትዮጵያ ልጆች ጵጵስና እንዳይሾሙ የተከለከለው በ318 አባቶች ነው ተብሎ አባቶቻችን የተቀበሉትን ታሪክ እኛም ትክክል መስሎን

በታሪክ ሰነድነቱ የኒቅያን አባቶች ስንነቅፍ መቆየታችን አይዘነጋም:: በመሠረቱ ይህ ከፍ ተብሎ የተጠቀሰው ቀኖና በኒቅያ ጉባኤ አለመወሰኑ ታውቋል::

NICENE AND POST-NICEAN FATHERS. THE SEVEN ECUMENICAL COUNCILS በተባለው መጽሐፍ page 8 "The Canons of the 318 Holy Fathers Assembled in the City of NICE, IN Bithynia ትርጉም የኒቅያ እና የድኅረ ኒቅያ አባቶች ሰባቱ የኢኩሚካል ጉባኤዎች "የ318ቱ ቅዱሳን አባቶች ሕግጋት በቢታንያ የኒቅያ ከተማ ስብሰባ" ይላል:: እነዚህ 318 አባቶች ኢትዮጵያ በግብጽ ውስጥ ሁና ትተዳደር ብለው አልወሰኑም:: ቃሉም ከዚህ የሚከተለው ነው::

PAGE 15 "The Bishop of Alexandria shall have jurisdiction over Egypt,Libya,and Pentapolis.As also the Roman bishop over those subject to Rome. so, too the Bishop of Antioch and the rest over those who are under them, If any by a bishop contrary to the judgment of the Metropolitan,let him be no bishop.Provided it be in accordance with the canons by the suffrage of the majrity, if three object,their objection shall be of no force." ሲል የተጻፈውን ማንበብ ችለናል::

አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ሕግን ጥሶ ሕጋዊ መሆን ይቻላልን? በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 55 "የእስክንድርያ መንበር በኢትዮጵያ ሀገረ ስብከት ላይ የሥልጣን የበላይነት እንዲኖረው ከየትኛውም የጥንት የቀኖና መጽሐፍ ላይ አይገኝም:: ሆኖም ግን ግብፃውያን በራሳቸው የሐሰት ቀኖና ቀምረው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በአባትነት ሳይሆን በገዥ የበላይነት ለ1600 ዓመታት ሲገዙ ኖረዋል" ሲሉ ጽፈዋል::

ንጉሠ ነገሥት አጤ ሀርቤ ከኢትዮጵያውያን መካከል ለማሾም ባደረጉት ጥረት በግብጾች መወገዛቸውን የሀሰት ሰነድ ሚያዝያ ወር የሚነበበው ስንክሳር ታሪኩን ጽፎት ይገኛል:: ይህ መጽሐፈ ስንክሳር የተባለው እስከ ግትልትሉ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስረክበዋት ነበር:: የሚገርመው ነገር ቢኖር እነሱ በሀገራቸው ከእስላሙ ጋር



ተስማምተው እየኖሩ በኢትዮጵያ ያሉት ክርስቲያኖች ከእስላሙ ጋር ተስማምተው እንዳይኖሩ መጥፎ ዘርም ዘርተዋል::

ሊቀ መዘምራን ላእከ ማርያም ወልደ ኢየሱስ ትርጉም መጽሐፈ ስንክሳር ዘወርኃ መጋቢት "የእስላም ወገን የሆነ ስሙ ግራኝ የሚባል ተነሥቶ አብያተ ክርስቲያናትን አጠፋ:: ከንጉሥ ልብነ ድንግል ጋር ጦርነት ገጠመ ንጉሡም ወግቶ መመለስ ቢሳነው አርበኞች ሠራዊትን እስከሚሰበስብ ከእርሱ ሸሸ በስደትም እያለ በድንገት ታሞ ሞተ" ይላል:: ይህ መጽሐፍ የሃይማኖት ድርሳን ሁኖ በመጋቢት ወር ይነበባል::

ተመልከቱ ይህ ከላይ የጠቀስኩት ጥቅስ የታሪክ መጽሐፍ እንጂ የገድል መጽሐፍ ሊሆን አይችልም:: ከዚሁ መጽሐፍ ነው ንጉሠ ነገሥት ቅዱስ ሀርቤ ኢትዮጵያውያን ከልጆችዋ መካከል ጵጵስና መሾም አለባቸው ብለው በመጠየቃቸው ምክንያት የግብጽ ፓትርያርክ ተቆጥቶ የውግዘቱ ደብዳቤ ኢትዮጵያ ሲደርስ በሀገሪቱ ቸነፈር ችግር ሆነ ብሎ የጻፈው::

አባቶቻችን አዋልድ መጻሕፍትን በጥሞና በሊቃውንት ጉባኤ ማስመርመር አለባቸው የምለው ለዚህም ነው:: ንጉሠ ነገሥት ቅዱስ ሀርቤ ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ሠርተዋል:: ይህም ታሪክ ነው ማንም ያላደረገውን እርሳቸው ተጋድለዋል::

ዶ/ር አያሌው ሲሳይ የአገው ሕዝቦችና የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ታሪክ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 136 "ጳጳስ ሚካኤል ከኢትዮጵያውያን መምህራን በመምረጥ በሥራቸው ጳጳሳት ማድረጋቸውን ትተው ቆሞስ እያሉ ሰባት ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾሙልህ ብለውታል::"

"በዚህም መሠረት አባ አብርሃም፤አባ ኤዎስጣቴዎስ፤አባዘፈረ ዲዮስቆሮስ፤አባ አርከ ማርያም፤አባ ብንያም፤አባ ተክሎተ ብርሃን እና አባ ዘመደ ፊልጶስ የተባሉ ሰባት መምህራን በቆሞስነት ተሹመው ኢትዮጵያን ተከፋፍለው እንዲያስተዳድሩ ተደርጓል:: ዘግይቶ ደግሞ የኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ ጳጳስ አባ ሚካኤል በንጉሡ ሀርቤ ልመና ስለጨመሩላቸው ቀሳውስትን እና ዲያቆናትን መሾም ችለዋል" ሲሉ

ጽፈዋል:: ከዚህ ወዲህ በኢትዮጵያ የተነሡት ነገሥታት ከግብፃውያን እጅ ለመላቀቅ ብዙ ጥረት አድርገዋል::

ቀዳማዊ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጻድቁ ለቤተ ክርስቲያን የታገሉ ናቸው:: እርሳቸው 12 ኤጲስ ቆጶሳትን ሹመዋል:: ግብጾች ይህን ሲሰሙ ያለ ምንም ጉቦና ደጅ ጥናት ራሳቸው ጳጳስ ሹመው ላኩ:: በዚህ ሰዓት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቀዳማዊ ለግብጻዊው መንበራቸውን አስረክበው ወንጌል ለማስተማር ተሰማሩ::

ከዚህ ወዲህ በተለያዩ ወቅት ግብጾች ክርስቲያኑን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከመርዳት ይልቅ ለትውልድ አገራቸው በማድላት ኢትዮጵያን ሲያደክሙ ቆይተዋል:: አጤ ቴዎድሮስ ቱርኮችን ከኢየሩሳሌም ለማስወጣት በሚያደርጉት ፍክራ የጦር መሣሪያ በኢትዮጵያ እንዲመረት የኢትዮጵያ ዳር ደንበር እንዲጠበቅ የሚያደርጉትን ተግባር ለማጨናገፍ የግብጹ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ታሰሩ::

አጤ ቴዎድሮስ ጳጳሳቱን አስረው ዝም:: አላሉም ሊቃውንቱን ጠርተው በነገሩ እንዲመክሩበት አድርገዋል:: ግን ጉባዔው መደረጉንና የጉባኤውም አሳብ ምን እንደነበረ ከዚህ በሚከተለው ቅኔ ለመረዳት ይቻላል:: ሁለት ወንድማማቾች ባሉበት ያልተሠራ ተሠራ ያልተደረገ ተደረገ ለነፍሱ ሥራ ብልሃተኛ የሆነው ቴዎድሮስ ጽዮን ሃይማኖትን ማደርያው እንድትሆን መርጧታልና ካለ በኋላ የሁለተኛዋ ኒቅያ መልካም ወይም ምሳሌ እንዲህ ከሆነ ጉባኤውንም ደብረታቦር ብሎ ከሰየማት ቁስጥንጥንያ ምንድናት ብሎ ቁስጥንጥያስ ኢትዮጵያ ናት ኒቅያም ደብረ ታቦር ናት÷” በማለት ቅኔውን ዘግቶታል::

ይህ ቅኔ በደብረታቦር የሊቃውንት ጉባኤ መደረጉን ከማስረዳቱም በላይ ጉባኤውንም በኒቅያና በቁስጥንጥንያ ከተደረገው ጉባኤ በማወዳደር የራሱን አክብሯል በቅኔው መጀመሪያ ሁለቱ ጳጳሳት ባሉበት ከዚህ በፊት ያልተደረገ ነገር መደረጉን ተናግሯል:: የጉባኤውም ምክንያት አጤ ቴዎድሮስ መሆናቸውን ገልጿል” ቅኔው ሥላሴ ቅኔ ሲሆን

ተገበረ ዘኢተገብረ፤ክልኤቱ አኃው ኃበ ሀለዉ፤



እስመ ለሃይማኖት ጽዮንማኀደሮ ከመትኩኖ ኃሪያ
ቴዎድሮስ ለተግባረ ነፍሱ ዘኮነ ኬንያ፤
አመኒ ደብረታቦር ለጉባዔሁ ሰመያ፤
ምንት ይእቲ ቁስጥንጥንያ፤
ቁስጥንጥንያሰ ኮነት ኢትዮጵያ፤
ወኒቅያ ደብረ ታቦር ነያ:: ይላል::

ቅኔውንም የተቀኙት የሞጣው ዓራት ዓይና ጎሹ ናቸው ይባላል:: ዓራት ዓይና የተባሉት በሊቅነታቸው እንጂ ዓይነስውር ነበሩ:: በማለት የነገሩኝ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ናቸው:: ከአብነት መምህራን ሊቆች መካከል አንዳንዶቹ ዓይነ ስውሮች ነበሩ:: በጊዜያችንም አለቃ አያሌው ታምሩ ዓይነ ስውር ነበሩ:: ወደ ተነሣሁበት ምዕራፍ ልመለስ::

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 176 “አጤ ቴዎድሮስን ከውጭ መንግሥታት ጋር በማበር እጅግ ያበሳጩአቸው የነበሩት የካቶሊክና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ብቻ አልነበሩም:: የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ደግሞ አገርዎን ይልቀቁ በሚለው አሳብ ከሁሉ የበለጠ ያሳዝኑዋቸውና ያበሳጩአቸው ነበር::”

“የፈረንሳይ መንግሥት ለደጃዝማች ንጉሤ እርዳታ ሰጥቶ አገር ለመቀበል ከመስማማቱ በፊት ሌላ ውጥን ነበረው:: የአሌክሳንደርያው የኦርቶዶክስ ፓትርያርክ የሆኑት አቡነ ቄርሎስ ወደ ሃይማኖት ልጆቻቸው ወደ ኢትዮጵያ ሄደው መሄድም ባይችሉ መልእክተኛ ልከው የኢትዮጵያው ግብጻዊ ጳጳስ አቡነ ሰላማንና ቴዎድሮስን መክረው የካቶሊክ ሚሲዮናውያን በኢትዮጵያ ውስጥ እንደፈለጉ እንዲሰብኩ እንዲያስደርጉ ጠየቁ::” “

“አቡነ ቄርሎስም እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 2 ቀን 1852 በተጻፈ ደብዳቤ አቡነ ሰላማ የካቶሊክ ሚሲዮናውያንን እንዳይቃወሙ አዘዙዋቸው:: ይህን የአማላጅነት ምክንያት ያገኙት አቡነ ቄርሎስ እንደ ጁሴፕ ሁሉ እሳቸውም ለአገራቸው ለግብፅ ማሰብ ወይም ነገሩን ማዞር ጀመሩ:: ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው አንድ ዓመት ያህል ቀደም ብሎ መሐመድ ሰይድ ፓሻ የግብጽ ገዥ ሲሆን በሱዳን በኩል ያለው ሁኔታ ተለወጠ:: መሐመድ ሰይድ ፓሻ በሱዳን በኩል ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ወሰን አልፎ ስናር በጎስ መንሳ ሐልሐል ሐባብና ሌሎችም

የግብፅ ግዛት ናቸው ብሎ አወጀ:: ይህንንም ለማስፈፀም በወሰን ላይ ከኢትዮጵያ ጋር ብዙ ጦርነቶች ተደርገው ኢትዮጵያውያን እያሸነፉ የግብጽን ጦር መልሰዋል"::

"የኦርቶዶክሱ ፓትርያርክ ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ በፈረንሳይ በኩል ለአማላጅነት ሲመረጡ ይህን የወሰን ጉዳይ በሰላም ለማስጨረስ መንገድ ለማዘጋጀት እንደሚሹ ለመሐመድ ሰይድ ፓሻ አመለከቱ:: ሰይድ ፓሻም ለፈረንሳይ አማላጅነት አስመስለው ይህን ጉዳይ ለማስፈጸም ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ ጠየቃቸው:: እሳቸውም ጥያቄውን በደስታ ተቀብለው በታኅሳስ ወር 1849 ዓም ወደ ኢትዮጵያ መጡ:: ምናልባት የማያውቁ አንባቢዎች ቢኖሩ በዚያ ጊዜም ሆነ ከዚያ በፊት ለኢትዮጵያ ጳጳስ የሚመጣላት ከግብጽ አገር ግብጻዊ የሆነ ሰው በፓትርያርኩ እየተሾመ ነበር:: ስለዚህ የፓትርያርኩ የአቡነ ቄርሎስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታ ነበራቸው::"

"አቡነ ቄርሎስ እንደመጡ አጤ ቴዎድሮስና ሕዝቡ ታላቅ አቀባበል አደረጉላቸው:: ከአቀባበሉም ሥነ ሥርዓት በኋላ አቡነ ቄርሎስ ከግብጽ ገዥ ከመሐመድ ሰይድ ፓሻ ለአጤ ቴዎድሮስ የተላከውን ደብዳቤ አቀረቡ:: የመጡበትም ምክንያት በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የጠበቀ ወዳጅነት ለመመሥረት እንደሆነ በማስታወቃቸው ቴዎድሮስ በጣም ተደሰቱ:: ይህንንም የሁለቱን አገር ወዳጅነት ቴዎድሮስ በጣም እንደሚፈልጉት ገልጸው ለሰይድ ፓሻ የሚላከውን የወዳጅነት ደብዳቤ መልስ እንደሚጽፉ ገለጹላቸው:: አቡነ ቄርሎስ ለሰይድ ፓሻ የሚላከውን የወዳጅነት ደብዳቤ ቀደም ብለን ታሪካቸውን ካነበብነው ከግብፃዊው የኢትዮጵያ ጳጳስ ጋራ ለማዘጋጀት ቢፈቀድላቸው ለማዘጋጀት ፈቃደኛ መሆናቸውን ለቴዎድሮስ ገለጡ"::

"አጤ ቴዎድሮስም ጉዳዩን በቅን ልቦና ተመልክተው በቴዎድሮስ ስም የሚላከውን ደብዳቤ እንዲያዘጋጁ ፈቀዱላቸው:: በሁለቱ ጳጳሳት የተረቀቀው ደብዳቤ ለአጤ ቴዎድሮስ ቀረበ:: አጤ ቴዎድሮስም የደብዳቤውን ረቂቅ ቃሉን ሰምተው ጉዳዩን በጉባኤ ለማስፈቀድ መኳንንቱንና ሕዝቡ እንዲሰበሰብ አዘዙ:: መኳንንቱና ሕዝቡ በተሰበሰበበት ጉባኤ ለሰይድ ፓሻ የተጻፈው ደብዳቤ ተነበበ:: ደብዳቤው ባጭሩ የሚለው ÷ጥበበኞች እንዲላኩላቸው በሦስት



የቱርክ መኮንኖች የሚመሩ የግብጽ ወታደሮች በኢትዮጵያ ያሉት የእንግሊዝና የጀርመን ዜጎችም እንዲወጡ የሚልና ወሰኑንም በሰላም በፓሻው አስተሳሰብ ለመጨረስ ፈቃደኛ መሆናቸውን የሚገልጽ ነበር:: ይህም አስተሳሰብ ኢትዮጵያ ባዶዋን ሆና ከውስጥ የቱርክና የግብጽ ወታደሮች ገብተው ማንኛውንም የኃይል ሥራ ለመሥራት እንዲችሉ የታሰበ ነበር::"

"አጤ ቴዎድሮስ ደብዳቤውን ካስነበቡ በኋላ ፓትርያርኩ በቃል የነገሩአቸውን ጭምር ለተሰበሰበው ሕዝብ ነግረው የእግዚአብሔርን መንገድ ማስተማር ትታችሁ ለገዥያችሁ ለሰይድ ፓሻ አሽከር ከሆናችሁ እኔም በአገሬ ገዥያችሁ ነኝና በመንገዱ አስራችኋለሁ ብለው ፓትርያርኩንም ጳጳሱንም አብረው አሰሩአቸው:: የዚያን ዘመን ኢትዮጵያውያን ታሪክ ጸሐፊዎች የቤተ ክህነት ሰዎች በመሆናቸው ከአቡነ ቄርሎስና ከአቡነ ሰላማ መታሰር ላይ ሲደርሱ የታሰሩበት ምክንያት ብዙ ነው እያሉ ያልፉታል:: አንዳንዶችም ቴዎድሮስ ስላበዱ ነው ይላሉ:: ቴዎድሮስ ግን እንደዚያ የሚያደርጋቸው የአገር ፍቅር እንጂ እብደት አልነበረም" ሲሉ ጽፈዋል:: ሌላው አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ደግሞ የግብጾችን ሴራ አስመልክቶ እንዲህ ይላሉ::

አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ <u>ድብቁ መለኮታዊ ጥበቃ በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 130 "ፓትርያርኩ መንፈሳዊ ልጆቼን እጎበኛለሁ ብለው ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ አባታዊ ጉብኝት ለማድረግ ሲነሡና ፈቃድም ሲሰጣቸው በግብፅ ለሚገኘው ለመንበረ ፓትርያርኩ የማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ ገንዘብ ለማግኘት ነበር:: ነገር ግን እውተኛ ተልእኳቸው ይህ ሳይሆን ቀይ ባሕርን አካለው ለያዙት ለቱርኮች ምልጃ ነበር የመጡት::"

"ይህ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ለእስላም አማላጅ ሆኖ መምጣት አጤ ቴዎድሮስን አናደደና ፓትርያርኩ ወደ እስር ቤት እንዲገቡ ተደረገ:: የፓትርያርኩ እስራት በሰላማዊ ድርድር ቢቋጭም ለኢትዮጵያ የተመደቡት ጳጳስ ግን ሕዝቡ ለአጤ ቴዎድሮስ እንዳይገዛ ፓትርያርኩን አስረዋል በማለት መቀስቀሻ አደረጉበት:: ይህ የቤተ ክርስቲያን አድማ ለዘመናዊት ኢትዮጵያ ግንባታ አርቆ ያሰበውን የቴዎድሮስን ራእይ እንዲቀጭ ዙሪያውን

ከተበተበው ከመሳፍንት አድማ ጋር ተዳምሮ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል" ሲሉ ጽፈዋል።

1ኛው አጤ ቴዎድሮስ ያወጡት ሕጎችና ራእይ ለቱርክ መንግሥትና በተለይ ለግብጽ ከሊፎች እጅግ አሳሳቢ ሁኖባቸው ሳለ እነዚህ ሴረኞች የግብጽን ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስን ኢትዮጵያ ሂደው አጤ ቴዎድሮስን ሐሳብ እንዲያኮላሹ።

2ኛው ቱርኮች ከኢየሩሳሌም ይልቀቁ ማለት አይገባም፤የሚለውን ኢትዮጵያ መጥተው "ቱርኮች የእስማኤል ልጆች ናቸው። ከእስራኤልም ሊወጡ አይችሉም"ብለው ተናገሩ አጤ ቴዎድሮስ ተበሳጭተው እኔ የክርስቲያን አባት ነህ ብዬ እንጂ የቱርክ መልክተኛ መሆንህን መቼ አውቄ? ያዝና እስርልኝ ይህን የድሃ ልጅ ብለው ግራ ቀኙን ጳጳሳት አሰሩአቸው። ከዚህ ላይ አጤ ቴዎድሮስ የተናገሩት "ይህን የድሃ ልጅ" ያሉት የግብጽ ክርስቲያኖች በአገራቸው ድሃ ናቸው። እንዲያውም በካይሮ አካባቢ ሥራቸው ጥራጊ መጥረግ ብቻ ነው። ስማቸው "ዛባሌን" ይባላሉ። ነገር ግን ስደቱ አጠንክሮአቸው ከአገር የወጡት የተማሩና ከራሳቸው አልፈው ግብጽ ያሉትን ወገኖቻቸውን የሚረዱ ናቸው። ጥራጊ ጠራጊ መሆናቸውን አስመልክቶ ታሪክ ልጥቀስ።

ዴቪድ ላምብ ትርጉም ነቢዩ ኢያሱ <u>አረቦች እና እሥራኤል</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 63 "ዛባሌን ትርጉሙ ጥራጊ ሰብሳቢ ማለት ነው። ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ናቸው። የግብጽ ስድስት ሚሊዮን ክርስቲያኖች በዐረቡ ዓለም ከፍተኛውን ቁጥር የያዙ ሲሆን ከደቡብ ግብጽ ወደ ካይሮ የሄዱት። በመጨረሻውም የመካከለኛው ዘመን ዓለም ጥራጊ ሠፈሩ፤መሄጃ አጥተው እዚያው ቀሩ።

ከቤተክርስቲያኑ በቀር በመንደሩ ሌላ ምንም የለም። ስምንት መቶ ዓመት እስከሆነው የካይሮ አስደናቂ ምሽግ ድረስ ካሉት የተያያዙ መኖሪያ ቤቶች በስተቀር ትምህርት ቤት የለም" ሲሉ ጽፈዋል። ይህን ድህነታቸውን አጤ ቴዎድሮስ ያውቁ ስለነበር ነው "ይህን የድሃ ልጅ ያዝና እስርልኝ" ያሉት። እኚህ ፓትርያርክ በመታሰራቸው ምክንያት አንዳንድ የበስማም ቄሶችና ደብተሮች በአጤ ቴዎድሮስ ላይ "ጳጳሱን አሰሩ" ብለው እንደ ጠላት ተነሡባቸው።



# ምዕራፍ 2

## አጤ ቴዎድሮስና አቡነ ሰላማ

ከግብጽ የመጡትን ፓትርያርክ ከእስራት ተፈተው የቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ ገንዘብ ወርቅ ተቀብለው በሰላም ከሄዱ በኋላ አቡነ ሰላማ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ከፍተኛ ዘመቻ ጀመሩ። ለዚህ ዘመቻቸው ደግሞ ተባባሪያቸው የእኛው ኢትዮጵያውያን ካህናትና መነኮሳት፤ ደብተራ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ማጥላላት ጀመሩ። መኳንንቱም በድብቅ ወደ አቡነ ሰላማ መላላክና የአጤ ቴዎድሮስን መንግሥት ለማፍረስ አብረው መዶለት ተግባራቸው ሆነ።

አጤ ቴዎድሮስ ተበሳጭተው ሰው ሲገድሉ ጳጳሱ ዝም ይላሉ። አጤ ቴዎድሮስ "ምነው ለምን አይገዝቱኝም" ሲሉአቸው መልስ አይመልሱላቸውም። አጤ ቴዎድሮስ ላይ ቅስቀሳ ሲያደርጉ በመገኘታቸው መቅደላ አቡነ ሰላማን አሰሩአቸው። ከዚያም ከእስር ላይ ሁነው ጦር ለማዘጋጀትና ከፈረንጆች ጋር ለማምለጥ መዶለታቸውን አስመልክቶ ሊቅ ዶ/ር ብላክ ጽፎአል።

<u>የእሥራት ዘመን በአበሻ አገር</u> መጽሐፍ ገጽ 174 "ኅበዜ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ከአቡኑና ከራሳም ጋር ግንኙነት ስለነበራቸው የ1859 ክረምት ከመግባቱ በፊት መቅደላን ለመያዝ መምጣቴ ነው ሲሉ ለአቡኑ መልእክትና ጥቂት መቶ ብር ልከው አቡኑን በሚቻላቸው ሁሉ እንዲረዷቸው ስለጠየቁ አቡኑም አምባውን ለመያዝ ከመጡ በሚቻላቸው ሁሉ እንደሚረዷቸው ሙሉ ተስፋ ሰጥተው ላኩባቸው" ይሉና "አቡኑ አምባውን ለመያዝ የነበራቸው እቅድ ወዳያውኑ የሚተማመኑባቸውን ሰዎች መርጠው መሣሪያ ለእኛ ሊልኩልንና እኛም በአሽከሮቻችን ርዳታ የታሰርንበትን እግረ ሙቅ ፈትተን ለምናምናቸው አሽከሮቻችን የጦር መሣሪያ አድለን መደራጀታችንን ለአቡኑ ስናስታውቃቸው የክህነት ልብሳቸውን ለብሰውና።"

"መስቀላቸውን ይዘው 200 በሚሆኑ ቀሳውስትና ደብተራዎች ታጅበው ሊወጡና በግልጽ አጤ ቴዎድሮስንና የሚከተላቸውን ሁሉ

አውግዘውና ገዝተው አሁንም ሠራዊቱ ታማኝነቱን ለቴዎድሮስ እንዳያደርግ ለመስበክ ሲሆን እኛም ከፖርቱጋሎቹና ከታማኞቻችን ጋር ቁጥራቸው 65 ስለሚሆን አቡኑም አምሳ የሚሆኑ የታመኑ ተከታዮች ስለማያጡ ሁለት መቶ የሚሆኑ ቀሳውስትና ደብተራዎች ጭምር በማሰለፍ ሁኔታውን ግራ አጋብተን ከወዲያም በኩል የሚንቀሳቀስ ሰው ቢኖር ያለምሕረት ለመምታትና ካስፈለገም በመጀመሪያው በር ቀሳውስቱን አሰልፈን የውጩን በር እኛ የጎበዜ ሠራዊት ደርሶ አምባውን እስከ ያዘ ድረስ ለመከላከል ነበረ" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህ ወጥቶ የነበረው እቅድ በአቡነ ሰላማ እና በደጃዝማች ዋግሹም ጎበዜ ገብረ መድኅን እና በአውሮፓውያን ሰዎች ነበር:: ሁኔታው ግን ሳይፈጸም ቀርቷል:: ይህ ከሆነ በኋላ ደግሞ አጤ ምኒልክ ከመቅደላ እንዳመለጡ መጥተው እንዲያወጡአቸው ልከውባቸዋል:: አጤ ምኒልክም ለመንግሥ ጳጳስ አስፈላጊ መሆኑን ያውቃሉና እንኳን ተጠይቀው ቀርቶ ጠይቀውም መምጣት ነበረባቸው:: ከሸዋ ወሎ መቅደላ መጡና ሲያጣሩ ቀድመው አቡነ ሰላማ አርፈው በመድረሳቸው ወደ መጡበት ሸዋ ተመልሰዋል:: ዛሬ እነ ደጃዝማች ዘውዴና የሕወሓት ደራስያን "አጤ ምኒልክ እንግሊዞችን መርተው መጥተዋል" የሚሉት አቡነ ሰላማን ለመውሰድ መምጣታቸውን ባለመረዳት ነው::

<u>የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 130 "አጤ ቴዎድሮስ ጳጳሱን አቡነ ሰላማን ተጣልቶት መቅደላ አምባ አግብቶ የቁም እስር አድርጎት አገዛኛ ተቀምጦ ነበር:: አቡነ ሰላማ ግን እባክህ አውጣኝ ታደገኝ ብሎ ሸዋ ከአቤቶ ምኒልክ ዘንድ ላከ:: አቤቶ ምኒልክም አቡነ ሰላማን ከመቅደላ ሊአወጣ ብልሃት ሲፈልግ ከመሀል አቡነ ሰላማ ሟልሳዊ ታሞ በ1860 ዓም በዘመነ ዮሐንስ ጥቅምት 15 ቀን ዓርብ በ9 ሰዓት ሞተ" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህን ታሪክ ሌሎችም ደራስያን ይስማሙበታል:: እንግዲህ አቡነ ሰላማ የአጤ ቴዎድሮስን ዓላማ ካፈረሱት አንዱ ናቸው:: አባቶቻችን ሲተርቱ "ሲጠባ የለመደ ጥጃ ሲያዙት ያጓጉራል" እንደሚባለው ስንፍና የለመዱ ካህናትና ደብተራ የነዚህን የኢትዮጵያን ምቀኞች ጳጳሳት ምክር እየሰማ አጤ ቴዎድሮስን ማናደድና ማስቸገር ተግባራቸው ሆነ::"



"እንዲያውም ይህን አስመልክቶ በወቅቱ ታዋቂ የነበሩት መምህር አካለ ወልድ "ይብላኝ ለደብተራ፣ይብላኝ ለወልደ ማርያም "በማለት ተቀኝተውበታል:: ይህ ደብተራና የበስማም ቂስ ዛሬም ድረስ ግብራችን ቀነስ ብሎ ሲያሸሚጥጥ ይውላል:: ሳይገባው የግብጽ አሽከር ሁኖአል:: ለዚህስ የዛሬው ብፁዕ ወጣያት አቡነ ጳውሎስም አንዱ ናቸው:: ሉስ እንጀለስ ሳሉ አባ ሽኖዳ ሲመጡ እርሳቸው የሚያከብሯቸውን ምእመናን አስከትለው የአሽከርነት አቀባበል አድርገውላቸዋል:: ዛሬ ደግሞ ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከሆኑ ወዲህ ዴር ሡልጣን ገዳምን ሊያስረክቡ እየተነጋገሩ ናቸው ይባላል:: አይ የደብተራ ልጅ ዛሬም ከክህደት አልተመለሱም::

የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከግብጾች ለማላቀቅ ቅድሚያ የተነሡት የዛጉዌ ነገሥታት በተለይ ንጉሠ ነገሥት አጤ ሀርቤ ሲሆኑ ወዲያው ደግሞ በ1261 ዓም ላይ አጤ ይኩኖ አምላክ ቀዳማዊ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ጳድቁ ጳጳስ እንዲሾሙ አድርገዋል:: ከዚያም በኋላ እርሳቸው ንቡራን ጵዶችን ሹመዋል::

ኋላም አጤ ቴዎድሮስ በማሰራቸው ምክንያት ኢትዮጵያውያን ከግብጻውያኑ ለመላቀቅ ጥረት ማድረግ ተጀመረ:: አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ግንቦት 10 ቀን 1860 ዓም ሲነግሡ በገዳም አበምኔት ተቀብተው ነገሡ:: አጤ ዮሐንስ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አፍቃሪ ከመሆናቸው የተነሣ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንዲሾምላቸው በመጠየቃቸው ምክንያት 4 ጳጳሳት ተላከላቸው::

አጤ ምኒልክ በሃይማኖት በኩል ብዙም የጎላ ተግባር አልፈጸሙም:: የልጅ ልጃቸው አጤ ልጅ ኢያሱ ሕፃን ከመሆናቸው የመጣ ጳጳሳትን አስመልክቶ የጣሩት አልነበረም:: ነገር ግን ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ 5 ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንዲሾሙ አድርገዋል:: ከነዚህም የበላይ ሊቀ ጳጳስ ሁነው የመጡት ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ ጣልያን አገራችንን ስትወር ኢትዮጵያን ትተው ወደ አገራቸው ሄዱት ናቸው:: ኢትዮጵያውያን ተወላጆች አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል ከአርበኛው ጋር ሁነው ሲታገሉ ቢገደሉም ሌሎች ግን ከጣልያን ውስጥ በነበሩ መኳንንቶች ርዳታ ቤተ ክርስቲያንን ምእመናንን ለማገልገል አቡነ አብርሃምን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አድርገው መረጡ::

አባ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ <u>የቋሚ ምስክርነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 79 "ጠላት ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ብዙ ችግር ፈጥሮባቸው ነበር፤ማለት 2ቱን ገደላቸው አንደኛውን አጋዛቸው:: አቡነ አብርሃም ብቻ እግዚአብሔር አድኗቸው በክብር እንዲገኙ ስላደረጋቸው ጣሊያን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ እንዲሆኑና ጳጳሳት እንዲሾሙ አድርጓል:: ስለዚህም ብዙ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ሹመዋል:: እርሳቸው በክብር ሲያርፉ አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳስ ሁነው አሁንም እርሳቸው ብዙ ጳጳሳት ሹመው መሥራት ሲጀምሩ ጣሊያን ድል ሆነና" ሲሉ ጽፈዋል::

በ1933 ዓም ኢትዮጵያ ከወራሪ ነጻ ስትወጣ ኢትዮጵያውያን ግብጻውያንን ማየት አይፈልጉም ነበር:: በዚህ ምክንያት በተደረገው ድርድር ቀደም ሲል ተሹመው የመጡት ግብፃዊ አቡን እስኪሞቱ ድረስ መጠበቅ እንዳለብን ተስማሙ:: አቡነ ቄርሎስ በዕድሜ መግፋት ዐረፉ:: ከዚያም በኋላ ኢትዮጵያዊው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሁነው ተሾሙ:: እርሳቸው ሲያርፉ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሁነው ተሾሙ:: እርሳቸውን ጳጳሳቱ ከደርግ ጋር ተመሣጥረው እንዲታሰሩና እንዲገደሉ አደረጉ:: ከዚያም ገዳማዊው አባ መላኩ በደርግ መንግሥት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተብለው ተሾሙ::

እርሳቸው ሲያርፉ አቡነ መርቆሬዎስ ተሾሙ:: የደርግ መንግሥት ሲወድቅ ከደርግ ጋር አብሮ የሠራው ሁሉ እንዲወድቅ በመደረጉ ከቦታው እንዲነሡ ብዙ ውስብስብ ሴራ ተካሀዶ ከሥልጣናቸው ተነሡ:: እርሳቸው አዲስ አበባ እያሉ አቡነ ጳውሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሁነው ተሾሙ:: የሚገርመው ነገር ደግሞ እበላ ባይ ደራሲ መጽሐፍ ጽፈው "አቡነ መርቆሬዎስ መንጋቸውን በትነው ተሰደዱ" ይላሉ::

ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ ሐምሌ 5 ቀን 1984 ዓም ሲሾሙ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አዲስ አበባ ነበሩ:: ከዚህ በኋላ ነው በአቶ ክንፈ ገብረመድኅንና በአቶ አባይ ፀሐይ፤ውትወታ በጥር 1985 ዓም ትተው የተሰደዱ:: በሌሎች ፀሐፊዎችም ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስን ለማስደሰት ሲሉ ብዙ ተጽፏል፡ብዙም ተተርኳል፤በምስል ድምጽ በንባብ ተቀነባብሮ ዲቪዲ ተሰራጭቷል::



ጸሐፊ ተወልደ ገ/ጊዮርጊስ <u>ሰማዕት ዘእንበል ደም</u> የተባለ የምስል ድምጽ ክር በ2000 ዓም ወጥቷል:: ይህ የምስል ቅንብር የዲቪዲ ክር የሚያሳየው ታሪክ ቢኖር ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስን ለውርደት የሚዳርግ ነው:: ምክንያቱም ብዙ ስህተት አለበት:: ስህተቱ "ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በ1967 ዓም መጨረሻ ላይ ወደ ኢትዮጵ እንዲመጡ ጠሩአቸው:: አባ ገብረ መድኅንም የዶክትሬት ዲግሪ ትምህርታቸውን አቋርጠው ጥሪውን ተቀብለው ወደ ኢትዮጵያ መጡ" ይላል:: ሌላም ሌላ ብዙ ስህተት አለበት:: ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ ከ1967 ዓም በፊት አዲስ አበባ ገብተው ሥራ መያዛቸውን ደግሞ የሕይወት ታሪካቸው መጽሐፍ ያብራራል::

<u>ዜና መዋዕል ዘብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ</u> ከተባለው መጽሐፍ ገጽ 60 "በአባ ገብረ መድኅን ገብረ ዮሐንስ ሥራ ከፍተኛ እምነት የሚጥሉት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መጀመሪያ መስከረም 6 ቀን 1967 ዓም የኮሚሽኑ ዋና ጸሐፊ አድርገው ሲመድቧቸው በጥቂት ጊዜ ውስጥ ለኮሚሽኑ ባሳዩት እንቅስቃሴና መረጋጋት አከታትለው የኮሚሽኑ ተ/ሥራ አስኪያጅ አድርገው በራሳቸው ፊርማ መድበው ሾመዋቸዋል" ይላል:: የሚጽፉት ከልባቸው ስላላይደል ለእበላ የተሰለፉ በመሆኑ ግድም አይሰጡትም::

• <u>የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ አጭር የሕይወት ታሪክ</u> የተባለች መጣጥፍ ገጽ 23 "በ1967 ዓም ቅዱስነታቸው ከአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ እውቅናቸውና አገልግሎታቸው የተነሣ ከሌሎች ሁለት አባቶች ጋር ለጵጵስና ተመርጠው በሁለተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አንብሮተ እድ ጵጵስና ተሹመዋል" ይላል::

እርሳቸው ጵጵስና የተሾሙት መስከረም 16 ቀን 1968 ዓም ሲሆን ደርግ ያሰራቸው መስከረም 28 ቀን 1968 ዓም ነው:: ደራስያኑ ዝም ብለው ቅዱስ ቢያደርጓቸውም ታሪክና የባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ ደም እኮ በእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን አልደረቀም:: ይህ ብቻም አይደለም በ2001 ዓም ጳጳሳትን አስደብድበዋል:: ቤተ ክህነትን

አዋርደዋል:: በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በእናት አብያተ ክርስቲያን ያልተፈጸመ በደል ፈጽመዋል::

በሐምሌ 2002 ዓም ሐውልታቸው በቤተ ክርስቲያን ግቢ ተሠርቶ እንዲተከል ሁኖአል:: በሀገራችን ኢትዮጵያ ምን ዓይነት አባት ነው ሐውልት የሚሠራለት? ኢትዮጵያ በፋሽስት በተወረረች ጊዜ ለሃይማኖታቸው ሲሉ ሰማዕት የሆኑ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ለእርሳቸው ሐውልት ተሠርቷል:: የተሠራው ሐውልት ተመተው ከወደቁበት ቦታ ላይ ሲሆን ሌላው ሰማዕት አቡነ ሚካኤል ጎሬ ላይ በተገደሉበት ቦታ ላይ ሊሠራ ተብሎ እስካሁን አልተሠራም::

እንዲሁም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በደብረ ጽጌ ሃይማኖት ካረፉ በኋላ ተሠርቷል:: ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በባዶ እግራቸው እየሄዱ ለቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ያደረጉ አባት ካረፉ በኋላ በቅድሥት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከተቀበሩበት ቦታ ላይ ሐውልት ተሠርቷል:: እኚህ አባት ለቤተ ክርስቲያን አልሠሩም እንዳይሉ ብፁዕ ወጣያት አቡነ ጳውሎስ ቡራኬ የሰጡበት መጽሐፍ እንዲህ ይነበባል::

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u> ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓም በተባለው መጽሐፍ ገጽ 26 "የወላይታ ሐዋርያ የነበሩት አባ መልአኩ ወልደ ሚካኤል ሰኔ 30 ቀን 1968 ዓም በኢትዮጵያ ምእመናንና ካህናት ተመርጠው ሐምሌ 11 ቀን 1968 ዓም እሑድ በመንበረ ፀባያት ቅድሥት ሥላሴ ካቴድራል የኤጲስ ቆጶስነት ሥርዓተ ሢመት ተፈጽሞላቸው ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተባሉ::"

"ነሐሴ 23 ቀን 1968 ዓም እሑድ የኢትዮጵያ ሦስተኛ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ" ካለ በኋላ የብፁዕ አቡነ ጳውሎስን ተግባር ደርድሮ ሲጨርስ መልሶ በገጽ 27 ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሦስተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ከተሾሙ በኋላ በተከታታይ 28 ኤጲስ ቆጶሳትንና ሊቃነ ጳጳሳትን ሾመዋል:: የቤተ ክርስቲያቱን ሐዋርያት በመላ ኢትዮጵያ በዓመት ሁለት ጊዜ እየላኩና እያዘመቱ የሰበካ ጉባኤ የስብከተ ወንጌል፤የሰንበት ት/ቤት ብሔራዊውንና መንፈሳዊውን የአብነት ት/ቤት እንዲጠናከር፤ልማት



እንዲለማ፤የካህናት ማሠልጠኛዎች እንዲደራጁ ከሁሉም የበለጠ ጥረት አድርገው ተሳክቶላቸዋል" ሲል ጽፎአል:: ሐውልት የተሠራላቸው አባቶች ቅድሚያ እነሱ በሕይወት እያሉ አይደለም::

እንዲሁም በደርግ የተገደሉት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ባሠሩት ጎፋ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሐውልት ተሠርቷል:: ብፁዕ ወጣያት አቡነ ጳውሎስ ግን እርሳቸው እያሉ ቁመው የመረቁት ሐውልት ተሠራ:: ከእርሳቸው ጋር የከበቡ ሁሉም ወደ ጥፋት እንዲያዘነብሉ ከመገፋፋት በቀር "ትክክል አይደሉም" ብሎ በቆራጥነት የተነሣ ጳጳስ የለም:: ለአንዱ ጋዜጣ አንድ ሲል በብር ሲያጅሉት "ይደልዎ" ይላል::

ሐውልቱ መሠራቱ ሕገ ቤተ ክርስቲያን አይፈቅድም ብለው ሁሉም አባቶች አብረው አልቆሙም:: ቢቆሙ ኑሮ ሕዝበ ክርስቲያኑ አብሮአቸው ይቆም ነበር:: ነገር ግን ጳጳሳቱ ሁሉም ገንዘብ ካገኘን ምን ቸገረን ብለዋል:: በሲኖዶስ ምስላቸውና ጣዖቱ ሊነሣ ከተስማሙ በኋላ እነሆ ዛሬ ድረስ አልተነሣም:: ምክንያቱም እያንዳንዱ ጳጳሳት ጠቀም ያለ ብር ለየብቻ ተሰጥቶአቸዋል:: ዛሬ በአዲስ አበባ ጳጳስ ሆን ማለት ገንዘብ ጫኝ ማለት ነው:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት አባታቸውን የበሉ ናቸው:: ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን አስበልተዋልና::

ተገኘ ብልሐቱ <u>ፍሬ አልባ በለሶች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 51 "ጳጳሳት የተወሰኑት ራሳቸው አቡነ ቴዎፍሎስ የሾሚቸው ናቸው:: በዚህም መምህሩን ካስገደለው ከይሁዳ ጋር ይመሳሰላሉ፤ይሁዳ ከካህናት አለቆች ክርስቶስን ለማስያዝ ገንዘብ ከተቀበለ በኋላ የነበሬውን ሐሳቡን ከዚያችም ሰዓት ጀምሮ አሳልፎ ለመስጠት ምቹ ጊዜ ይሻ ነበር በማለት ወንጌላዊው መዝግቧል ማቴ26፤16 ይሁዳ የገንዘብ ፍቅር በልቡ ስላደረበት::"

"ገንዘቡን ተቀብሎ ምቹ ጊዜ ፈልጎ መምህሩን ለገዳዮቹ አሳልፎ ሰጠ እነዚህም የሹመት ፍቅር በልቦናቸው ስላደረ ሳይሳካላቸው የቆዩ በመሆኑ ምቹ ጊዜ ሲያገኙ አባታቸውንና መምህራቸውን ለገዳይ የደርግ መንግሥት አሳልፈው ሰጡ አሁን እነዚህ ከይሁዳ የሚለዩበት ምን ነገር አለ? እነዚህ ሰዎች ክርስቶስን ቢያገኙት አይገድሉትም

ብሎ ማሰብ ይቻላልን? እኔ በበኩሌ አይገድሉትም ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው የሚመስለኝ::"

በፍትሐ ነገሥት ሹመትን መፈለግ ሰይጣናዊት በሽታ ናት ተብሎ እንደተጻፈው በዚች ሰይጣናዊት በሽታ ስለተጠመዱ ክርስቶስንም ቢያገኙት አይተውትም ነፍስ ገዳዮች የሰይጣን ልጆች ሆኑ ደግሞ ጌታችን ልክ እንደነዚህ ያሉ ነፍስ ገዳዮች ሊገድሉት እንደሚፈልጉ ባወቀ ጊዜ እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበረ ብሎ የነዚህን የሰይጣን ልጅነት አስቀድመው በነበሩት ነፍስ ገዳዮች ሥራ ተናግሮታል::

ዮሐ 8፤44 እና እነዚህ አስቀድመው ባይገድሉትና በነዚህ ጊዜ እዚህ ቢገኝ ኑሮ እነዚህ ይገድሉት ነበር:: ጌታ እንዳለውም የሚሸፍራቸው ሰይጣን ስለሆነ እርሱ እንደሆነ በየዘመኑ ሥራ ማሠራት ያውቅበታል:: በነዚያ አድሮ ጌታን አስገደለ በነዚህ አድሮ ደግሞ አቡነ ቴዎፍሎስን አስገደለ በአቡነ ቴዎፍሎስ ቦታ ጌታ ቢገኝ አያስገድሉትም ብሎ ማሰብ ሞኝነት ይሆናል" ሲሉ ጽፈዋል::

ቃለ አብ <u>ይድረስ ለአባ ጳውሎስ ቄሣር</u> በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 7 "ግብዙ ንጉሥ ናቡከደነፆር በንዋያ ቅድሳቱ ላይ ከሚከበርባቸውና እርሱን ጨምሮ ዓለሙን ሁሉ ፈጥሮ ከሚገዛው ከኃያሉ አምላክ ከልዑል እግዚአብሔር ይልቅ በዙሪያው ሆነው ጠጅ እየቀዱ፤ጮማ እየጎረዱ ንጉሥ ሆይ!ሺህ ዓመት ንገሥ በሚለው የማታለያ ነጠላ ዜማቸው መዋቲ መሆኑን እንዲረሳ::"

"እያደነዘዙ ከርሳቸውን የሚሞሉ ሆዳም ተከታዮቹንና አብረውት በኃጢአት የሚወድቁ ዕቁባቶቹን ለማስደሰት ሲል ቅዱስ እግዚአብሔር በቅድስና ይገለገልባቸው ዘንድ የመረጣቸውንና ያከበራቸውን ንዋያተ ቅድሳት የጠጅ መጠጫ፤የሰው መላገጫ በማድረጉ ምክንያት በፍትሐ አምላክ ዘመንህ ተቆረጠ፤በመድሎተ አምላክ ተመዝነህ ከገለባ ይልቅ ቀልለህ ተገኘህ፤ክብርህም ለሌላ አልፎ ተሰጠ፤እንደተባለ ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል::"

"አሁንም በዘመናችን በክርስቶስና ደሙን ባፈሰሰባቸው ንጹሑን አምላክ በትሕትና በማገልገል ፈንታ ድሆች ለጽድቅ ብለው



ከራሳቸውና ከልጆቻቸው ጉሮሮ እየነጠቁ ለቤተ ክርስቲያን በሚመጸውቱት የእንባ ገንዘብ ብዙ ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ጥይት የማይበሳው መኪና መግዛትዎ (ማስገዛትዎ) ሥዕልዎን በውድ ዋጋ አሠርተው በአብያተ ክርስቲያኑ ማስቀምዎ አንሶ ክርስቶስ በደሙ ዋጅቶ ለቅድስና ተግባር በመረጣትና ባከበራት በተቀደሰችው የእግዚአብሔር አደባባይ ቄሣራዊ ሐውልትዎን በማቆምዎና እግዚአብሔር በደሙ በቀደሳቸው ካህናት ንዋየ ቅድሳት ተጠቅመው ይህንኑ ቄሣራዊ ሐውልት መመረቅዎ ለአሕዛቡ ንጉሥ ለናቡከደነፆር የተላለፈው ማኔ፤ቴቄል፤ፋሬስ የሚለው መልእክት ይመለከተዎታል" ሲሉ ጽፈዋል::

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ <u>ኢትዮጵያ በሦስት ፍካሬዎች</u> በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 8 "አሳፋሪና አሳዛኝ ክስተት የሚያሳየው ሃይማኖቱን ጠብቀው ለማስጠበቅ በቦታው ላይ የተሰየሙት ጳጳሳት ዓለም በግልጽ የሚያውቀውን ይኸን ያክል ትልቅ በኦርቶዶክስና በሮማ ካቶሊክ መካከል ያለ ልዩነት አለማወቃቸውና ለማወቅም ሆነ ለመታረምም አለመሞከራቸው ነው:: ቤተ ክርስቲያናችን እምነቱን ለማስተማርና ለማሳየት ከምትጠቀምባቸው የተለያዩ መንገዶች መካከል ሥዕላዊ መግለጫ አንዱና ዋነኛ ቦታን ይይዛል::"

"ከነዚህም አንዱ ጳጳሳት ሲሰየሙ የሚሰጣቸው አርዌ ብርት የሚባለው ብረት ነው:: እብረቱ ጫፍ ላይ የሚናደፉ እባቦች በመካከላቸው ወደ ተሰቀለው ክርስቶስ አፋቸውን ከፍተው ጥርሳቸውን አግጥጠው ምላሳቸውን ጎልጉለው ይታያሉ::"

"በስተጀርባቸው ያለውን ነገረ መለኮቱን ያልተረዳ በሊቃውንቱ እግረ ሥር ተቀርጾ በምናኔው ሰርጾ ያላደገ፤ጳጳስ ከሆነ፤በሚጨብጠው አርዌ ብርት ላይ የተቀመጡትን እባቦች ሰይጣን መጠቀሚያ ሰረገላው ሊያደርጋቸው ይችላል ይሉ ነበር:: ዛሬ በዘመናችን ያሉት ፓትርያርክና አርዌ ብርቱን ከጨበጡት በዛ ያሉት ይህን መስለው ተገኙ:: አቡነ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ሆነው አሁን በዘመናቸው ለሚካሄደው የፖለቲካ መዋቅር መሣሪያ የሆኑ ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል::

አንባብያን አጤ ቴዎድሮስና አቡነ ጳውሎስ ምን አገናኛቸው ትሉ ይሆናል:: ትክክል ነው:: ነገር ግን የአቡነ ሰላማን ግብጻዊ ተንኮል

ዛሬም እኛ አባቶች ያልተዉት መሆናቸውን ለመግለጽ ስለፈለኩኝ ነው:: ሌላው ይቅርና በግፍ የተሰደዱት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አይዞዎት የሚላቸው ያጡ መሆናቸውን የሚያውቅ ይኖር ይሆን? ምነው ዛሬስ በሃይማኖት አባቶች በዛ? ከማን ግብረ ገብነትን አይተን እኛ ምእመናን ግብረገብ እንሁን?

ጳጳሳቱ አባታቸውን የሚበሉ? በ1968 ዓም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ያስበሉ ጳጳሳትና ካህናት ተስማምተው ነው እኮ? በ1983 ዓም መጨረሻ ጀምሮ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን እንዲባረሩ ያስደረጉ ጳጳሳቱ አይደሉም? ታዲያ ከማንኛው አባት ትሕትና ተምረን እኛ ልጆቻቸው ትሑት እንሁን? ለዚህ ነበር አጤ ቴዎድሮስን የመሰለ ጀግና የሚያስፈልገው ምነው ዘንድሮ የሚመጡ በሆነ! ስንቱን አባ ሰላማ ዓይነት መቅደላ አስሮ ያስቀምጠው ነበር?

<u>ምንኩስና በኢትዮጵያ ዛሬና ትናንት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 99 "ትልቁ ጥፋታቸው በአበው መንገድ እንዳልተጓዙ እያወቁ፤በስህተት ጎዳና እየተራመዱና ራሳቸውን አታለው ሌላውን እያሳሳቱ እንደሚገኙ በውስጣቸው እያመኑ፤ኃጢአታቸውን ንስሐ ገብተው ለማስወገድ አለመሞከራቸው ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

መነኩሴ ሲለወጥ ጳጳስ የሆኑት ሁሉ ተሳስተው ሌላው ሕዝብ እንዲሳሳት ያደረጉ እነዚህ ጳጳሳት ናቸው:: የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀደም በግብጽ ጳጳሳት ዛሬ ደግሞ በግብር ልጆቻቸው እየታመሰች ትገኛለች::

በተለይ በስደቱ ዓለም ኢትዮጵያውያን ተካሰው ፍርድ ቤት መሄድ የጀመሩ በጳጳሳት ምክንያት ነው:: ኢትዮጵያውያን የምንታወቀው በሀቀኝነትና በጀግንነት መሆኑን ብዛት ያላቸው የታሪክ መጻሕፍት ያትታሉ:: በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ የምንታወቅ ተካስን ፍርድ ቤት በመሄዳችን ነው:: ለዚህም ግንባር ቀደሙ በ1980 ዓም ሎስ አንጀለስ በቤተ ክርስቲያን ተከሰው የቀረቡ የዛሬው ብፁዕ ወጣያት አቡነ ጳውሎስ ናቸው::

ዶ/ር ጌታቸው መካሻ <u>ፍኖተ ተዋሕዶ</u> መስከረም 1 ቀን 1999 ዓም ገጽ 31 "ጳኛው (ጥቁር ነበር) በእውነቱ በጣም ጨዋ ሰው ነበር:: እናም ወቀሰን:: እናንተ ኢትዮጵያውያን ለሁላችን አርአያ መሆን



ሲገባችሁ እንዴት እርስ በርስ ትካሰሳላችሁ ብሎ በጣም ወቀሰን" ሲሉ ጽፈዋል:: ለዚህ በታሪክ የመጀመሪያው በውጭ አገር ተከሰው ፍርድ ቤት የቀረቡት ብፁዕ ወጣያት አቡነ ጳውሎስ ናቸው:: መከሰሳቸውን የጦቢያ መጽሔት አዘጋጅ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ነሐሴ ላይ መልሰውለታል::

ብ.አ.ጳውሎስ <u>ጦቢያ መጽሔት</u> ነሐሴ 1984 ዓም ገጽ 6 "ውጭ አገር በነበሩበት ወቅት ክስ ነበረበዎት?" ብሎ ለጠየቃቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ "በጠበቃዬ ነፃ መሆኔን ተነግሮኛል" ሲሉ መልሰዋል::

ስለዚህ ብፁዕ ወጣያት አቡነ ጳውሎስ በታሪክ የመጀመሪያ ተከሳሽ ጳጳስ ናቸው:: ያውም በውጭ አገር? ይህን ልጆቻቸው ያውቁ ይሆን?አገር ቤት ገብተው ቅዱስ የሆነውን ማዕረግ በኃይል ከያዙት በኋላ ደግሞ ባሕታዊ ፈቃደ ሥላሴ ከእግራቸው ሥር ሲወድቁና ሌሎች ጠንካራ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በስደቱ ዓለም በእርሳቸው ምክንያት ተሰደው መንከራተታቸው ለ3ኛው ሽህ መግብያ ታሪክ ዘግቦት ይገኛል::

አቡነ ሰላማ አጤ ቴዎድሮስን ቢያስቸግሯቸው መቅደላ አሰሯቸው:: ይህን ያደረጉት ጳጳሱ የኢትዮጵያን አንድነት እንዳይከበር በመጣራቸው ምክንያት ነበር:: የግብር ልጆቻቸውን ካህናቱንና ደብተራውን አንድ ባንድ ቀጥተዋቸዋል:: ዛሬም የአጤ ቴዎድሮስን ዓይነት ቅጣት ሳይሆን ሻል ባለ መልኩ የሚቀጣቸው ካልተገኘ የኢትዮጵያ አንድነትና ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሊከበሩ አይችሉም:: እጅግ በጣም አስቸግረዋል:: የአቡነ ሰላማ የግብር ልጆች ጠንካራ መሪ ካልያዛቸው በቀር አስቸጋሪዎች ናቸው::

አንባብያን ከዚህ ከፍ ብሎ በጠቀስኩት ምዕራፍ ጥፋቱን እየዘረዘርኩኝ የጻፍኩበት መሆኑ አይዘነጋም:: ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ከተሾሙ ጀምሮ ብዙ ለውጦች ታይተዋል:: ይህን ደግሞ ልናሠምርበት ይገባል:: ከዚህ ምዕራፍ ላይ ይህን አድርገዋል ብዬ ደህናውን ሥራቸውን ባልገልጸውም ቅሉ ከጥፋቱ ጋር ልማቱ አንድ ባይሆንም ብዙ የተሠሩ ሥራዎች መኖራቸውን አላጣሁትም::

# ምዕራፍ 3

## ቤተ ክህነትና አጤ ቴዎድሮስ!

“ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከአንዲት ሴት በቀር ሌላ አግብቶ ቢገኝ ሀብቱን እንዳለ ለመጀመሪያ ሚስቱ ጥሎ እንዲወጣና ርስትም ሆነ ሹመት እንዳይሰጠው”የሚለውን ሕግ አጤ ቴዎድሮስ ከማወጃቸው ይልቅ ቤተ ክርስቲያን ማስተማር ነበረባት። በእርግጥ በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ካለው ጀምረን ስንቆጥር ቤተ ክህነቱ ለ1500 ዓመታት ከግብፅ ተገዝተው የሚመጡት ጳጳሳት አላሠራ እያሉ መኖራቸው ጠፍቶኝ ሳይሆን የእኛ አባቶችም አስትዋጽኦ ማድረጋቸው ሊደበቅ አይገባም።

ግብጾች በኢትዮጵያ ይመረታል። ታዲያ አበላሉ አስቸጋሪ ነው። ግብጦ ቅድሚያ ተቆልቶ ከረምት ቅጠል ለብሶ ደንጊያ በበላዩ ተደርድሮበት ከወራጁ ውሃ ላይ ለሦስት ቀን ያህል ከቆየ በኋላ መርዙ ይለቃል። ይህን ሲበሉት ለሆድ መድኃኒት ነው። መርዙ ሳይለቅ ግብጦ አገኘሁ ብሎ ትንሽ ቢበላ እስከ መሞት ያደርሳል። ግብፆችን ለኢትዮጵያ እንደ ግብጦ መርዛቸው ከፍተኛ ጠንቅ ነው።

አጤ ቴዎድሮስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስተዳደራዊ ለውጥ ለማምጣት ካላቸው ፍላጎት የተነሣ አገልጋይ ካህናት 5 ብቻ እንዲሆኑ የቤተ ክርስቲያን የመሬት ይዞታ እንዲቀነስ ማድረጋቸው ከካህናቱ ጋር እንዲጣሉ ምክንያት ሆኗል። ኢትዮጵያን ሊያስተዳድሩ የሚነሡ ሁሉ ቅድሚያ ሃይማኖታቸውን ማስጠበቅ ይወዱ ነበር። ይህ ሊሆንበት የቻለው አገሪቱ ስትመሠረት ጀምሮ ሃይማኖት ስለነበራት ነው።

1ኛ ሕገ ልቡና ከ982 ዓመተ ዓለም ወዲህ ሕገ ኦሪትን ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ ሕገ ወንጌልን ተቀብላ የነበረች አገር ስትሆን በ330 ዓም የመንግሥት ሃይማኖት ክርስትና ሲሆን ከዚያም እስልምናን እንዲያውም የነቢዩ ሙሐመድን ቤተሰቦች ያስተናገደች ቅዱስ ቁራንንም በጎን የተቀበለች አገር ናት።



የአሪት አማኝ ንግሥት ዮዲት ከ842 ዓም እስከ 882 ዓም ለ40 ዓመት ገዝተዋል። ከ1517 ዓም ጀምረው የተዋጉት በ1519 ዓም ግራኝ አህመድ አጤ ልብነ ድንግልን ከወጉ በኋላ ለ15 ዓመት በኢትዮጵያ እስልምና የመንግሥት ሃይማኖት እንዲሆን ጥረዋል። አጤ ሱስንዮስ ከ1607-1623 ዓም ሲነግሡ ራሳቸው ካቶሊክ ሁነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ካቶሊክ እንዲሆን አውጀዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የካቶሊክን ሃይማኖት አንቀበልም በማለቱ ምክንያት ብዙ ደም ፈሷል። ይህ ሁሉ ሲሆን ቤተ ክህነቱን ወደ ሥልጣን ወንበር የተቆናጠጠው ሁሉ መጠቀሚያ ሲያደርገው ኑሮአል። እንኳን ቀደም ዛሬም ቢሆን ቤተ ክህነቱን ሆነ ቤተ መስጊዱን የራሳቸው አድርገው ምእመናኑን የሚደፈጥጡ ጥቅመኞችን የሚሾሙ የመንግሥት ወንበር ላይ ቁጢጥ የሚሉ ናቸው። አጤ ቴዎድሮስ ግን ከሌሎች ሁሉ ልይት ያሉ ነበሩ። ቀደም በኢትዮጵያ ብዙ ስህተት ይፈጸም ነበር።

1ኛ የሰው ልጅ እንደ እቃ ሲሸጥ ቤት ክርስቲያኗ ተቃውሞ አለማሰማቷ!
2ኛ ቤተ ክርስቲያኗን ደፍሮ ተሳስታለች የሚል አለመኖሩ!
3ኛ ካህናቱ በወንጌል ተምሮ ማስተማር ተግባር አለመጠንከራቸው!
4ኛ ከ24 ካህናት በላይ ላንድ ቤተ ክርስቲያን ሲተራመስ መዋሉ!
5ኛ ቤተ ክርስቲያኒቱ የሕዝቡን መሬት በቁጥጥሯ ሥር ማዋሏ!
6ኛ ዓለማዊ ባለሥልጣኖች ብዙ ሚስት ሲኖራቸው ቤተ ክርስቲያን አለመገሰጿ!
7ኛ በክርስቲያኑ ሕዝብ ላይ ጥንቆላ በዝቶ እያዩ አለማስተማራቸው! ሌላም።

ከዚህ ከፍ ተብሎ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች አጤ ቴዎድሮስ በጥሞና ተመለከቱ፤ ራሳቸው የነበሩአቸውን ቁባቶች አሰናበቱና ከእቴጌ ተዋቡች አሊ ጋር ሥጋ ወደሙ ተቀበሉ። ከዚህ በኋላ ከእርሳቸው ጋር የነበሩት መኳንንቶች እርሳቸውን መከተል ጀመሩ።

24 ካህናት ሁኖ ሲንገዋለል ይውል የነበረውን በ2 ቄስና በ3 ዲያቆን እንዲቀደስ፤ መሬት የመንግሥት እንጂ የቤተ ክርስቲያን አይሆንም ብለው አዋጅ ሲያወጡ ይህ የበስማም ቄስ ሁላ ይንጫጫ ጀመር።

“ድግ ደግላይ ወገቡን ሰባቂ”ሠርቶ ይብላ በማለት ሲነሡበት ይህ ደብተራ ሁላ ተሰብስቦ ሌላ መላ አመጣ። ምናልባት መነኮሳቱ ቢያናግሯቸው ይተዉ ይሆናል በማለት ጢማቸውን ያንዠረገጉ

ፊታቸው ሎሚ የሚመስል መነኮሳትን አስመጥተው "ጃንሆን ትክክል አይደሉም" ብለው ሳይጨርሱ አጤ ቴዎድሮስ" ጌታችን አንድ ወንድ ላንድ ሴት ብሎ አስተማረ እንጂ መንኩሱ ብሎ የት ላይ አስተምሯል::

"ሰነፍ ሠርተህ ብላ ይህን መደበቂያ አድርገህ ልትኖር አስበህ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ሚስት አታግባ አይልም:: ሚስትህን አክብርና ተከባብረህ ኑር አንድ ወንድ ባንዲት ሴት ኑር ይላል እንጂ? እንግዲያ የሰው ልጅ እንደከብት ሲሸጥ ለምን አታስተምሩም ነበር? ሌላው ይቅር ፋቅራና ጠንቋይ ተስፋፍቶ ዝሙት በዝቶ አንድ ወጭማዳ ሁለትና ሦስት ሴት ሲያስቀምጥ ይህ ሃይማኖታችን አይፈቅድም ብላችሁ ለምን አላስተማራችሁም?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ስትረክስ ማጽዳት የእናንተ ሥራ አልነበረምን? ዛሬ ጥቅማችሁ ሲነካ እኔን ልትመክሩ መምጣታችሁ እግዚአብሔርን አትፈሩም" ብለው ከፍና ዝቅ አድርገው ሲመለከቱአቸው መነኮሳቱ ደንግጠው ተመለሱ:: ከዚህ በኋላ ተበደልን ባዮች ካህናቶች ከተለያዩ አካባቢ ተሰብስበው ጉባኤ ይደረግልን አጤ በደሉን ሲሉ ጠየቁ አጤ ቴዎድሮስም ፈቀዱላቸውና በጉባኤ ክርክር ይነታረኩ ጀመር::

አበበ ኃይለ መለኮት <u>የአድዋ ድልና የኢትዮጵያ ጀግኖች ውለታ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 12 "እስከ አጼ ቴዎድሮስ ንግሥና ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ የተጠናከረ ማዕከላዊ መንግሥት ባለመኖሩና እኝህም መሪ ቢሆኑ ባካሄዱት የአንድነት ዘመቻ የተጠቀሙበት ስልት በጊዜው ተንሰራፍቶ የነበረውን የፊውዳል ባላባቶች ጥቅምና በተለይ የቤተ ክርስቲያን ሲሶ መንግሥት የሚለውን የሚሸረሽር ስለነበር በዚህ ትልቅ ተቃውሞ ይደርስባቸው ስለነበር" ሲሉ ጽፈዋል::

ከላይ እንደተጠቀሰው አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ለማሠልጠን ጥረት ሲያደርጉ ይህ የበስማም ቄስ የማይገባው ደብተራ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርሶ እንዳይበላ ወሩን በባላት ሞልቶ ሕዝቡን በረኀብና በስንፍና ተቀፍድዶ እንዲቀር ለማድረግ ከግብጽ የመጣውን የሴራ በዓላት መደርደር ጀመሩ:: ለምሳሌ ግብጽ ውስጥ ሕዝባቸው



የማይሠራው ዓርብ፤የእስላሞች በዓል ሲሆን እነሱ ግን እሁድ እንዲሠሩ ይገደዳሉ::

ተገዝተው የሚመጡት ጳጳሳት ይህን ሥርዓት በአገራቸው መኖሩን እያወቁ ኢትዮጵያ ሲመጡ ግን የኢትዮጵያ አርሶ አደር እንዳያርስ ብለው ይህን የኛውን ቄስ ይነግሩታል:: ከግብጽ የሚመጡ ጳጳሳት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሠርቶ ከበላና ከጠጣ ፊቱን ወደ አባይ ወንዝ አዙሮ ይሠራና ወደ ግብፅ የሚሄደው ውኃ እንዳይቀንስ ብለው ነው:: ታዲያ እነሱ በመሰሪ ተግባር ታጥቀው ሲነሡ የእኛዎቹ በወር በዓል ቀን ሲያርምና ሲያርስ የታየ አርሶ አደር ቢሞት አይፈታ ልጅ ቢወልድ ክርስትና አይነሣለት "ውጉዝ ከመአርዮስ" ብለው ይቀፈድዱታል::

ውግዘት ሠርቶ ለሚበላው ሕዝብ ሳይሆን በሃይማኖት ምክንያት ተወግዞ የሚለይ መናፍቅ ነው:: ይህ ቀደም ለአርሶ አደሩ ያሸከሙት የነበረው ዛሬ ጳጳሳቱ እርስ በርሳቸው ተወጋግዘው ይገኛሉ:: ለምሳሌ ቀደም ሲል የነበሩት የበስማም ቄሶች የሚያደርጉትን የዛሬዎቹ ጳጳሳት በሐሣብ ያልተግባባቸውን ጳጳስ ማውገዝ ተጀምሯል::

ይህ ተግባር ቀደም ጀምሮ የመጣ በመሆኑ የዛሬዎቹስ ከቀድሞዎቹ ደግሞ የላቁ ናቸው:: የቀድሞዎቹ የሚያወግዙት የጠሉትን ብቻ ነበር የዛሬዎቹ ደግሞ የጠሉትን ብቻ ሳይሆን ተራውን ምእመን ጭምር ማውገዝ ተጀምሯል:: አንድ ሰው ሊወገዝ የሚገባው በሃይማኖት ክህደት ሲያሳይ ለዚህም በጉባኤ ቀርቦ ተመክሮ አልመለስ ሲል ብቻ ነው::

ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለሕገ ወጡ የወያኔ ሲኖዶስ የተሰጠ መልስ <u>የማይገለጥ የተከደነ</u> <u>የለም</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 172 "እውነተኛ የሃይማኖት ሰዎች አንድን የሃይማኖት ሰው ሲያወግዙ የሚወገዘው ሰው አስተምህሮው እንዴት እንደሆነ በጉባኤ ተጠይቆ በትክክል የሃይማኖት ሕፀፅ ከተገኘበትና እንደነ አርዮስ ተመክሮ አልመሰልም ሲል ብቻ ነው" ይላል መጽሐፉ::

ትክክለኛ አውጋዥ በዚህ መሠረት እንጂ የሚያወግዘው የግብጽ አጳጳሳት በተንኮል የመከሩትን ምክር በመያዝ የቤተ ክርስቲያንን ልጆች ማባረሩ አግባብ አይደለም:: ዛሬ እንደሚያደርጉት ሁሉ

ቀደምም አጤ ቴዎድሮስን አሳሠራቸው ያሉ እነዚህ የቤተ ክህነት ሰዎች ነበሩ::

አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ የተወለዱ ለኢትዮጵያ የተሠዉ ንጉሠ ነገሥት ናቸው በተባለው መጣጥፉ ገጽ 16 "አጤ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ተብለው በመላ ኢትዮጵያ ከነገሡ በኋላ አስተዳደር ሲጀምሩ መቸም ሥልጣን ለያዘው ሁሉ ማንም የማይቀድማቸው አንዳንድ የቤተ ክህነት ሰዎችና ከያኒዎች አቀባበልና የደስታ ርችት አቅርበውላቸው ነበር:: በመሀሉ አጤ ቴዎድሮስ ይህ ሁሉ ሊቃውንት ቀሳውስት፣ደብተራ፣ዲያቆናት በምን ይተዳደራሉ ብለው ቢጠይቁ ይህ የሚታየው ደብተራ ሁሉ::"

"በያንዳንዱ ደብር 100፣150፣200፣300 ተሠርቶ ሁሉም ቀዳሽና አወዳሽ ሆኖ ነው የሚኖረው የሚተዳደረውም በገጠሩ አገር በሚኖረው አራሽ ሕዝብ ሪም የተባለ አበል አውድማ ከጣለው አራሽ ገበሬ እህል እየተከፈለው እየተቀበሉ ነው የሚተዳደር ተብሎ ከተነገራቸው በኋላ ጉዳዩን በጥሞና አጥንተው ፍትሐ ነገሥት ተመልክተው ያልሠራ አይብላ በሚለው መሠረት::"

"ከዛሬ ጀምሮ ለአንድ ደብር 2 ቄሶችና 3 ዲያቆኖች ይበቃሉ ሌላው ግን በየሀገርህ ገብተህ የምትችለውን ሥራ እየሠራህ ኑር ብለው አዋጅ በማስነገራቸው "ሲጠባ የለመደ ጥጃ ሲይዙት ይጓጉራል" እንደሚባለው ገበሬው ያረሰውንና ያመረተውን ምርት ሁሉ ከተማ እያስመጣ ሲበላ ሲጠጣ የነበረው ሁሉ ጥቅሙ ስለተነካበት ተቃወማቸው" ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 88-89 "የቀሳውስቱ አፈ ጉባኤ (ተናጋሪ) አራት ወር በጎንደር ተቀምጠው አርማጭሆን፣ ጠገዴን፣ወልቃይትን ስሜን ትግራይን ይብሉ:: አራት ወር በአሪንጎ ተቀምጠው በጌምድርን፣ላስታን የጁን ወረሂመኑን ወሎን ሸዋን ይብሉ:: አራት ወር ይባባ ላይ ተቀምጠው ሜጫን አገውን፣ዳሞትን ጎጃምን፣ይብሉ:: እንደ ጥንቱ እንደ ነገሥታቱ ይሁን አሏቸው:: ይህን አባባል ስንመለከተው ንጉሡ ከቀሳውስቱ ራስ ላይ ተነሥተው ባላገሩ ራስ ላይ እንዲሰፍሩ የሚጠይቅ ነው::"



"አጤ ቴዎድሮስም ለቀሳውስቱ ጥያቄ ሲመልሱ በሴት አጠራር እየተናገሩ እኔ ብቻዬን ብሆንልሽ ጊዜ እንደ አጤ ኢዮአስ በኛሽ አንቀሽ ልትገድሊኝ ነው? አሉና በፍትሐ ነገሥት እንዲወሰን አዘዙ:: ፍትሐ ነገሥቱ በቀሳውስት የተዘጋጀ የሕግ መጽሐፍ በመሆኑ ለቀሳውስት ያደላልና የፍትሐ ነገሥቱን ውሳኔ ለቀሳውስት ሆነ:: ይህን የሰሙት ቴዎድሮስ አንድሽ አንባቢ አንድሽ ተርጓሚ ብለው ተቆጥተው የወደዳችሁትን በአልጋው አስቀምጡበት" ብለዋል::

በዚህ ምክንያት ከቤተ ክህነቱ ጋር ከፍተኛ ውጥረት ገቡ:: አጤ ቴዎድሮስ የሚሉትን የመሬት ሥሪት የማይቀበሉ ሆኑ:: ካህናቱም ልማዳችን ተሻረብን በማለት አልተኙላቸውም ቅድሚያ መኳንንቱ ሲሸፍቱ ማበረታታት ብቻ ሳይሆን "ቴዎድሮስን የተከተልክ ተወግዘሃል" በማለትም ወታደራቸው እንዲርቅ ከፍተኛ የሆነ ሴራ አሴሩባቸው::

## ምዕራፍ 4

## አጤ ቴዎድሮስና ደብተራ፣

ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት ገጽ 25 "አጤ ቴዎድሮስ ደብተራ አይወዱም ነበርና ደብተራን ሲሰድቡ ድጉን በራሱ ላይ እየታጠቀ አይዋጋ አይገብር ከከተማ ሁኖ የሰው ምሽትና ጋለሞታ እየመለመለ ነው ኑሮው ይሉት ነበር" ሲሉ ጽፈዋል::

የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 119 "ይልቁንም ደብተራ በንጉሡ ፊት የተጠላ ሆነ:: ይሰድበው ጀመረ:: ስድቡም አረግራጊ፣አቴና ወጊ፣ራሱን ታጣቂ፣ወገቡን ሰባቂ ይለው ነበረ" ሲሉ ጽፈዋል:: ደብተራ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በገባኝ መሠረት ላብራራ:: ቀደም በአሪት ደብተራ ማለት ቤተ መቅደስ የሚያገለግሉትን ይመለከታል::"

"ከክርስትና በኋላ ግን ደብተራ አይባሉም:: በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት "ደብተራ" ማለት ደግሞ ሁለት ትርጉም ያለው ይመስለኛል:: አንደኛው ካህኑ በትጳር ላይ እያለ

ሚስቱ፡ ብታርፍበት ካልመነኩሰ ቅስና ማዕረጉን ስለማይጠቀምበት ከውጭ ሁኖ ቤተ ክርስቲያንን ስለሚያገለግል “ደብተራ” ይባላል።

ሌላው ደግሞ መንፈሳዊ ትምህርት በመማር የገፉ ውለው አድረው ምርምራቸውን የሚቀጥሉ ከመንፈሳዊ ይልቅ ወደ እርኩስ መንፈስ የሚጠጉ ደብተራ ይባላሉ። እነዚህ ደብተሮች በጣም የተማሩ ስለሆኑ “እንደርብ” የሚባል ድግምትና እንዲሁም ቅጠል በጥሰው መቀመም የሚችሉ ናቸው። ስለዚህ አጤ ቴዎድሮስ እነዚህን በሁለተኛ ደረጃ የተመዘገቡትን ደብተሮች አይወዱአቸም ነበር።

እኔ እንኳን የቆሎ ተማሪው ደብተራ ያየሁት ተንኮል ቀላል አይደለም። በ1966 ዓም ሚያዝያ መጨረሻ ላይ ከባሕር ዳር ወደ ጎንደር ከአንድ የቆሎ ተማሪ ጋር አብሬ ስሄድ ሳለ ጉድ አይቻለሁ። ከመጽሐፍ ላይ ቀርቶ በወግ እንኳን ለማውጋት ይከብደኛል። ያየሁትን በ1979 ዓም የከተብኩት ይህን ይመስላል።

አማረ አፈለ ብሻው <u>እኔ ከጆሮዬና ከዓይኔ ጋር</u> በተባለው መጽሐፌ ገጽ 120 “አይቸውና የቆሎ ተማሪው ወደ ቆላድባ ጉዞአቸውን ሲያደርጉ ለልመና መንደር ገቡ። በጣም የምታምር ሴት እንጀራ ልትሰጣቸው ወጣች። የቆሎ ተማሪው እንዴት እንዳፈዘዛት አይቸው ሳይገባው በረኛ አድርጎት እርሱ ሴቲቱን ተኝቶአት ወጣ”ስል በዓይኔ ያየሁትን ጽፌዋለሁ።

ስለዚህ አጤ ቴዎድሮስ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎቻችን የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች የሆንን ይህን የደብተራ ተግባር አጥብቀን እንጠለዋለን። ከፍ ተብሎ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ላይ ያልጠቀስኩት ተማሪ ሁኜ እየተማርኩኝ በነበረ ሰዓት ብዙ ጉድ አይቻለሁ።

የአባቴ የነፍስ አባት ዛሬ ድረስ ያሉ ቄስ ይርዳው ባይለኝ የሚባሉ። ጎረቤቶቻቸው ቀን ቤት እየገቡ እንጀራ ስለሚሰርቁአቸው አንድ ቀን ከሞሰቡ ላይ በድግምት እባብ አስቀምጠውበት ሄዱ። መስረቅ የለመዱ ጎረቤት እንደለመዱት ሞሰብ ሊከፍቱ ሲሞክሩ እባብ በማየታቸው መስረቁን አቆሙ። ሌላ ደግሞ አለቃ ቀለመወርቅ የተባሉ ደብተራ በ1964 ዓም የግራሪያን እሕል በረዶ እንዳይመታው ኀላፊነት ይወስዳሉ። ላይ ጊሩ ከተባለው ተራራ ላይ ሁነው ራቁታቸውን ሲቀባጥሩ በዓይኔ ተመልክቻለሁ። በረዶው እርሳቸው



ከሚጠብቁት አልፎ ወርዶ እህሉን አጥፍቶታል። ይህ የልጅነት ጭንቅላቴ ዛሬ ፈጽሞ አይረሳኝም።

ይትባረክ ግደይ <u>የቅኔ ቤት ባህልና የሕይወቴ ገጠመኝ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 8“ ዕፀዋት ከጥቅማቸው ሌላ ለጠላትም እንደ ማደንዘዣና መቀጣጫም ሆነው የድሮ ሊቃውንት ይጠቀሙባቸዋል። ለምሳሌ እንደ አንደርቢ የሚሠራው ከዕፀዋት የተቀመመ ነው። ጥላ ወጊ የሚባልም አለ እሱም አንዳንድ ዕፅ በአስማት ለሰባት ቀናት ያህል ተደግሞ በጠላት ጥላ ዙሪያ ሲያዞሩት ሰውየው ወዲያውኑ ይወድቃል። ወይም ይታመማል ብሎም ይሞታል” ሲሉ ጽፈዋል።

ይገርማል ይህን የሚያደርጉ ደብተሮችን ነው አጤ ቴዎድሮስ የጠሉአቸው። አጤ ቴዎድሮስ የደብተራውን ሴራ ያወቁት ጎጃም ከደጃዝማች ጎሹ ቤት ሳሉ በዓይናቸው ያዩት ታሪክ ነበር። ይህም ታሪክ ደብተራው የአባወራ ሚስት አፍቅሮ ሌሊት በድግምት ወደ ቤቱ ወስዶ የፈለገውን ከጨረሰ በኋላ ደግሞ ወደ ቤቷ ይመልሳታል። በዚህ ወቅት አንድ ቀን የአውሬውን ሳይደግም እያብከነከነ ሲወስዳት ጅቡ በላት።

<u>የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 96 “አለቃ አርአያ የሚባል አስማተኛ ደልማ አማኑኤል ላይ ነበረ። የውላ ከሚባል አገር ላይ የጎልማሳ ሚሽት ውሽምነት ለምዶ በአምጽኦ ብእሲት ማታ ማታ ያመላልሳት ነበረ። አንድ ቀንም የጅብ ሳይደግምባት ቀርቶ በምሽት ስትሄድ ሳሲ ከሚባል አገር ላይ ስትደርስ አውሬ በላት። እናትና አባትዋ ባሉዋም ደምበጫ ሄደው ለደጃዝማች ጎሹ ጮሁ። ደጃች ጎሹም ተጮሆብሃልና መጥተህ መልስ ብሎ ላከበት።”

“አለቃ አርአያም በአስማቱ ኮርቶ አልመጣ አለ። ደጃች ጎሹም አስማቱ ሲአድነው እየዋለሁ ብሎ እጁን የሚይዝ ጭፍራ ሰደደ። ይሄን ነገር አለቃ አርአያ በሰማ ጊዜ በቤቱ አጥር ዙሪያ ዕፀ መሠውር መድፍን ፀር ደገመና ረጨው። እኔ አርአያ አልተማርኩማ ብሎ ፎከረ። የዚህ ጊዜ ወታደር አለቃ አርአያን ሊይዝ በመጣ ጊዜ ቤቱን ለማየት ተሳነው። ቤቱን አሳዩን እያለ ያገኘውን ሁሉ ባሳገር ሁሉ ሲደበድብ አምሽቶ አጥቶት እየተደነቀ ተመለሰ። ከነቤቱ ተሰውሮ ጠፋን ብሎ ለደጃች ጎሹ ተናገረ።”

"ደጃች ጎሹም እዚያው እየተወዳጃችሁ ነው እንጂ ቤቱ ተሠውሮ አይደለም ብሎ እሄዳለሁ ጫኑ አለ:: መኳንንቱም ያዋርደናል አይሆንም ባይሆን ታማኝ ሰው ሄዶ ይያዘው አሉ:: ደጃች ጎሹም አይሆንም ሰው አላምንም ብሎ ተነሣ::"

"አማሬ ኢየሱስ ከሚባል አገር ሲደርሱ አለቃ አርአያ ሰምቶ የእግረ መልስ ደገመ:: ቀንደ መለከቱና ነጋሪቱ እንዳይጮህ ድምፅ የሚዘጋ አስማት ደገመ:: የዚህ ጊዜ የነጋሪቱና የመለከቱ ድምፅ ሲዘጋ ሠራዊቱ ደነገጠ:: አይሆንም እንመለስ ሌላ ቀን በድንገት አዘናግተን ሌሊት እንይዘዋለን ብሎ መኳንንቱ ደጃች ጎሹን ተቆጡ:: ከዚያ ወዲህ ባትከና ወደ በኸራ ተመለሰ:: በሌላ ቀን አዘንግቶ ድንገት በሌሊት አስይዞ ገርፎ ዋሚት ዋሻ አሠረው" ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ ደብተራ ሊጠሉበት የቻሉት ከላይ የተጠቀሰውን አለቃ አርአያን ለመያዝ ከሄዱት ወታደሮች አንዱ ሳይሆኑ እንዳልቀሩ አንዳንዶች ይናገራሉ:: በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም አጤ ቴዎድሮስ ደብተራን የጠሉት:: ኋላም ከነገሡ ወዲህ ደብተራ ፈጽሞ አይወዱም ነበር:: ከቄስ የበለጠ ግብር እንዲከፍል ያደርጉት ነበር:: በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ደብተሮች አጤ ቴዎድሮስን የጠሉአቸው:: የመምህር አካለ ወልድን የሕይዎት ታሪክ የጻፈው ደራሲ የደብተራውን ስም ጠቅሰው አብራርተዋል::

የመምህር አካለ ወልድ <u>የሕይወት ታሪክ እና ቅኔዎቻቸው</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 31 "አጤ ቴዎድሮስ ጭከናቸው ይነገራል እንጂ ዕውቀታቸውና ፍርዳቸው እጅግ አይነገርም:: ነገር ግን ወልደ ሚካኤል የሚባል ደብተራ በተንኮሉ አእምሮአቸውን ሳይለውጠውና ሳያጠፋው እጅግ የሚያስደንቅ ፍርድ ይፈርዱ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህ ደብተራ ሁሉ የአጤ ቴዎድሮስ ዓላማ እንዳይሳካ ያደረጉ ተንኮለኞች ናቸው:: አይሠሩ አያሠሩ አንዱን ካንዱ ሲያጣሉ የሚውሉ ነበሩ:: እነዚህ ደብተሮች ለአጤ ቴዎድሮስ ዓላማ አለመሳካት ዋናዎቹ ተንኮለኞች ሕዝቡ ከእርሳቸው እንዲርቅ ያደረጉ ናቸው:: ዛሬም እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ይቅርና አንዳንድ በስደቱ ዓለም የሚያመሳቅሉ መኖራቸው አይዘነጋም::



# ምዕራፍ 5

## አጤ ቴዎድሮስና መነኮሳትና ካህናት

ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር <u>ምንኩስና በኢትዮጵያ ዛሬና ትናትና</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 91 "የሐሳውያኑን መነኮሳት ተንኮል የተረዱት አጤ ቴዎድሮስ ብቻ ነበሩ፤የእነዚህ ሐሳውያን መነኮሳት ባሕታውያን ሰለባ ከሆኑት መካከል አጤ ዮሐንስ ይገኙበታል:: አጤ ዮሐንስ ወደ መተማ ዘምተው እንዲሞቱ ምክንያት የሆኑት በአጤ ምኒልክ የተላኩ የቀበሮ ባሕታውያን ነበሩ" ሲሉ ጽፈዋል::

ካህኑ የጌታን ሥጋና ደም አስመልክቶ በቅዳሴ ጊዜ እንዲህ ይላሉ" ንጹሕ የሆነ ከቁርባኑ ይቀበል! ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቀበል! ለሰይጣንና ለመላክተኞቹ በተዘጋጀ በመለኮት እሳት እንዳይቃጠል! በልቡናው ቂምን የያዘ ልዩ አሳብና ዝሙትም ያለበት ቢኖር አይቅረብ! እጄን ከአፍአዊ እድፍ ንጹሕ እንዳደረግሁ! እንደዚሁም ከሁላችሁ ደም ንጹሕ ነኝ ደፍራችሁ ወደ ክርሥቶስ ሥጋና ደም ብትቀርቡ ከርሱ ለመቀበላችሁ መተላለፍ የለብኝም:: ኀጢአታችሁ በራሳችሁ ይመለሳል እንጂ በንጽሕና ሁናችሁ ባትቀርቡ እኔ ከበደላችሁ ንጹሕ ነኝ" ብለው መነኮሳቱ ይናገራሉ::

ቃሉ መባልም ያለበት መሆኑን ከእኛ ይልቅ መነኮሳቱ ያውቃሉ ነገር ግን "ቂምን የያዘ" የሚለውን ቃል ራሳቸው ተናግረው ምዕመናኑን "አሜን" አስብለው ቂም በዝቶ የሚታይባቸው በመነኮሳቱ መሆኑ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ቀኞችሁን ሲመቱአችሁ ግራችሁን"ስጡአቸው አለ እንጂ ቂም ይዛችሁ ኑሩ ብሎ አላስተማረም:: መነኮሳት ቃሉን ለምእመናን ያስተምራሉ::

አጤ ቴዎድሮስ መነኩሴ አይወዱም ነበር:: ምክንያታቸው ሰነፍ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባረከውን ጋብቻ ሽረዋል ብለው ይነቅፏቸው ነበር:: ከቄስና ከመነኩሴ ቄስን ይመርጣሉ:: በነገራችን ላይ መነኩሴ ሁሉም አንድ ናቸው ማለት አይደለም ብዙ ጥሩ መነኮሳት ቀደሞም ነበሩ ዛሬም ደግሞ አሉ::

በእርግጥ የቀድሞዎችን የሠሩትን ታሪክ አንብበን ተግባራቸውን ልንረዳላቸው እንችላለን የአሁኖቹ ግን እንዲያው እግዚአብሔር ይቅር ይበላቸው:: ከቀድሞዎቹ መነኮሳት አንድ ሰው ጠቅሼ ልለፍ::

አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ መጽሐፈ ምስጢር ገጽ 74“ እግዚአብሔር እንደ አዳምና ሔዋን እንደጠየቃቸው እባብን በደሏን ሳይጠይቅ እርግማንን አስቀደመ:: ምክንያቱም የኃጢአት መሠረት ከእባብ እንደ መጣ ያውቃልና እንደገና እግዚአብሔር ሰይጣንን ተቃወመው” ሲሉ ጽፈዋል::

ከዚህ በላይ የተጠቀሰችው ጥቅስ ጥልቅ መንፈሳዊ ትርጉም አላት:: የዚህ አይነት ጥልቅ ትምህርት የሚያስተምሩትን መነኮሳት አጤ ቴዎድሮስ አልጠሉአቸውም:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን አጤ ቴዎድሮስ ያደንቋቸው ነበር ይባላል:: ምናልባት ይህን መጽሐፈ ምስጢር የተባለውን መጽሐፍ ሳያነቡት አይቀሩም:: ከዚህ መጽሐፍ ላይ በ14ኛ ክፍለ ዘመን ከአንድ የውጭ አገር ሰው ጋር መከራከራቸውን መጽሐፉ ይገልጻል:: ረትተው ሰደውታል ይባላል:: በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም አጤ ቴዎድሮስ የተማረ የሚፈልጉት ልክ እንደሳቸው መጤዎችን አሳምኖ የሚልክላቸው::

አጤ ቴዎድሮስ “ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ ያከበረውን ጋብቻ ንቆ ቀብ አግብቶ ወንጌልን አይሰብክ:: አገር ለአገር እየዞረ አይሠራ አያሠራ ግብር አይከፍል ግራ የገባው ምንኩስናን የሰነፍ ዋሻ አደረገው” በማለት ይቆጩ ነበር:: ለነገሩ መነኮሳት ክርስትና ሲጀመር አልነበሩም:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይም ጳጳሳት የሚሆኑት ባለትዳር መሆናቸው ግልጽ ነው::

ለምሳሌ ወደ ጢሞትቴዎስ 3፡1“ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል፤የሚለው ቃል የታመነ ነው:: እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤የማይነቀፍ የአንዲት ሚስት ባል፤ልከኛ ራሱን የሚገዛ፤እንደሚገባው የሚሠራ፤እንግዳ ተቀባይ፤ ለማስተማር የሚበቃ፤የማይሰክር፤የማይጨቃጨቅ ነገር ግን ገር የሆነ የማይከራከር ገንዘብን የማይወድ፤ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?”የሚለውን የተረዱ ነበሩ::



ቀደም ክርስትና ከተስፋፋ በኋላም ጳጳሳት እንኳን ባለትዳሮች ነበሩ:: ለምሳሌ አንድ ካህንና አንድ መነኩሴ ሲያስተምሩ ልዩነት አላቸው:: ምክንያቱም የተማረ ካህን ከሆነ ትምህርቱ ዓለማዊና መንፈሳዊ አቀላቅሎ ስለሚሆን በተለይም ዛሬ ላለነው ትውልዶች የቄሱ ትምህርት ይበልጥ ጥቅም አለው:: ነገር ግን ካህናቱ ደግሞ በብዛት የተማሩ አይደሉም:: ያም ሆነ ይህ የጳጳሳትና የመነኮሳት ሕግ የወጣው ቆይቶ ነው:: በተለይም ስለመነኮሳት ደግሞ ማር ይስሐቅ የተባለው መጽሐፍ የመነኩሴን ተግባር ጥሩ አድርጎ ያብራራል:: በማር ይስሐቅ መጽሐፍ መሠረት የዛሬው መነኩሴ ሁሉ ዜሮ በዜሮ ይወጣል:: በዚህ ምክንያት ነበር አጤ ቴዎድሮስ መነኮሳቱን አጥብቀው የሚጠሉአቸው:: እንኳን በሳቸው ዘመን ቀርቶ የዛሬዎቹ መነኮሳት ተንኮላቸው አይጣል ነው::

አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 103 “ሁለት መነኮሳት ተጣልተው ሲሰዳደቡ ያየና የሰማ ወታደር ሁለቱንም ይዞ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ አቀረባቸው፤ወታደሩም በሁለቱ መነኮሳት በኩል በተነሣው ጠብ ያየውን ትግልና የሰማውን ስድብ እየዘረዘረ ለንጉሠ ነገሥቱ አስረዳ፤ንጉሡም የሰሙት ነገር ሁሉ ፍሬ ቢስ መሆኑን ከሰሙና ከተረዱ በኋላ መነኩሴ ምንኛ ጠገብሽ ድግሺን ከራስሽ እየጠመጠምሽ አትዘምች፤አትዋጊ አታርሺ፤አትነግጂ፤እንዲያው ዝም ብለሽ አገር ለአገር እየዞርሽ እየበላሽ ጠግበሽ ሰውን አላሳርፍ ካልሽ በሉ አሁን ሁለታችሁም ልብሳችሁን ጣሉና ትግል ግጠሙ አሉአቸው::”

“ሁለቱም ልብሳቸውን ጥለው ቀሚሳቸውን ብቻ ለብሰው ከንጉሡ ፊት ትግል ገጠሙና አንዱ በላይ በታች ሳይሆኑ አህያ ውድቂያ እንደሚባለው ግድም ለግድም ተወዳደቁና ይጎፈጫጨሩ ጀመር:: በዚህ ጊዜ ንጉሡ እየሳቁ የታባሽ መነኩሴ መላስ ብቻ ተሽከመሽ በሉ አንሡአቸው አሉ:: ከእንግዲህ እርስ በርሳችሁ ስትደባደቡ ብትገኙ እገርፋችኋለሁ ብለው አሰናበቱአቸው” ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ አሁን ኑረው ቢሆን ስንት መነኩሴ ጉዱ ይወጣ ነበር? በተለይም ይህን ተምትሜና ከምክሜ ቂስና መነኩሴ ጥሩ አድርገው ይቀጡት ነበር:: በነዚህ መነኮሳት እናት ቤተ ክርስቲያን ጠፋች:: መነኮሳት እነሱ በፈለጉት መንገድ ካልሄደላቸው የጠሉትን አጤ ሆነ

ግለሰብ የሚያስጠሉበት ኃይል አላቸው:: ይህን ስለተረዱ ነው መጨረሻ አጤ ቴዎድሮስ "ታግዬ ያልጣልኩት የካህናትን ጠብ ነው" ያሉት:: እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ እንጂ እኔም የእናንተን ተንኮል አስመልክቶ ደጋግሜ በመጻፌ መኮነኔ አይቀረም::

የራሴ አልበቃ ብሎኝ በእናንተ ምክንያት ጭማሪ ማግኘቴ ግልጽ ይመስለኛል:: አጤ ቴዎድሮስ ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው መነኮሳትን ይዘልፏቸው ነበር:: ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስን ጠንቅቀው የማይችሉ በመሆናቸው ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስን ጠንቅቆ የሚያውቅ መምህር ይወዳሉ:: የማይወዱት ሰነፉን ነው:: ለዚህም ነበር መምህር አካለ ወልድን አቆላምጠው አካልዬ" ይሏቸው የነበር::

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ <u>ጠልሰም በዲሲ ደፍተራ</u> በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 30 "የአጤ ቴዎድሮስም ውሳኔ የሚታለፍ አይደለም:: መንፈሱ የላሸቀውን የኔ ቢጤ ሰርጎ ገብ የከተማ ቄስ ገስጸውና አስተካክለው ለመመለስ ከገዳማቸው ብቅ የሚሉትን የእንጦስን ሥርዓት ለሚከተሉ ከፍተኛ ክብር እየሰጡ፤ጠልሰመኞችን ራስ ታጣቂ ወገብ ሰባቂ፤አቴና ወቂ፤እያሉ ከየደብሩ አስወጡልኝ ይሉ ነበር:: የፀሐይ ቆብ ደፍቶ መነኩሴ መስሎ ከገዳሙ እየለቀቀ ከተማ ገብቶ የቅንጦቱን ኑሮ በመጀመር የሚአምታታውን ደግሞ ኩፌት ደፊ ጢም ከፍካፊ፤ቀሚስ አንዘርፋፊ ሁሉ ከፊቴ አጥፉልኝ ይሉ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው በብዛት ባጤ ቴዎድሮስ ዘመን የነበረውን ታሪክ ዳሰስ ካደረኩኝ በኋላ ወደ ቅርቡ ዘመን መነኩሴ ልመልሳችሁ:: መነኮሳት ቀደም ባጤ ቴዎድሮስ ዘመን ይረብሹ የነበሩ ዛሬም ከመረበሽ አልተቆጠቡም:: በሞቴ አንዱን መነኩሴ ቀርባችሁ ጸባዩንና የምንኩስና ልብሱን በጥሞና ብታጠኑት ይገርማችኋል:: እኔ መቸም ለወደፊቱ መስቀል አናሳልምህም እንዳይሉኝ እንጂ ተግባራቸውን ተረድቻለሁ::

<u>ምንኩስና በኢትዮጵያ ዛሬና ትናትና</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 89 "በኢትዮጵያ ምንኩስና ሥርዓት በየጊዜው ከሚከሰቱ እንቅፋቶች አንዱ ሐሰተኛ መነኮሳት (የቀበሮ ባሕታውያን) የሚፈጥሩት ችግር ነው:: እነዚህ ሐሰተኞች በስምና በአለባበስ መነኮሳት መስለው በገቢር



ግን አንዱን ከአንዱ እያምታቱ የግል ጥቅማቸውን ሲያሳድዱ የሚኖሩ ናቸው::"

"እነዚህ አስመሳዮች በቁጥር አነስተኛ ቢሆኑም መንግሥትንና ሕዝብን ነገሥታቱንና ባለሥልጣናትን ቤተ ክርስቲያንና መንግሥትን በማጋጨት ከፍተኛ ችግር ሲፈጥሩ ኖረዋል:: እነዚህ መነኮሳት ሽፍን የሚንቀሳቀሱበት ደበሎና ብጫ ለባሾች ከጥንት ጀምሮ አሁን እስካለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በችግር ፈጣሪነታቸው በርካታ ጉዳቶችን ፈጽመዋል"ሲሉ ጽፈዋል::

በተለይ የቅርቡ መነኩሴማ የጥቅም ሰዎች አይደሉም እንዴ? እነሱ አንድ ነገር ለማግኘት ሲፈልጉ ከቻሉ በቀጥታ ካልቻሉ በተዘዋዋሪ ፀሐይ ሳትገባ ይወስዳሉ:: ከእነሱ ያለ ነገር ቢኖር ደግሞ መሬት ከፍ ቢል ሰማይ ዝቅ ቢል አይሰጡም:: ኸረ እግዚኦ ያሰኛል:: መጽሐፍ ቅዱስ እያስተማሩ ትሕትናን እየሰበኩ በእነሱ በኩል ግን አይታወቅም:: ከሚገርመው ነገር ደግሞ ማስመሰል ይችላሉ:: ከምእመናን ፊት ሰላም ያላቸው ይመስላሉ:: አብረው እየቀደሱና ሥጋ ወደሙ እየፈተቱ እነሱ እኛን እያስተማሩ አይስማሙ በአዲስ አበባማ እንዲያውም በፎቶ ተደግፎ የወጣው መጽሐፍ የሚለው ለገንዘብ ብለው መስቀላቸውን ለእስላሞች ማስረከባቸው ተጽፎአል::

<u>ፍሬ አልባ በለሶች</u> የተባለው መጽሐፍ ገጽ 35 የሚታየው ምስል ፎቶ ክርስቲያንነትን ሲያጥላሉና ክርስትናን ክደው እስልምና ሲቀበሉ ገጽ 36 ከሰለሙ በኋላ በደስታ ከሙስሊሞች ጋር ከተቃቀፉ በኋላ ዝቅ ብሎ ያለው ፎቶ ደግሞ ከሰለሙ በኋላ የእጃቸውንና የአንገታቸውን መስቀል ለሙስሊሞች ሲያስረክቡ ገጽ 37 የእስላም ቆባቸውን ከደፉ በኋላ ዝቅ ብሎ ያለው ፎቶ ደግሞ ሲሰግዱ ያሳያል:: ገጽ 38 ሙሉ የሙስሊም መለያ ልብስ ለብሰው ዝቅ ብሎ የሚታየው ፎቶ ደግሞ ሙስሊሞች ከመነኮሳቱ አንገት የተረከቡትን መስቀል ወድቆ ይታያል ይህን ያደረጉት ሆዳም መነኮሳት ናቸው::

ከዚሁ ፍሬ አልባ በለሶች ከተባለው መጽሐፍ ገጽ 40 "በአንድ ወቅት በነበርኩበት ክፍለ ሀገር አንድ መነኩሴ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ማደሪያ ስጡኝ ብሎ እንግድነት ጠየቀ:: በጠየቀው መሠረትም በቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ቤት ተሰጥቶት ተቀምጦ እያለ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተማረ ስለሆነ ቅዳሴ ልቀድስ ብሎ ጠየቀ

በጠየቀውም ጥያቄ ተፈቅዶለት እየቀደሰ ምእመናን እናቶች በአገልግሎት ላይ ስላዩት ፍትፍት በሳህን እያመጡ እየቀለቡት ለተወሰነ ሳምንታት ከቆየ በኋላ አንድ ቀን በአንድ ትልቅ ሆቴል ገብቶ የምንኩስና ልብሱን እንደለበሰ ከሴተኛ አዳሪ ጋር አልጋ ቤት ገብቶ ይተኛል።

"በዚህን ጊዜ የሆቴሉ ባለቤት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲቀድስ አይተውት ስለነበር ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በመተባበር ለፖሊስ ጠቁመው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ ይታሠራል። በበነጋው ቀደም ብሎ ግንኙነት ያላቸው ኑሮ የሙስሊም መሪዎች ዋስ ሆነው ያስፈቱትና መስጊዳቸው ወስደው የቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ስለተማረ ጥሩ ድምጽ ስለነበረው አዛን (የስልምና የፀሎት ጥሪ) የሚጮህላቸው ያደርጉታል ትንሽ እንደቆየም አዲስ አበባ ይመጣና እንደገና መነኩሴ ነኝ ብሎ በአዲስ አበባ አድባራት ሲዘዋወር አዲስ አበባ በመጣሁበት ጊዜ አገኘሁት አንዳንዶቹ እንደሚሉት ደግሞ በቀዳሽነት ተቀጥሮ ሲሠራ ነበር ብለውኛል" ሲሉ ጽፈዋል።

ታዲያ ይህ እየተደረገ ባለበት ወቅት አጤ ቴዎድሮስ ቢገኙ ኑሮ ስንቱን በእምነቱ ሳይሆን የፀሐይ ቆብ አድርጎ የሚታየውን አስመሳይ መነኩሴ ሁሳ ይገርፉት ነበር? አንባብያን የኢትዮጵያ ቀጥተኛ (ኦርቶዶክስ)ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምንም አይነት እንከን የለባትም። ሃይማኖቷ ጥሪት ያለች መጽሐፍ ቅዱስን በእምነት የተቀበለች መሆንዋ አይካድም።

መነኮሳት ሲሳሳቱ ብታዩ አኩርፋችሁ እናት ቤተ ክርስቲያንን እንዳትርቁ። ዋናው ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ከዚህ ላይ ነው። ለዚህም ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል አስተምሮአል። ማቴ 23፥1 "በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ነገራቸው፤ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል።

ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ፤ጠብቁትም ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ። ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትክሻ ይጭናሉ፤እነርሱ ግን በጣታቸው ሊነኩት አይወዱም። ለሰውም እንዲታዩ ሥራቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፡ስለዚህ አሸንክታባቸውን ያሰፋሉ፤ዘርፍንም ያስረዝማሉ በምሳም የከበሬታ



ስፍራ በምኩራብም የከበሬታ ወንበር በገበያም ሰላምታና-መምህር ሆይ!መምህር ሆይ ተብለው እንዲጠሩ ይወዳሉ" ሲል ተናግሮአል። ማቴ 21፥13 "ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት" ብሎአቸዋል።

ኮሎኔል አስራት ቦጋለ ኢትዮጵያ ዕድሏ 1ኛ መጽሐፍ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 121 "ቁርባን በሚቀበሉበት ጊዜ በቁርባን አስመስለው መርዝ ሊያቀምሷቸው በነበሩ ካህናት ላይ ጥላቻ ስላደረባቸው በየምክንያቱ ብዙ ካህናትን በጭካኔ በመቅጣታቸው የቤተክህነቱን ተቃውሞ አስከተለባቸው" ሲሉ ጽፈዋል። የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ካህናት በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ጨክነውባቸው ነበር ለአጤ ቴዎድሮስ በግልጽ ወታደር ሁነው ከተዋጋቸው ይበልጥ ባለቤታቸውን እንዲያጡ ያደረጓቸው ካህናቱ ናቸው።

አቶ አሰግድ ድሌ በግዕዝ የተጻፈ መጽሐፍ ያላቸው ወዳጄ "ካህናቱ የአጤ ቴዎድሮስን ዓላማ ባያሰናክሉ ኑሮ ኢትዮጵያ እድገት ታመጣ ነበር። ከእርሳቸው በኋላ የነገሡትን ነገሥታት እንዲሁ ተግባራቸው እንዲቀየር አድርገዋል። 4ኛው አጤ ዮሐንስ ባለቤታቸው የአፋር ተወላጅ እስላም ሲሆኑ ቅድሚያ አስተምረው አጥምቀው ነበር ያገቧቸው። ኋላ ካህናቱ የወሎን እስላም ሳያስተምሩ ይጠመቁ ብለው ስለወተወቷቸው አጤ ዮሐንስ የእስላም አገሩ መካ የጠጣ አገሩ ሜካ ክርስትና ካልተቀበልክ ብለው በመነሣታቸው ምክንያት ለጎንደር በድርቡሽ መቃጠል ምክንያት ካህናት ናቸው" ብለውኛል።

ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር እፎይታ መጽሔት ሐምሌ 1991 ዓም ገጽ 35 "መይሳው ካሳ ክርስቲያን ነው፡አልፎ አልፎ ሁኔታዎች እንዲጨክን ቢያስገድዱትም አንድ ሰንበት ጧት ሥጋ ወደሙን ሊቀበል ሊያጎርሱት ሊያጠጡት ሲሉ ውቃቢው ነገረው። ዞረና ቄሶቹን ያን ለሱ አቅደውት የነበረውን ኅብስትና ወይን እነሱ እንዲቀምሱት አስገደዳቸው። እዚያው ቆረቡና ሞቱ። መይሳው ስንቃቸውን አብልቶ አጠጥቶ ወደ መንግሥተ ሰማያት ሸኛቸው" ሲሉ ጽፈዋል።

ከላይ እንደጠቀስኩት እኔ የሰማሁትን ከመጻፍ አልቆጠብም። ያነበብኩትንም እንዲሁ ጥቅስ ከመውሰድ አልተውምና ካህናቱና አጤ ቴዎድሮስ የተጣሉት በጥቅምና በእድገት ምክንያት አልግባባ

በማለታቸው ነው:: አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ለማሳደግ በነበራቸው ፍላጎት ሲሆን ካህናቱ ደግሞ በጥቅማቸው ስለመጡባቸው አጤ ቴዎድሮስን ጨክነው ሊገድሉአቸው ተነሡ::

ታንጎ <u>መይሣው ጋዜጣ</u> ህዳር 12 ቀን 1992 ዓም ገጽ 4 "ሥጋወደሙ አስመስለው የዝሆን ሃሞት ሊአጠጧቸው ሲሉ አጤ ቴዎድሮስ ክርስቶስ ለራሱ ተቀብሎ ነው ያቀበለው በሉ ራሳችሁ መጀመሪያ ተቀበሉ አሏቸው:: ቄሶቹ ሃሞቱን ጠጥተው ሞቱ:: ካሣ በዚህ ተናዶ እዚያ ያሉትን ካህናት ቤተልሔም ውስጥ ዘግቶባቸው ሄደ:: እሳት ተነሣ (በትርምሱ ይሁን ወይም እነሱው ይታዘንልናል ብለው ያቃጠሉት አይታወቅም) እየገሰገሰ መጥቶ አሽከር ለንጉሡ ይናገራል ታዲያ ምን ይደረግ? ይላል ካሣ፤እናውጣቸው፤ እግዚአብሔር ወርዶ ሲፈርድ አትፍረድ ነው የምትለው? አለ ካሣ ካህናቱ በቃጠሎው ሞቱ" ሲሉ ጽፈዋል::

ከዚህ ላይ አጤ ቴዎድሮስ በነበሩ ሰዓት ጀምሮ የነበሩ ደራስያን "ካህናቱ መርዝ ሊሰጡአቸው ሲሉ ነቁባቸው" ብለው አልጻፉም:: በእኔ ግምት ስሜን አትናገር እንዳሉኝ ወዳጄ ቄሶችን ፈርተው እንጂ በትክክል ካህናቱ አጤ ቴዎድሮስን ለማስገደል መሞከራቸው ግልጽ ነው::

አጤ ቴዎድሮስና ካህናቱ ከዚህ ወዲህ ተጨካከኑ:: እነሱም አልተኙላቸውም እርሳቸውም አልተበገሩላቸውም:: ምንም እንኳ በመጨረሻው "ታግዬ ያልጣልኩት የካህንን ጠብ ነው" ቢሉም ተጨካክነው ነበር:: ይህን የሚያደርጉት ደግሞ ሰነፍ ቄሶች ናቸው:: እርሳቸው "ከተማ ቁጭ ብላችሁ አታላግጡ ወንጌልን አጥብቃችሁ አስተምሩ" እያሉ ቀደም በምክር ኋላ ደግሞ በተግሳጽ ይነግሯቸው ነበር:: አንዴ ከጦርነት ላይ የመነኩሴ ልብስ ለብሰው "የዚህን ንጉሥ ጦር በለው" እያሉ ሲያዋጉ ይማረኩና ከአጤ ቴዎድሮስ ይቀርባሉ::

ማራኪው "ጃንሆይ መነኩሴ ማረኩ" ብሎ ሲያቀርብ ያ የተማረከ መነኩሴ "ቄስ ነኝ"ይላቸዋል:: አጤ ቴዎድሮስም እንዳትዋሽ ተጠንቀቅ ይሉታል" ያ ተማራኪ ቄስ" አልዋሽም" ይላል አጤ ቴዎድሮስም ቀጠል አድርገው "ቄስ ከሆንክ ዳዊት ስንት ምዕራፍ አለው" ብለው ሲጠይቁት በክንዱ ያነገተው ዳዊት ስንት ምዕራፍ እንደሆነ ይጠፋበትና" ጃንሆይ ይማሩኝ እንጂ የሜዳ ቄስ ነኝ" እያለ



እየለፈለፈ ሲስት ተመለከቱትና አጤ ቴዎድሮስ እየሳቁ ይህን ገጥመዋል::

"አልዋሽም ያልከው ምነው ቄሱ ዋሽህ
ተመልከት ጉልበትክን እንዲህ ተበላሽተህ"

ቄስ ሲያገኙ ልቡ እስኪጠፋ በጥያቄ ያጣድፉታል:: ጥያቄያቸውን በትክክል የሚመልስና ልበ ሙሉ ቄስ ከሆነ ደግሞ "አካልዬ ተገኘቷል" በማለት ሸልመው ይልኩታል:: አጤ ቴዎድሮስ ወንጌሉ የሚለውን የሚነግራቸው ካህን ይወዳሉ:: ይከራከሩታል አጥጋቢ መልስ ከመለሰላቸው ደስ ይላቸዋል::

ምክንያቱም አውሮፓውያን ፕሮቴስታንት "ካህናቶቻችሁ ማስተማር አይችሉም" ይሏቸው ነበር:: ይህ ቃል ተለውጦ "ካህናቶቻችሁ ማስተማር ይችላሉ" ተብሎ እንዲነገር ይፈልጋሉ:: ካህናቱ በሌላው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጊዜውን ከሚያጠፉ ይልቅ ለእነዚህ ከይሲዎች አጥጋቢ መልስ የሚሰጥ መጽሐፍ ቅዱስ የተማረ መሆኑን ስለሚያምኑበት መምህር አካለወልድን ወንጌል አስተማሪዎች በብዛት እንዲማሩ ለተማሩት ጠቀም ያለ ገንዘብ ቢከፈላቸው የኛ መምህራን ቢኖሩ ኑሮ ይህ ጭባጭባ በሕዝቤና በቤተ ክርስቲያኔ ላይ አይጨፍርብኝም ነበር" እያሉ ይናገሩ ነበር::

መምህር ልዑለ ቃል አካሉ ተጽሕፈ እም አሐዱ ሊቅ ኢትዮጵያዊ ጎሩይ ወመፈክራዊ <u>ፍኖተ እግዚአብሔር</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 41 "አጤ ቴዎድሮስ ወንጌል እንዲስፋፋ ቤተ ክርስቲያን እንድትጠነክር በደቡብ በምሥራቅ በምዕራብ ኢትዮጵያ ወንጌልን ካህናቱ ወጥተው እንዲሰብኩ መመሪያ ሰጥተው ነበር::"

"ነገር ግን የመድረኩ ትምህርት ከተቋረጠ ብዙ ጊዜ ስለሆነው ካህናቱ በከተማ ተቀምጠው የጣመ የላመ እየተመገቡ በከተማ መቀመጥን ስለመረጡ በንጉሡ ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ ስላደረጉባቸው ንጉሡ ፀግዛቴ በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ እግዝአብሔርን የማያውቅ በክርስቶስ ሳያምን የሚሞት እንዳይኖር ሁሉም ለዘላለማዊ ሕይወት እንዲበቃ የጠላት መሣሪያ የሚሆን እንዳይኖር ብለው አስተምሩ አሉ" ሲሉ ጽፈዋል::

ታዲያ ካህናቱ ይህን ማድረግ አልፈለጉም፡፡ አጤ ቴዎድሮስ ከካህናቱ ጋር ጠባቻውም በስንፍናቸው የመጣ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መለወጥና ማስተካከል በመጀመራቸው ጠቡ በጣም ተጋጋለ፡፡

ቀሲስ ዘመነ አቡሐይ ደስታ <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጭር ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 76 "በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስተዳደራዊ ለውጥ ለማምጣት ካላቸው ፍላጎት የአገልጋይ ካህናት ቁጥር እንዲወሰን ቀዳስያን 5 ብቻ እንዲሆኑ፤ የቤተ ክርስቲያንም የመሬት ይዞታ እንዲቀነስ ማድረጋቸው ከካህናቱ ጋር እንዲጣሉ ምክንያት ሆኗል፡፡ በአጠቃላይ በጎ ራእይ ያላቸው ለውጥ ፈላጊ የሀገር መሪ ከመሆናቸው የተነሣ ይከተሉት የነበረው የዘመናዊነት ፖሊሲ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ አልተወደደላቸውም" ሲሉ ጽፈዋል፡፡

አጤ ቴዎድሮስና ካህናት አይግባቡም ነበር፡፡ ምክንያቱም አጤው አገር ለማሳደግ ሲነሡ ይህ የበስማም ቄስ ሁሉ ግራ አጋባቸው፡፡ ሠራዊታቸው ጠንክሮ እንዳይዋጋ የንስሐ ልጃቸውን እየመከሩ እንዳይዋጋ አደረጉ፡፡ ለዚህም በ1848 ዓም አጤ ቴዎድሮስ ሸዋ ላይ ካህናቱ ከወታደሩ ሰርገው ገብተው በጳጳሱና በእጨጌው ስም የታዘዘ ነው ብለው ለወታደሩ መምከራቸው አጤውን እንዲጠሉ አድርገዋል፡፡ ይታያችሁ እነዚህ ካህናት ለአገርና ለሕዝብ ያልሆኑ ነበሩ፡፡

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 173-174 "አንኮበር ላይ (ጎረቤላ) ከአፋፉ ሆነው ለዚህ ንጉሥ ለቴዎድሮስ ዕንጨት የሰበረ ውሃ የቀዳ ሣር ያጨደ የተከተለውም ውጉዝ ይሁን፡፡ ይህ ቃል የአቡነ ሰላማና የዕጨጌ ወልደ ማርያም ነው እያሉ ገዘቱ፡፡ በዚህ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ብዙ ሠንጋ ታርዶ ግብር ሊበላ ሲል ግማሹ ወደ ግብር ተጠርቶ የቀረው ቀለብ እንዲያመጣ ወደ ሐራምቦ ሂድ የተባለ ጊዜ እግዚኦ!እግዚኦ!፡፡"

"እያለ በመጮህ እምቢታውን ሲያሰማ ቴዎድሮስ ወደ ጫፍ ወርደው ጠበንጃና ጦራቸውን እንደያዙ ከፈረሳቸው ላይ ወጥተው የኔ የሆንክ ብለው ታማኙንና ታዛዡን ከለዩ በኋላ በቁጣና በብስጭት ከሠራዊታቸው ውስጥ በጠበንጃ ሰደፍ የመቱት ጦር ወርውረው



ጠበንጃ ተኩሰው የሳቱት እንዳለና በዚህም የትርምስ ጊዜ ግማሹ ሲመታ የቀረውም ሲሸሽ በመካከሉ አቡነ ሰላማና ዕጨጌ ወልደ ማርያም እንደ ገላገሉ ከዚያም ንጉሡ እንደ ተበሳጩ ወደ ቶራ መስክ መውጣታቸውን ያመለክታል፡፡"

"እነዚህን በጳጳሱና በዕጨጌው ስም ሲገዝቱ የነበሩት ወይም በዚህ የግዝት ዐድማ የተገኙት ንጉሡ ቶራ መስክ ከወጡ በኋላ በሰላይ ተይዘው ቀርበው በአደባባይ የተፈረደባቸውን ዐርባ ስምንቱን ሰዎች በጥይትና በጎራዴ እያስመቱ አስገደሉአቸው" ሲሉ ጽፈዋል፡፡ በአቡነ ሰላማ እና በዕጨጌው ስም ውግዘት ያደረጉት ካህናት ወታደር መስለው ከተቀላቀሉ በኋላ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ውግዘቱን የፈራው ሕዝብ እነሱን ተከትሎ በመንቀሳቀሱ 48 ሰዎች ተገደሉ ብዙ ሕዝብ አለቀ፡፡

ቄስ አምባው <u>ጉግሣ መጽሔት</u> ቅጽ 4 ቁጥር 1 ሐምሌ 1994 ዓም ገጽ 30 "ቀደም የሰማሁት ጨዋታ መምህሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መምከር እንዳለበት የሉቃስ ወንጌል ም/3 ቁ 11 ÷ሁለት ልብስ ያለው አንዱን ለሌላው ይስጥ! ምግብ ያለውም ለሌላው ያካፍል÷ የሚለውን በመያዝ ሲያስተምር ሚስቱ ትሰማለች፡፡ ከቤቱ ብዙ ልብሶች እንዳሉት ታውቅ ነበርና እርሱ ዘኬ ሊበላ ደጀሰላም ሲቆይ እርሷ ወደ ቤቷ ትሄዳለች፡፡

በዚያ ልብሱ ያለቀበት የቆሎ ተማሪ በእንተ ስማ ለማርያም ዕለእመብርሃን ብለው፤ብሎ የማርያምን ስም ይጠራል፡፡ ይች ሴት ቁራሽ ልትሰጠው ስትወጣ የለበሰው ልብስ ብጭቅጭቅ ያለ በመሆኑ ጥዋት የሰማችውን ትምህርት አስታውሳ የባልዋን ልብስ አንስታ ትሰጣዕች፡፡ ባል በሌላው ቀን ልብሱን ቀይሮ ሊለብስ ሲፈልግ ያን ልብስ ያጣዋል፡፡ ሚስቱን ይጠራና ልብሴን የት ጣልሽው? ብሎ ሲጠይቃት የሆነውን ትነግረዋለች እርሱ እኔ ሌሎችን አልኩ እንጂ መች የኔን አልኩኝ" ብሎ ካህኑ ሚስቱን መቆጣቱን አስመልክቶ ጽፈዋል፡፡

<u>የእሥራት ዘመን ባበሻ አገር</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 237 "አንዱን ቄስ በጢሙ ይዘው እናንተ ሃይማኖቱን ሊለውጥ ነው ትላላችሁ፡፡ ሃይማኖቴን እንድለውጥ የሚያስገድደኝ ኃይል ቢመጣ አስቀድሜ ራሴን እገድላለሁ ብለው ጦራቸውን በኃይል ከመሬት ላይ ቸክለው

ፎክረው የተቆጣ ሰው በሚናገረው ቃል አቡኑን ረገሙ" ሲሉ ሔንሪ ብላንክ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስን ሕዝቡ እንዳይከተላቸው ከፍተኛ ቅስቀሳ ካህናቱ አድርገዋል። ከላይ እንደገለጥኩት ከካህናቱ ጋር የተፈጠረው አለመግባባት ቀስ እያለ መኳንንቱና ካህናቱ በእርሳቸው ላይ ማበር ሲጀምሩ የአጤ ቴዎድሮስን ዓላማ በወሬ ይፈቱት ጀመር። ወሬ ከልክ ካለፈ መጥፎ ነው።

እንኳን የሰውን ልጅ ቀርቶ ወሬኞች ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያስተምረውን ትምህርት አጣመው ተርጉመው እንዴት እንዲሞት እንዳደረጉ ሐዲስ ኪዳንን ማንበብ ነው። ያውም እንደዛሬው ድኅረ ገጽና የነፋስ ድምጽ ሬዲዮ ጠማር ጋዜጣ በሌለበት ዘመን ሆኖ ነው እንጂ ከባድ ጠላቶች ነበሩባቸው። ይህ ሰነፍ የበስማም ቄስ እርሱ መሥራት ስለማይወድ የሚሠራውን እንዳይሠራ ሲገዝት ይውላል። ይትባረክ ግደይ ወሎ ክፍለ ሀገር ሰቆጣ አውራጃ በ1951 ዓም ገጠመኛቸውን እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል።

<u>የቅኔ ቤት ባህልና የሕይወቴ ገጠመኝ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 53-56 "መሪጌታ መልአኩ በተፈጥሮአቸው በጣም ትጉህ ሠራተኛ ከመሆናቸው የተነሣ በዓል የሚባል ነገር አያውቁም። ከቅዳሜና እሁድ በስተቀር ዛሬ አቦ ነው፤ነገ ሥላሴ ነው፤ተነገወዲያ ሚካኤል ገብርኤል የሚባል አያውቁም። አያውቁም ሳይሆን አያከብሩትም፤ እንጂ ማወቅማ ከሌላው ኅብረተሰብ በላይ ስለተማሩ የበለጠ ያውቁታል። እርሳቸው ሥራ ስለሚወዱ እሱም ከመጠን በላይ ይወዳቸዋል፡ ያከብራቸዋልም፤ የድካማቸውን ውጤት ይሰጣቸዋል። የፈለገ በዓል ቢሆን ከሥራቸው የሚያግዳቸው እምነትም ሆነ ኃይል አይኖርም የአካባቢው ካህናት ግን በየጊዜው ከፉኛ ይቃወሟቸዋል፡ ገዝተንሃል፤እንዳትንቀሳቀስ ዛሬ በዓል ነው ውጉዝ ከመአርዮስ ቃለ ሐዋርያ ነው እያሉ የተጠመዱትን በሬዎች ለማስፈታት ይሞክራሉ።"

"መሪጌታ መልአኩ ግን በምንም ዓይነት በቄሶች ውግዘት ሥራቸውን ያቆማሉ ማለት ዘበት ነው። የመንደሩ ካህናትም መልአኩ ሰይጣን ስለሆነ የዘራው እህል በረከተለት፤በረዶ ሳይነካው ቤቱ ገባለት፤ይህ የሰይጣን ምልክት ነው፤መሪጌታ መልአኩ ስሙ እንጂ ተግባሩ ፍጹም



ዲያብሎስ ነው ከእርሱ ጋር ማኅበር እንዳትጠጡ ቢሞት እንዳትቀብሩት፤ ከመልአኩ ጋር ጋብቻ የፈጸመ ጥቁር ውሻ ይውለድ እያሉ ስማቸውን ይበክሉታል። መሪጌታ መልአኩ ግን ለሁሉም ደንታ የላቸውም። ከዓላማቸውም ንቅንቅ ብለው ወይም በቄሶቹ አባባል ተበሳጭተው አያውቁም።"

"ታዲያ በአንድ ወቅት በአካባቢው የዝናብ እጥረት ያጋጥምና ረኃብ ይከሠታል። የመንደሩ ነዋሪ ሕዝብ ይቸገራል። በተለይም በክረምት ወራት ወቅት የሚበላ የሚቀመስ እህል ይጠፋል። በመሪጌታ መልአኩ ቤት ግን ቢያንስ የአምስት ዓመት የተከማቸ ጤፍና ስንዴ በተለያዩ ጎተራዎች እንደታሸጉ ናቸው። በዚህ ወቅት ቄሶችና ሕዝቡ በሰንበት ዕለት ከቤተክርስቲያን መልስ በአንድ ላይ ተሰብስበውና ተያይዘው ወደ መሪጌታ መልአኩ ቤት እህል ልመና ወይም ብድር ጥየቃ ይሄዳሉ።"

"መልአኩም ከቤተሰቦቻቸው ጋር በሞቀ ህድሞአቸው ወይም ቤታቸው ውስጥ ተቀምጠው ኮረፌ ጠላቸውን እየኮመኮሙ እንዳሉ የቤታቸው በር ተንኳኳና ከቅጥር ገበሬዎቻቸው አንዱ በሩን ከመክፈቱ በፊት ፈቃድ ጠይቆ ካስፈቀደ በኋላ ሰዎች እንዲገቡ ተደረገ። ምነው በደኅና መጣችሁ አሉ መሪጌታ መልአኩ፤ምን ደኅንነት አለ ብለው ነው?ተርበን እንጂ፤ልጆቻችን በረኃብ ሊያልቁ ስለሆነ እርስዎ እህል እንዲያበድሩን ብለን ነው የመጣነው፤ገብሱን ለስንዴ፤ስንዴውን ለጤፍ ባቄላውን ለገብስ ወይም ለስንዴ ለውጠን ለከርሞ እንድንከልፍዎት ቢፈቅዱልን አሉ ቄሶቹ እንደ ኀፍረት ነገር እየተሰማቸው።"

"ወቼ ጉድ አሉ መሪጌታ የቄሶቹን ሁኔታ እያሰቡና እየተገረሙ እኔ ብሰጣችሁ ወይም ባበድራችሁ ደስ ይለኛል፤ ሕዝብ እየተራበ ብቻዬን በልቼ ብቻዬን መኖር አልፈልግም። ግን እናንተ የግዝት አባቶች የበዓል አማልክቶች በበዓል የተሠራና የተዘራ የመልአኩን እህል እንዴት ትበላላችሁ? እንዴትስ ይዋጥላችኋል? ብለው የወቀሳ ጥያቄ ከጠያየቁና ከወቃቀሱ በኋላ ለሁሉም እንደአቅማቸው አከፋፍለው ሰጧቸውና ሐምሌና ነሐሴ በመልአኩ እርዳታ ወደ ጥጋብ ዘመን ስለደረሱ ከዚያ ቀን ጀምሮ መሪጌታ መልአኩን ማውገዝ አቆሙ" ሲሉ ጽፈዋል።

መሪጌታ መልአኩ ይትባረክ በወር በዓል ቀን ቢያርሱም የአካባቢው ሕዝብ ሲቸገር በእርሳቸው እህል የችግሩን ወቅት ማሳለፋን ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ ያስረዳል። እኒህ መሪጌታ ጥሩ የተማሩ በመሆናቸው የአካባቢውና የበስማም ቄሶች አድማ ሳይበግራቸው በመሥራታቸው ብዙ ሕዝብ ታድገዋል። መሪጌታ እንደ አካባቢው ካህን ቢሆኑ ኑሮ ለአካባቢው ሕዝብ መታደግ አይችሉም ነበር። እኒህ መሪጌታ በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ይሸለሙ ነበር።

ዛሬም ጠንካራ ካህናት ጠንክረው ወንጌልን ከዘሩ ልክ እንደ መሪጌታ ምእመናንን ይታደጋሉ። አለበለዚያ ግን ያው ከላይ እንዳነበብነው የአድማ ካህናት እንኳን ለእኛ ሊሆኑ ቀርቶ ለራሳቸውም አይሆኑም። ስለዚህ ካህናት በተለይም በስደቱ ዓለም ያላችሁ ተምትሜዎች ጠንቀቅ በሉ።

አጤ ቴዎድሮስ "ከሺህ ጦረኛ የቄስ ወሬኛ ይበልጣል" በማለት ተናግረዋል። መቼም ደግሜ ደጋግሜ በካህናቱ ላይ የምጽፈው ወድጄ ሳይሆን ዛሬም ያሉት ስለሚፈጽሙት ነው። ይህ የካህኑን ሴራ አጤ ቴዎድሮስ ጥሩ አድርገው ተረድውት ነበር። እርሳቸው ብዙ ተናግረዋል። ለምሳሌ ከተናገሩአቸው ጠቃሚ ቃላት መካከል ከላይ የምዕራፉ መጠሪያ የሰጠሁትና ሌላም እንዲሁ የተናገሩት አለ። "ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው ይበልጣል" ብለዋል።" እንዳይርቅህ መንፈስ ቅዱስ ብዙ ጊዜ አትቅረብ ወደቄስ" ብለዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ካህናትን የጠሉበት ምክንያት ብዙ ነው። ባለጌ በመሆናቸውም ጭምርት ነው። ብልግናቸውን አስመልክቶ አለቃ ተክለ ኢየሱስ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል። በነገራችን ላይ የግጥሙን ፍሬ ቃል ላም ሲጠብቅ ያላደገ ሰው ግር ሊለው ይችላል። ለማንኛውም የዚህ ምዕራፍ መደምደሚያ ላድርገውና ይህን ምዕራፍ ልዝጋው።

<u>የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 114 "ያን ወራት አባ ወልደ ሥላሴ የሚባል የደረቤ ቄስ የንስሐ ልጁን ለምዶ በሐሰት ሲቀድስ ክርስቶስ ገመናውን ገለጠበት። በሽሽጎት መሥረቁ ቀርቶ በክሡት አደረገ። ያውም ጆሮዋን በባልዋ እጅ አስይዞ በተንኮል የመጋኛ መድኃኒት ላደርግላት ብሎ ነው። የዚህ ጊዜ ባልዋ የተንኮል መሆኑን አውቆ ከሰሰው።"



"አደባባይ ወሰደው። ይህን ነገር ደጃች ተድላ በሰማ ጊዜ ተቆጣ። እንስሳ አሠርረህ ትከሳለህን አለና አባረረው። ያ ገበሬ ባልዋም የአደባባይ መሳቂያ ሆነ። አባ ወልደ ሥላሴም የወገን ማላገጫ ሆኑ።
ጫንቃ ሰበር ይዞ ሥረሩ ቢላቸው
አባ ወልደ ሥላሴ ምን ፍርድ አለባቸው፤
አባ ወልደ ሥላሴ ምናኔ ምናኔ፤
ቆብሁ ተግርግዳ አካላትሁ ተኔ!
እያለ ዘፈነባቸው" ሲሉ ጽፈዋል።

## ምዕራፍ 6

## አጤ ቴዎድሮስና ሸህ ሁሴን ጅብሪል!

ሼህ ሁሴን ጅብሪል በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን አብረው የነበሩ ናቸው። በወቅቱ አጤ ቴዎድሮስ ባወጡት አዋጅ ከተደሰቱት መካከል ሸህ ሁሴን ጅብሪል አንዱ ነበሩ። እርሳቸው ቃልቻ፤ጠንቋይ አይወዱም ነበር። የኢትዮጵያ ውድቀትም እንደ አጤ ቴዎድሮስ ያንገበግባቸው ነበር። በዚህም ምክንያት በአጤ ቴዎድሮስ በኩል ተደማጭነት የነበራቸው ታላቅ ሰው ነበሩ።

ምናልባት አንዳንድ አንባብያን ከዚህ በፊት በሰፊው ሳይጠቀስ ለምን ቀረ ይሉ ይሆናል። ጥያቄው ትክክል ነው። ለዚህ በወቅቱ የነበሩ ደራስያን ሳያልፉት አልቀረም። ነገር ግን የተጻፈም የለም ማለት አይቻልም። የተጻፈ መኖሩ ደግሞ ግልጽ ነው። ለዚህም ራሳቸው ሸህ ሁሴን ጅብሪል ከትንቢታቸው መጽሐፍ የአጤ ቴዎድሮስን ዘር ሳይቀር ጠቅሰውት ይገኛል።

ቦጋለ ተፈሪ በዙ <u>ትንቢተ ሸህ ሑሴን ጅብሪል</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 97 "ቴዎድሮስ ለጋስ ነው ቸርነት አያጣም
ማንም ያሞኘዋል ያሳዝናል በጣም
ለእስላምም ደጉና ነው እስላምም አይጎዳም
ራቅ ይላል እንጂ እስላም ዘር አያጣም" ሲሉ ተናግረዋል።

ሼህ ሁሴን ጅብሪል ወሎ ክፍለ ሀገር ወረሂመኖ አውራጃ ባዙራ ምክትል ወረዳ በባሆች ቀበሌ እምበለ ሴዳ በ1811 ዓም ተወለዱ።

ሸህ ሁሴንና አጤ ቴዎድሮስ የተወለዱበት ዘመን አንድ ነው:: ምናልባት ወሩንና ቀኑን እንጂ ዓመቱ አንድ በመሆኑ አብረው የሠሩ ናቸው:: ሸህ ሁሴን የማይወዱት አጤ ዮሐንስን ሲሆን ቄሱ አጤ ሳያስተምሩ እስላሙን በማጥመቃቸው ምክንያት ሸህ ሁሴን ከፍ ተብሎ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 34

"ደረሱብን እንጂ መች ደረስንባቸው
ቁረቡ ይሉናል የነፍስ አባታቸው" ሲሉ ተናግረዋል::

ሸህ ሁሴን ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ብቻ ሳይሆን ከመምህር አካለወልድ ጋር በጣም ይግባቡ ነበር:: ሁለቱም ምሁራን በየጸሎት ቤታቸው ቆይተው ይገናኙና ብዙ ያወሩ ነበር:: ይህን ታሪክ በልጅነቴ አባ የሱፍ የምንላቸው ሽማኄ ከጓሯችን ሽማቃ ዘርግተው ይሠሩ ነበር:: በተለይ ከብዙ ፈተና በኋላ በ1973 ዓም ወደ ትውልድ መንደሬ ስመለስ ከእርሳቸው ጋር ቁጭ ብለን ስንጫወት እንውል ነበር::

ዛሬ ራሱን ችሎ መጽሐፍ የተጻፈላቸውን የሸህ ዘካርያስ የኋላውን የአለቃ ዘካርያስን ታሪክ አንድ ባንድ ዘርዝረው ነግረውኛል:: ታዲያ አባ የሱፍ ከአባታቸው የሰሙትን የሸህ ሁሴን ጅብሪልንና የመምህር አካለወልድን ታሪክ እንዲህ ሲሉ አጫውተውኝ ነበር::

አባ የሱፍ "ሁለቱ ከጸሎት ቤታቸው ከቆዩ በኋላ ሁሌም ይገናኛሉ:: ታዲያ አብረው ሲሄዱ የእስላም ሸህና የክርስቲያን መምህር አይመስሉም ነበር:: በዚህ ወቅት ደብተሮች ቀኑና ሊያጣሏቸው ፈለጉ:: ያልተባለ ነገር እየነገሩ ቢደክሙም መግቢያ ቀዳዳ አጡ:: በመጨረሻ ሊጣሉበት የሚችሉት በሃይማኖታቸው ስንመጣባቸው ነው ብለው አንድ ቀን ሁለቱ ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ቆይተው ሲወጡ አለቃ ፈንታ የተባሉት በኋላ በአጤ ቴዎድሮስ የተገደሉት እንዲህ ሲሉ ጠየቋቸው ሼህ ሁሴንን ፥ሸሁ ክርስቲያን ነው እስላም የሚጸድቅ፥በማለት ጠየቋቸው:: የአለቃ ፈንታ ሴረኝነት ሼህ ሁሴን እስላም ነው የሚጸድቀው ሲሉ መምህር አካለወልድ ደግሞ ክርስቲያን ነው ይላሉና ይጣላሉ ብለው አስበ ነበርና ይህን ጥያቄ ያነሡት:: ነገር ግን ሼህ ሁሴን ጅብሪል ይህን ሲሉ መለሱላቸው::"

"ከሁለቱ አንዱ ይገባል ገሐነብ
በተለይ ደብተራ ይሆናል የሚንገበገብ



ብለው አሳፈሩአቸው::"

"ልክ ዛሬ ተቆጥቶ መጥቶ ሰድቦኝ እንደሚሄደው ደብተራ ፈቃዱ የአክስትህ ልጅ ባል ዓይነት ደብተራ ነበሩ:: አለቃ ፈንታ አጤ ቴዎድሮስ ደብታቦር መድኃኔዓለምን አሠርተው አለቃ ይህ ቤተ ክርስቲያን ይበቃ ይመስልሃል ሲሉአቸው አለቃ ፈንታ ጃንሆይ መችም ለሁለት ቄስና ለሦስት ሰሞነኛ ይበቃል አሉአቸው:: ኋላም እንዲሁ አጤ ቴዎድሮስ ወዳጅ መስለዋቸው አንድ ቀን አለቃ ይህ ካህናትና ደብተራ ሁሉ ጠገበኮ ቢሉአቸው አለቃ ፈንታ ጃንሆይ ጠግቦ መሬት ለቆ በማለት ተናግረው የተገደሉ ናቸው::"

ደብተራ ሲባል ነገረኛ ነው:: ልክ አለቃ ፈንታ ሼህ ሁሴንንና መምህር አካለወልድን ለማጣላት ጥሮ በሸሁ መልስ አፍሮ ተመልሶ ነበር ኋላ ግን ተቅለብልቦ አጤ ቴዎድሮስን በመጋፋቱ ተደብድቦ ተገሏል" በማለት ሠፋ አድርገው ታሪክ ጠቅሰው ለልጃቸው ለወንድማገኝና ለእኔ ይነግሩን ነበር:: መምህር አካለወልድና ሸህ ሁሴን ጅብሪል የኢትዮጵያ አንድነት መደፈር የሚያንገበግባቸው ምሁራን ነበሩ:: ለዚህም ሁለቱ አንድ ከብት አርደው ሥጋውን ተካፍለው በልተዋል:: ለዚህ መሠረቱ ደግሞ ለአገር አንድነትንና ለሃይማኖት ነፃነት ሁለቱም የሃይማኖት አባቶች ከአጤው ጋር ተስማምተው መሥራታቸው ዋና ምልክት ይመስለኛል::

<u>የመምህር አካለ ወልድ የሕይወት ታሪክ እና ቅኔዎቻቸው</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 33 "አጤ ቴዎድሮስ ለእስላምና ለክርስቲያን አንድ በሬ ሲሰጡ ማን ያረደውን ማን ተካፍሎ ለመብላት ችግር ተፈጠረ:: ግን መምህር አካለ ወልድ እስላሙ ይረደው አሉና ታርዶ እኩል የተከፈለውን ሥጋ በስመአብ ብለው በመስቀል ባርከው በካራ እንደ መቁረጥ አድርገው ለካህናቱ ሰጥተዋል" ተብሎ ተጽፏል::

መምህር አካለ ወልድና ሸህ ሁሴን ጅብሪል አብረው ለኢትዮጵያ አንድነት ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር የታገሉ አባቶቻችን ነበሩ:: የመምህር አካለ ወልድ ታሪክ አልደበዘዘም በስማቸው ትምህርት ቤት ተሠርቷል:: ነገር ግን እየደበዘዘ የመጣ የሸህ ሁሴን ጅብሪል ተግባር ነው:: ለኢትዮጵያ አንድነት ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር አብረው የታገሉ መሆናቸው በሰፊው አልተብራራም:: እኒህ እንቁ የኢትዮጵያ ልጅ ተግባራቸው እንዳይጠፋ በስማቸው አንድ ተቋም ሊመሠረትላቸው

ይገባል፡፡ ሼህ ሁሴን ጅብሪል ለአገር አንድነት የለፉ መሆናቸው በወቅቱ ጠንከር ብሎ አልተመዘገበም፡፡ ለወደፊቱ ያለው ትውልድ በሃይማኖት አሳቦ ሳይሆን በአገር ወዳድነት መንፈሳቸው በስማቸው ተቋም ሊመሠረትላቸው የሚገባ አገር ወዳድ አባት ናቸው፡፡

እንደእርሳቸው ዓይነት ጠንካራ አባት ኑሮ ቢሆን ኑሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለት ሞሰብ ማቅረብ አይገደድም ነበር፡፡ አጤ ቴዎድሮስም "ክርስቲያኑንና እስላሙን በአንድ ሰደቃ ያላበላሁት እንደሆነ የመይሳው ልጅ አይደለሁም" በማለት ይፎክሩ ነበር፡፡ ለዚህም በሁለቱ የሃይማኖት አባቶች አማካኝነት አንድ በሬ ለሁት በልተዋል፡፡ እስኪ በየትኛው ዓለም ነው ክርስቲያንና እስላም ለየብቻ የሚያርድ? ይህ መቅረት ያለበት መሆኑን ዛሬ ደፍሬ ልጽፍ ተነሣሁ፡፡

ሱዳን አገር በመጀመሪያ ስንገባ አልለመደን ብሎ ነበር፡፡ እኔ በተለይ ለ4 ወራት አልተዋጠልኝም ነበር፡፡ ገዳሪፍ ከሚባለው ከተማ ከግብጾች ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም እሄድ ነበር፡፡ ታዲያ ቄሱን አውቃቸው ነበርና አንድ ቀን ከሥጋ ገበያው ሳልፍ እርሳቸው ሲገዙ ተመለከትኩኝ፡፡ ለሌላ ሰው መስሎኝ ነበርና ቀረብ ብዬ ብጠይቃቸው ለራሳቸው እንደሆነ አስረዱኝ፡፡

ለማንም አልተናገርኩምና አፍሬ ዝም አልኩኝ፡፡ ከዚያ ወዲያ ችግሩ ባሰብኝና ሥጋ ገዝቼ መብላት ለመድኩኝ፡፡ ካርቱም ከሄድኩኝ በኋላ ደግሞ አርመኖችም እንዲሁ ሲሉ ተመለከትኩኝ፡፡ አሜሪካ መጥቼም እስላሞች ከገበያው ሥጋ ገዝተው እንደሚወስዱና እንደሚበሉ አስተዋልኩኝ፡፡ የኢትዮጵያ እስላሞችም እንዲሁ በእኛ የታረደውን ሁሉ አብረን እንበላለን ይህ ከሆነ ለምን ነው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚለያዩት?

መጽሐፍ ቅዱስ ሆነ ቅዱስ ቁርዓን "ለባዕድ አምልኮ የታረደውን አትብሉ" ይላል እንጂ ክርስቲያን ያረደውን አትብሉ አልያም ደግሞ እስላም ያረደውን አትብሉ አይልም፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ እስላሞችና ክርስቲያኖች ከሌሎች አገር የተለዩ የሚያደርጋቸው አንድ ከብት አርደው አብረው አለመብላታቸው ብቻ መሆኑን ተረዳሁ፡፡ ይህን አስመልክቶ ደግሞ ቀደሰ ዓለማየሁ ሞገስ ደርሶ በጥብቅ ይነቅፉታል፡፡



ቀደሰ ዓለማየሁ ሞገስ ደርሶ ሁሉም ሁሉን ይወቅ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 226 "ክርስቲያኑ የእስላም፤እስላሙ የክርስቲያን ሥጋ አንበላም የሚሉ ሰዎች በሀገራችን በኢትዮጵያ ብቻ እንዳሉ የታወቀ ነው፡፡ ይህም ለመለያ፤ለመለያያ ለመጣያ ብለው ሰርባቾች የፈጠሩት እንጂ በሐዲስ ኪዳንም ሆነ በቁርዓን ክርስቲያን ያረደውን ስላም፤እስላም ያረደውን ክርስቲያን አይበላም የሚል የለም፡፡ ምንም እንኳ ቅዱስ ጳውሎስ ኅሊናው ደካማ የሆነን ሰው ላለማዳከም ለጣዖት የታረደ ለደካማው ወንድም ኅሊና ስትል አትብላ ቢልም፤ ክርስቲያንና እስላም ለጣዖት ስለማያርዱ ወይንም ስለማይሠዉ የእስላም ሥጋ አትብሉም ብሎ ማወጅ ልክ አይደለም፤ (1ቆሮ 8)ስለዚህም አንዳንድ ሰዎች መላ ምት የመሰለ ተረት ይሰጣሉ፡፡"

"እስልምና ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ክርስትና በደጋው ኢትዮጵያ ነበረ፡፡ እስልምና ቆላ ቆላውን እየሰበከ ወደ ደጋው ኢትዮጵያ ወደ ትግሬ ወደ አጋሜ እነ መሐመድ ነጋሽ ወደሚገዙት ብቅ ሲል በቆላው ለቆሌ፤ለአድባር፤ለአውሊያ፤ለዛር ለጋኔን የሚታረደውን አንበላም ብለዋል ክርስቲያኑም እኛም ለቆሌ ለአድባር አንሠዋም የምንባርከው በስመ እግዚአብሔር ነው ብለዋል፡፡"

"ቢሆንም መሐመድን ካልተቀበላችሁ ያረዳችሁትን አንበላም ብለው እስላሞች እምቢ ስላሉ ክርስቲያኖችም ግም ሲሉት ጥምብ አይል የለምና እኛም የእናንተን አንበላም በማለታቸው መለያያ ሁኖ ቀርቷል፡፡ በኋላም ገዥዎች ለማለያየት ይረዳናል ብለው ስለደገፉት በጎጋው ሕዝብ ዘንድ ጸድቆ ቀርቷል፡፡ ሃይማኖቱ ጽኑ የሆነ ክርስቲያን ሁሉ ማንም ይረደው፤ያዘጋጀው ሳይጠይቅ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ባርክልን ብሎ መብላት ይችላል፡፡"

"ይህ ካልሆነ ግን የሚበላው እህል የሚለብሰው ልብስም ሊያረክሰው ስለሚችል እስላም የነካውን፤ የሠራውን ክርስቲያንና ክርስቲያን ያበጀውንም ብዙ እስላም መልበስ መብላት የለበትም፡፡ እዚህ ላይ የሚገርመው የኛ ጳጳሳትና ሸሆች በዓለም ሲዞሩ ያገኙትን ሳይጠይቁ እየባረኩ ይበላሉ፡ እስላሙም ክርስቲያኑም ስመ እግዚአብሔር እየጠራ ሲበላ ያያሉ፡፡ ወደ ሀገራቸው መጥተው ግን ሸሁም ጳጳሱም በዚህ አንጣላም አትጣሉ ብለው አያውቁም፡፡ በልማድና በማይረባ ተረት መጣላት ማንንም አይጠቅምም" ሲሉ ጽፈዋል፡፡

በአጤ ቴዎድሮስ መንግሥት ብዛት ያላቸው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ሲሠሩ የነበሩ ናቸው:: ዛሬ አንዳንድ አክራሪ የሆኑ ግለሰቦች አጤ ቴዎድሮስን ፀረ እስላም አድርገው ቢያቀርቧቸውም ታሪክ ግን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው የቴዎድሮስን መንግሥት ለማጠናከር የደከሙ መሆናቸው አይዘነጋም:: ከታሪክ መጽሐፍት አንዳንድ የለቀምኳቸውን የግለሰቦች ስም ሰብሰብ ላድርጋቸው ከዚህ ምዕራፍ ላይ:: የሃይማኖቱን ጉዳይ አስመልክቶ ሸህ ሁሴን ጅብሪል ዋናው ነበሩ:: በመንግሥት አስተዳደርና በወታደራዊው መስክ ደግሞ ከዚህ የሚከተሉት ከብዙ በጥቂቱ ልመዝግባቸው::

| | |
|---|---|
| 1ኛ ራስ አዳሉ መስጠፋ | 2ኛ ደጃዝማች ይመር አሊ |
| 3ኛ ፊታውራሪ ሀሰኔ | 4ኛ አቶ መሐመድ ሰይድ |
| 5ኛ ባሻ ለምለሜ መሐመድ | 6ኛ አቶ ሞአሊም ማቴ |
| 7ኛ አቶ መሐመድ ሠራዊት | 8ኛባሻ ጣህር ቃሲም ይገኙበታል:: |

## ምዕራፍ 7

### "እንዳይርቅህ መንፈስ ቅዱስ ብዙ ጊዜ አትቅረብ ከቄስ"

አጤ ቴዎድሮስ "እንዳይርቅህ መንፈስ ቅዱስ ብዙ ጊዜ አትቀረብ ወደ ቄስ አሉ"ለምን ይሆን ይህን ቃል የተናገሩት? የአጤ ቴዎድሮስ አነጋገር ምንን ይገልጻል? ወደ ካህናት በጣም መጠጋት ከእግዚአብሔር ይለይሃል ለማለት ነው:: እንግሊዞችም ይህን አባባል ይጋሩታል:: የአጤ ቴዎድሮስን አነጋገር በራሴ ትርጉም ከሆነ ከካህናት ጋር በብዛት የምትቀርብ ከሆነ እነርሱ የሚሠሩትን ሥራ አይተህ ሃይማኖትህን ትጠላለህ! ያ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ ይርቅሃል ማለት ይመስለኛል::

ካህናት ያጠፋሉ ለምሳሌ የቤተ ክርስቲያን ልዩነት የተጀመረው በካህናት ምክንያት ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመረጣቸው 12 ደቀ መዛሙርት መካከል ይሁዳ በ30 ብር ጌታችንን የሸጠ ሲሆን አልግባባ ብለው በ51 ዓም የመጀመሪያው ርክበ ካህናት አልያም ሲኖዶስ በሐዋርያት የተደረገው በመካከላቸው ሰላም



ባለመኖሩ ምክንያት ነው:: ይህን ስብሰባ የመራው ሐዋርያው ያዕቆብ ሲሆን በተለያዩ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አባቶች አልግባባ ብለው ልዩነታቸው በርትቶ ዛሬ በዓለም ላይ ያለው አንዱን መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው ስማቸው ክርስቲያን ተብሎ ብዛታቸው ከ1200 በላይ እንደሆነ ይገመታል:: ጉባኤዎችም የተደረጉት በቀሳውስት ክህደት ነው:: እንዲያውም ንስጥሮስማ ፓትርያርክ ነበር::

የቅርቦቹ ካህናት ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ አባታቸውን ወንጅለው ደብዳቤ የጻፉና፤የከሰሱትን ስም ጠቅሼ ባለፈው በጻፍኩት በአባ ጳውሎስና በጳጳሳት ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ላይ የተነሣው እሳት በተባለው መጽሐፍ የገለጽኩት ዋቢ ይሆናል:: ዛሬ በስደት ዓለም ባለችው ቤተ ክርስቲያን በየቦታው ተካሰው ፍርድ ቤት እየሄዱ ናቸው:: ካህናት የግል ጥቅማቸው እንዳይቀርባቸው ሕዝቡንና እርሳቸውን ለማጣላት የማይፈነቀል ደንጊያ የለም:: ደግሞም "ገለልተኛ ነኝ" የሚሉ ካህናት ናቸው:: ገለልተኛ ብሎ የሃይማኖት መሪ ሊኖር አይችልም በእኔ እምነት::

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ <u>የተወደደችውን የጌታን ዓመት እንስበክ</u> በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 4 "የሚበላ የሚጠጣ ሰው በእምነት በአገር በሕዝብ ላይ ከሚደርሰው ችግር ሁሉ ገለልተኛ ነኝ ማለት እሬሳ ነኝ ማለት ነው" ሲሉ ጽፈዋል:: እውነትም *ሬሳ ነው:: የሰስማም ቄሶች ዛሬም ቢሆኑ በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን እንደነበሩት እንዲያውም* ሳይብሳቸው አይቀርም:: በስደቱ ዓለምማ በጣም እንጂ ሁሉ በስደተኛው ቤተ ክርስቲያን ላይ በደል እየፈጸሙ ናቸው::

ዛሬ ሥልጣኔው ባደገበት ወቅት እንኳን ለሃይማኖት እድገት ከሚያደርጉት መሯሯጥ ይልቅ ለግል ጥቅማቸው ሲስገበገቡ ይታያሉ:: አጤ ቴዎድሮስ ሆኑ፤አጤ ዮሐንስ ሌሎችም ነገሥታት የደከሙላት ተዋሕዶ ሃይማኖት በእኛው ካህናት እየደከመች ናት:: በቅርቡ የገባው ሃይማኖት በአጭር ጊዜ እድገት እያሳየ ሲመጣ ተዋሕዶ ሃይማኖት እየደከመች መጥታለች:: ይህን ድክመት አስመልክቶ እኔ ከምጠቅሰው ይልቅ በ2001 ዓም የብፁዕ ወጣያት አቡነ ጳውሎስ ሲኖዶስ ያመነበት መሆኑ አይዘነጋም::

ደጀሰላም ድረገጽ <u>ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን</u> ላይ የፈጸሟቸው ዐበይት ችግሮች በተባለው ሰፋ ያለ

መጣጥፍ ገጽ 4 “በዘመነ ፕትርክናቸው ከምንጊዜውም በላይ የስብከት አገልግሎት መዳከሙ ብቻ ሳይሆን መጥፋቱ ግልጽ ነው:: ለዚህም አንዱ ማሳያ ቤተ ክርስቲያን በሀገር አቀፍ ደረጃ ያላት የምእመናን ቁጥር መቶኛ ድርሻ በተዓምራዊ ፍጥነት እየቀነሰ መምጣቱ ነው:: በአንጻሩም የሌሎች እምነት ተከታዮች በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ መሆኑን የ1999 እና 2000 ዓም ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት በግልጽ እያሳየን ነው” ሲል ጽፏል::

ጃን ያንግ <u>መብረቅ ጋዜጣ</u> ሐሙስ ሐምሌ 8 ቀን 1991 ዓም ገጽ 8 “በጋምቤላ ውስጥ በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ መሠረት 71.500 ሰባ አንድ ሺህ አምስት መቶ የጴንጤ ቆስጤ እምነት ተከታዮች እና 39.000 ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ የኦርቶዶክስ እምነት አማኞች ናቸው” ሲል ጽፏል:: ተመልከቱ ይህን ያህል ሌሎች አማኞች እድገት ሲያሳዩ የኛው የተዋሕዶው ቤተ ክርስቲያን ያለበትን ድክመት ያሳያል::

ታዲያ ቤተ ክርስቲያንን እናስፋፋለን ምእመናኑን በሕገ እግዚአብሔር እንመራለን ብለው ቃል የገቡላትን ቤተ ክርስቲያን ሲያደክሙ ማየት ምን ያህል ሰነፎች እንደሆኑ እያየን ነው:: በዚህ በ2003 ዓም ከአንድ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ የቀረበው ውይይት “የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ቁጥር 8 ሚልዮን ቀንሷል:: ቁጥሩ በአደባባይ እንዳይነገር ተደብቋል በማለት ተነግሯል ይህ ድክመት ሊመጣ የቻለው ሰነፍ እረኞች በመብዛታቸው ምክንያት ነው:: የዚህን አይነት ካህናት ነው አጤ ቴዎድሮስ “ወገቡን ሰባቂ አታደግድግ” ይሉት ነበር::

ዛሬ ስገምተው ክህነቱ ቢኖረኝ በምድረ አሜሪካ ካለው የበስማም ቄስ አላንስም ነበር:: በእኔው አቅም ስገምታቸው ባዶ ናቸው:: ዛሬማ አሜሪካ ያሉትን ካህናት ከግማሽ በላይ የሚሆኑትን በተለያዩ ምክንያት ቀርቤ አቅማቸውን ገምቸዋለሁ:: ዘመናዊ መምህር ናቸው ቢባሉም እንኳ ከዚያው አልወጡም:: ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ዐርፈው ለፍትሐተ ጸሎቱ በምድረ አሜሪካ ካሉት ቤተ ክርስቲያን የብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ ልጆች ካልሆኑ በቀር ሌሎች መጥተው ነበር::

ግማሽ ሌሊት ላይ ገና አስከሬን ሳይገባ ቀድሜ ገብቼ ነበር:: ታዲያ ካቦርትና ከራባት የደረበው መስቀሉን በኪሱ የደበቀው ካህን



ለአስተናጋጅ አስቸግሮ ነበር:: ይህን ሳይ ቆይቼ የሌሊቱ ጸሎት ሲጀመር ጸናጽል ሲጨበጥ የበስማም ቄሶችና ምሁራኑ ተለዩ:: ጉድ ሆነ! ይህ ግትልትል ቆብ የጫነው መነኩሴና ቄስ ነኝ ብሎ ካቦርት የደረበው ሁሉ እርጥብ ተደረቅ ተለየ:: ጸናጽሉን በጁ ይዞ አፉ ሳትከፈት ዝምታን መርጦ አስተዋልኩኝ::

ታዲያ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስና ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ፤ ከሳንዲያጎ የመጡ ወጣት መሪጌታ ነቢዩ እጃቸው ከጸናጽሉ ጋር ሲወረወር ሌላው ዲዳ ሲሆን አይቻለሁ:: ቅኔ ሲዘራ ግን ቁጥራቸው በርከት ብሎ ነበር:: ለካስ የዚህ ዓይነት የበስማም ቄስ በዝቶ ኑሮአል አጤ ቴዎድሮስን አስቸግሮአቸው የነበረው:: አይኔ ጉድ አየ፡ እርጥብ ተደረቅ ሲለይበት:: የሚገርመው ነገር ደግሞ አሜሪካ ያሉ ካህናት ስጡን እንጂ በቃን አያውቁም::

የትምህርት ሲዲ ሌላም ሌላ ማዘጋጀት ጀምረዋል:: በዚህ መመስገን ይገባቸዋል:: በርቱበት አይዟችሁ እላለሁ:: ታዲያ የነሱን መሸጥ የሌሎችን በነጻ መቀበል ይወዳሉ:: ይህም እኮ ትክክል አይደለም:: ከምእመናን የሚዘጋጁትንም እኮ ከፍላችሁ መውሰድ አለባችሁ:: ነጻ አትውሰዱ እኔ የብዙ ካህናት ስም ዝርዝር በእጄ ይገኛሉና አስበበት:: እንዲያውም እናንተ የምታዘጋጁት ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዝ ከሆነ ነጻ መታደል ነበረበት::

<u>ማቴ 10፤5</u> “እነዚህን አሥራ ሁለቱን ኢየሱስ ላካቸው፤አዘዛቸውም፥ እንዲህም አለ፤በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፥ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ፤ይልቅስ የእስራኤል ቤት ወደሚሆኑ ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ፡እንጂ:: ሂዳችሁም መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ፡ ድዉዮችን ፈውሱ፡ሙታንን አስነሡ ለምጻሞችን አንጹ፤ አጋንንትን አውጡ በከንቱ ተቀብላችሁ በከንቱ ስጡ::

ወርቅ ወይም ብር ናስ በመቀነታችሁ ወይም ለመንገድ ከረጢት ወይም ሁለት እጀ ጠባብ ወይም ጫማ ወይም በትር አታግኙ” ይላል:: ስለዚህ እናንተ የእግዚአብሔር ቃል የምታስተምሩበትን ክር ደመወዝ የሚከፍላችሁ ቤተ ክርስቲያን ሰብስቦ አባዝቶ ሽጦ ለቤተ ክርስቲያን ገቢ ማድረግ ሲገባ እናንተ ቆማችሁ ያስተማራችሁበትን ሰብስባችሁ ለምእመናን ትሸጣላችሁ::

ይህ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቶያን ሥርዓት ሳይሆን የፕሮቴስታንት ሥርዓት ነው:: ሣታውቁት የፕሮቴስታንትን አሠራር በተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያስገባችሁ ነው:: ዛሬ እሁድ ቁሞ ያስተማረውን ስብከት በክር አዘጋጅቶ ለገቢያ ማቅረብ ዋናው ትልቁ ገቢ ሁኖአል:: ለምሳሌ አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ የሚያስተምሩት ትምህርት ተራብቶ ለምእመናን የሚያቀርቡት ቤተ ክርስቲያን እንጂ በእርሳቸው አማካኝነት አይደለም::

የእርሳቸው ፍላጎት ትምህርቱ ለምእመናን መድረሱ ብቻ ነው:: ይህ ነው የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እንጂ ምጣኔ ሀብት ለመሰብሰብ በግል መስገብገብ ትክክል አይደለም ጥንቃቄ ይደረግበት:: ለካ የዚህ ዓይነት ካህናት በዝቶ ነው አጤ ቴዎድሮስን ሲያበሳጫቸው የነበረው::
አጤ ቴዎድሮስ አገራቸውን ለማሠልጠን ከፍተኛ የሆነ ፍቅር ኑሮአቸው ሲነሡ ግንባር ቀደም ወሬኞች የበስማም ቄሶች ካህናት ነበሩ ለእርሳቸው ጠላት የሆኑት:: ለዚህም ነበር አጤ ቴዎድሮስ "ታግዬ ያልጣልኩት የቄስን ጠብ ነው" ያሉት በልጅነታቸው የቄስ ትምህርት የተማሩ ከመሆናቸው በላይ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ስማቸው ያልተጠቀሰው መነኩሴ ጥሩ አድርገው አስተማሩአቸው::

እርሳቸውም የቄሱ ተንኮል አልጠፋቸውም ሁኖም ካሸነፋቸው መካከል ካህናት መሆኑ ራሳቸው ተናግረዋል:: የካህናቱ አድማ ግቡን የሚመታው ለምንድነው? በዛን ሰዓት ይቅርና ዛሬ ድረስ ካህናቱ የጠሉትን የሚያስጠሉበት ዘዴ ብዙ ነው:: የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ ሳነብና ዛሬ የማያቸውን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ተግባር ሳጤን እውነትም ቄስን ታግሎ መጣል አይቻልም:: ምክንያቱም ቄሶች የሚናገሩት ሁሉ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አለው::

ቄሶች አጥፍተው ሌላውን አጥፊ አድርገው ያቀርባሉ:: ከዚህ በፊት በጻፍኩት መጽሐፍ "የበስማም ቄሶች"አልክ ብለው የተወሰኑ ምእመናን ወቀሱኝ ለነገሩ አልረዳቸው ብለው እንጂ እንደ ካህን አድመኛና ሴረኛ የለም:: የቤተ ክርስቲያን ምእመን ሳያጠፋ አጥፊ ተብሎ ልጅ ቢወልድ ክርስትና አይነሣለት ሰርግ ቢያደርግ አይባረክለት ለምን ተብለው ሲጠየቁ ከማስረዳት ይልቅ በደፈናው አጥፍቷል ብለው በሩን ይዘጋሉ:: እነሱ የወደዱትን ባላቸው ሥልጣን ተጠቅመው ለማስታረቅ ጥረት ሲያደርጉ እነሱ የተጣሉ እንደሆነ



ታረቁ ሲባሉ ፈጽሞ ይላሉ ምእመናኑን በቀላሉ አሳምነው እነሱ የጠሉትን ግለሰብ ከኅብረተሰቡ አግልለው ያስጠሉታል::

<u>አቶ ሀብተ እንደነገሩኝ</u> "ቤተ ክርስቲያን አባል ሁኜ ሳለ የገንዘብ አቅም አንሶኝ መክፈሌን ካህኑ ያውቃሉ:: እሁድ እሁድ ሥለምስራ ቤተ ክርስቲያን አልሄድም:: ይህን ካህኑ አሳምረው ያውቃሉ:: ታዲያ አንዴ ስብሰባ ላይ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ላይ ውይይት ነበርና እኔ ስናገር ካህኑ ቅድሚያ እሁድ እሁድ ቤተ ክርስቲያን መሄድና አሥራት በኩራት የማይከፍል ሰው አስተያየት መስጠት አይችልም በማለት አሳፈሩኝ በማለት ነግረውኛል:: የዚህን ዓይነት ካህን ነበር አጤ ቴዎድሮስ "ሰነፍ እረኞች ስለሆናችሁ እግዚአብሔር ይፈርድባችኋል" ይሏቸው ነበር:: ታዲያ ለእንዲህ ያለ ካህን ሐጢያት ብሎ ቢነግሩት ፀሐይ ሳትገባ አገሩን የሰማሁት ብሎ ያዳርሰው የለም እንዴ?

<u>ት/ተ ሕዝቅኤል</u> ም÷34÷3 "እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? ጮማውን ትበላላችሁ ጠጉሩንም ትለብሳላችሁ የወፈሩትን ታርዳላችሁ በጎቹን ግን አታሰማሩም:: የደከመውን አላጸናችሁትም የታመመውንም አላከማችሁትም የተሰበረውንም አልጠገናችሁም የባዘነውንም አልመለሳችሁትም የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም በኃይልና በጭቆናም ገዛችኋቸው:: እረኛንም በማጣት ተበተኑ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ::" ይላል::

ቆኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ምእመናን ዛሬ ጠባቂ በማጣታቸው እየባዘኑ ናቸው:: በተለይ በዚህ በስደቱ ዓለም የቤተ ክርስቲያን ልጆች እየባዘኑ ናቸው:: ልዑል እግዚአብሔር ሁሉን የሚያይበት መነጩር እንዳለው ከእኛ ይልቅ እነሱ ያውቃሉ:: በዚህ በአሜሪካን አገር አንዳንድ ካህናት ከሰባካ ጉባኤው ከቦርድ ጋር ይመረጡና አብረው ይሠራሉ::

ታዲያ ካህኑ በስብሰባ ከሰበካ ጉባኤው ጋር አልግባባ ሲሉ አስቀድመው" እንዳትናገር አውግዝለሁ" እያሉ አንዱን ሁሌ ያበሳጩታል:: በአንድ የሃሳብ ፍጭት ላይ ሊናገር እጁን ሲያወጣ ቄሱ የተለመደውን ውግዘታቸውን ሲጥሉበት "እኔም በመሃይም ሙብቴ አውግዝዎታለሁ እንዳይናገሩ" ብሎአቸዋል:: ይህን ያህል ነው ምእመናን በስቃይ ላይ ያሉት::

# ምዕራፍ 8

## አጤ ቴዎድሮስን ቀደምም ዛሬም የሚወዱ ካህናት አሉ!

አጤ ቴዎድሮስ በነበሩበት ዘመን የነበሩ የሃይማኖትና ወታደራዊ ጀግና ስመ ጥር ሰዎችን ስንጠቅስ መምህር አካለ ወልድና ፊታውራሪ ገብርዬ በእስላም ሃይማኖት ሼክ ሁሴን ጅብሪል ቅድሚያ የሚጠቀሱ ናቸው:: ኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንት ወቅት በተለይም ቤተ ክርስቲያን ጠፍታ ነበር:: ይህን በመረዳት መምህር አካለ ወልድ አጤ ቴዎድሮስን በጣም ይወዱአቸው ነበር:: ለዚህም እርሳቸው የተቀኙት ቅኔ ዋቢ ነው:: ይህ መምህር አካለ ወልድ የተቀኙት ቅኔ ከዚህ በፊት በተለያዩ መጻሕፍት ተጠቅሶ ነበር:: አሁን ግን ራሱን ችሎ የመምህር አካለ ወልድ ታሪክ መጽሐፍ በመታተሙ ከዚህ በታች ጥቅስ ልውሰድ::

<u>የመምህር አካለ ወልድ ቅኔዎች</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 227
"ለሞት ወለሕይወት፣
ሥልጣን ብከ ቴዎድሮስ፣
እለ ኢተቀንዩ ለከ እስመ ልቃሐ ሞት ተፈድዩ፣
ወወረሱ ሀገረ ሕይወት ዘለከ ተቀንዩ::
አመኒ ተሰምዐ በዜና ነገረ ብሉይ አብድዩ
ተረፈ ኤልያስ ዘየሐዩ
እምጠለ ቤትከ ፍትሕ በዘይረውዩ፣
አስምዕ ሰብአ መሃይማነ አርያሃ
ወዘካርያስሃ ወልደ በራክዩ::"

ትርጉም ወደ አማርኛ
"ቴዎድሮስ ሆይ!
ለመግደልም ለማዳንም ሥልጣን አለህ፣
ለአንተ ያልተገዙ የሞት ብድራትን ተቀብለዋልና
ለአንተ የተገዙም የሕይወት ሀገርን ወርሰዋልና
በሕይወት የሚኖረው የኤልያስ ቅሬት የሆነው
የሽማግሌው አብድዩ ነገርም በዜና በተሰማ ጊዜ



ከቤትህ ጠል/ፍርድ ይረኩ ዘንድ
የታመኑ ሰዎችን/አርያንና
የበራክዩ ልጅ ዘካርያስን አስመስክር" ይላል ቅኔው::

የቅኔው ፍሬ ሐሳብ አጤ ቴዎድሮስ በሕይወትም በሞትም ላይ ሥልጣን ስላላቸው አሜን ብለው የተገዙት ሕይወትን ሲወርሱ እምቢ ተኞች የሞት ፍዳ መቀበላቸውን ከአርያና ከበራክዩ ከዘካርያስና ከአብድዩ ታሪክ ጋር እያመሳሰሉ አቅርበውታል:: ያጤ ቴዎድሮስ አነሣስ ለመሳፍንቱ አሣርና መከራ ሲያወርድ ለተርታው ሕዝብ በተለይ ለተበደለው ወገን ደስታ እንደሚያመጡ ተገምቷል:: ይኸንንም የሚያስረዳን በነገሡበት ቀን እንዲህ ብሎ የተቀኘው የአማርኛው መወድስ ቅኔ ነው:: ቅኔውን ካሣ ብሎ ነው የተቀኘው::

"ይበዝህ የበደልኸኝ አንተ
ምውተ ምግባር እኔን እግዚአብሔር ሕያው
ብንታረቅም አሁን በካሣ ነው::
ስጥተውኛልና ሥሳቤ ፈርደው
እህሉም በቅሉ እንዳይጠፋ
ዝናመ ምሕረት ካሣን
በኢትዮጵያ አዘንምኸው
አሁንም ስጠኝ ካሣዬን በጉልቆ ፍጡራን አኃው
ጉልቆ ዘመኑን ታውቃለህና ጉልቆ ዘመኑን አታጉድለው
ወእንበለ ካሣ ተዐረቀ ኢይበሉኒ አበው
ካሣ ለተበደለ ከጥንት የመጣ ነው::" ሲሉ ተቀኝተዋል::

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጭር ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 75 "በዘመነ መሳፍንት የተከፋፈለችውን ኢትዮጵያን አንድ በማድረግ የሚታወቁት ታላቁ ንጉሥ አጤ ቴዎድሮስ ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት ታላቅ አክብሮት ስለነበራቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን ጭቅጭቅ ለማስወገድ የበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል" ሲሉ ጽፈዋል:: ወጣት ካህናት የዛሬዎቹ የአጤ ቴዎድሮስን ተግባር የተቀበሉ ብዙ ናቸው::

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 76 "አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ከተዋሕዶ ሃይማኖት፣ተዋሕዶ ሃይማኖትን ከኢትዮጵያ ነጥለው የማያዩ

ሃይማኖታዊና ብሔራዊ መሪ ነበሩ:: በዘመናቸው በኢትዮጵያ የነበሩትን ሚሲዮናውያን ሁሉ ሰብስበው ኢትዮጵያ የራሷ የወንጌል መምህራን አሏት:: ይልቁንስ እናንተ የሠለጠናችሁበትን ለእኛም የሚያስፈልገንን ብረት ማቅለጥና መቀጥቀጥ ቴክኖሎጂ አስተምሩን ብለዋቸው ነበር" ሲሉ ጽፈዋል::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ አጤ ቴዎድሮስ ብሔራዊ መሪ መሆናቸውን ተረድተው ትውልዱ እንዳይረሳቸው ጽፈዋል:: ሰነፍ ካህናት ዛሬም ድረስ የሚጠላቸው መኖሩ አይዘነጋም:: ነገር ግን ከጳጳስ እስከ መነኩሴ ተዋሕዶ ሃይማኖት እንዲስፋፋ የሚፈልጉ ሁሉ ዛሬም ያከብሩአቸዋል:: የሚያከብሩአቸው ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዳትጎሳቆል የሚያስቡት ብቻ ናቸው:: ሆድ አምላኪዎች ካህናትማ ስማቸው እንዲጠራ የማይፈልጉ አሉ::

አባ ገሪማ (ዶ/ር) <u>የኢትዮጵያ ኦርቶቅዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር</u> በየዘመናቱ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 49 "የተወሰኑ ካህናት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ተገን አድርገው አጤ ቴዎድሮስን ሊያወናብዷቸው ቢሞክሩም አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ከተዋሕዶ ሃይማኖት ተዋሕዶ ሃይማኖትን ከኢትዮጵያ ነጥለው የማያዩ ሃይማኖታዊና ሀገርን ወዳድ ኢትዮጵያዊ መሪ ስለነበሩ በወንበዴዎች ሙከራ ሊበረግጉ አልቻሉም" ሲሉ ብፁዕ አቡነ ገሪማ ጽፈዋል::

እንዲያውም ብፁዕ አቡነ ገሪማ "በወንበዴዎች ሙከራ ሊበረግጉ አልቻሉም" ሲሉ ካህናት ወንበዴዎች መሆናቸውን ተረድተዋል:: በነገራችን ላይ ብፁዕ አቡነ ገሪማ ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ላይ ወንበዴዎች መኖራቸውን የመሰከሩ መሰለኝ:: ቤተ ክርስቲያን እንዳታድግ የሚያደርጉ ጳጳሳት መኖራቸውን በካህናት አስመስለው መግለጻቸው ነው:: ይህ ተግባራቸው ዛሬም እየታየ መሆኑን ከመሰከሩ ለወደፊቱ እባክዎ እውነትን ብቻ ይዘው ውሸትን ትተው እንዲሰብኩ ይሁኑ::

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓም</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 335 "የተወሰኑ ካህናት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ተገን አድርገው አጤ ቴዎድሮስን ሊያወናብዷቸው ቢሞክሩም አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ከተዋሕዶ ሃይማኖት ተዋሕዶ ሃይማኖትን ከኢትዮጵያ ነጥለው የማያዩ



ሃይማኖታዊና ሀገርን ወዳድ ኢትዮጵያዊ መሪ ስለነበሩ በወንበዴዎቹ ሙከራ ሊበረግጉ አልቻሉም" ሲሉ ጽፈዋል:: ለዚህም ነው ዛሬ ድረስ አገራቸውን የሚወዱ ካህናት አጤ ቴዎድሮስን የሚወዱአቸው::

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 267 "ከካህናቱ መካከል በጥቅማቸውና በክብራቸው መነካት የተነሣ ግማሾቹ ሲጣሉዋቸው ብዙዎቹ ደግሞ በዘመነ መሳፍንት የነበረውን የእርስ በእርስ ጦርነት የየአውራጃውን መከፋፈል በጎንደርና በደብረታቦር ከተማዎች የነበረውን ድሎትና ቅንጦት መበርከት በመመልከት ጠንከር ያለ ሁሉን ተቆጣጥሮ የኢትዮጵያን ስም የሚያስጠራ የማዕከላዊ መንግሥት መሪ በመጥፋቱ ይናደዱ የነበሩት የሊቃውንት ወገኖች በትንቢት የተነሡት ቴዎድሮስ የሚያደርጉትን ጥረት ከዘመናዊ ግንባታቸው ጋር በማያያዝ የሚገባ አድርገው ድጋፋቸውን እየሰጡ በወረብና በቅኔ የሚያበረታቷቸው ነበሩ::

ከነዚህም መካከል ቴዎድሮስ ራሳቸው ይማሩዋል እንደ አካልዬ ይዋጉዋል እንደ ገብርዬ ብለው ትምህርታቸውን ያደነቋቸው መምህር አካለ ወልድ ይገኙሉ:: እርሳቸውም ቴዎድሮስ የመግደል የማዳን ሥልጣን ከአምላክ እንደ ተሰጣቸው ለርሳቸው አልገዛም ያሉት የሞት (ኩነኔ)እንዳገኛቸው የተገዙላቸውን ግን መንግሥተ ሰማያትን እንደ ወረሱ ለማመልከት ሥላሴ ቅኔ ተቀኝተውላቸዋል::

"እንደዚሁም በደረስጌ ከእቴጌ ተዋበች ጋር ስለ መንገሣቸው የተነገረው ቅኔ::"
ተዋቡን ሲያገባ ሠርጉ መች ደመቀ፤
ደረስጌ ስናየው መልሱ አንጸባረቀ፤
ፊትማ ሲያገባት ተክሊል መች ነበረው፤
ካሣ ደረስጌ ነው በሕግ የተዳረው፤
ሊቃውንት ካህናት ካንድ ላይ በሙሉ፤
ጎንደር አልነገሠም ብለው ያድማሉ፤
በከንቱ ነው እንጂ በራስ ፍርድ ለማምጣት፤
ዘውዱ ከተሰራ ሆኗል ዐስር ዓመት፤
ለኢትዮጵያ ሲበጅ ካየነው፤
የነገሡበቱ ደረስጌም ጎንደር ነው"

ብለው ካህናቱ የተቀኙትን ወደ አማርኛ ተርጉመው ጽፈውታል:: ሌሎችም ካህናት በተለያየ ጊዜ ስለ አጤ ቴዎድሮስ ሙገሳ ቅኔ የተቀኙ መኖራቸው ከተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት መልቀም ይቻላል::

በበምእት ምእተ በዘመነ ሐጋይ መስፍን፤
ዘበቆለ በርእሰ መቅደላ ቴዎድሮስ ወይን፤
እምዘዚአሁ አስካል አምጣነ ጸግቡ በዐይን፤
እለ ጸዋምያነ ኮኑ አውሮፓውያን፤
እመቅደላ ከመ ይጹም እዝን::

ትርጉም
በመቅደላ ራስ
የበቀለ ቴዎድሮስ/ወይን በበጋ መስፍን
ዘመን በመቶ አፈራ
ከመቅደላ ጆሮ ይፆም ዘንድ
ጾዋሚዎችን የሆኑ የአውሮፓ ሰዎች
ከእርሱ ፍሬ በዐይን ጠግበዋልና::

ሞት ታቦተ ሕጉ ለወልድ
አፎ ተቀርፀ በዘቴዎድሮስ ዕድ

ትርጉም
የወልድ የህጉ ታቦት/ሞት
በቴዎድሮስ እጅ እንዴት ተቀረፀ

እያሉ ይቀኙላቸው ነበር:: አንዳንድ የቀድሞ ቤተ ክርስቲያን አፍቃሪዎች ካህናት የግል ጥቅም ሳያጠቃቸው የኢትዮጵያ አንድነት የሚጠበቅ ጠንካራ አጤ ሲነሣ መሆኑን ያምኑበት ነበር:: በዘመናችንም ቢሆን አጤ ቴዎድሮስን የሚጠሉ ካህናት እንዳሉ ሁሉ የሚወዱአቸው ካህናት ብዙ አሉ:: በቅርቡ የቤተ ክርስቲያን ምሁራን ለአጤ ቴዎድሮስ የፍትሐት ጸሎት ማድረግ አለብን ብለው የተነሡ እንደነበሩ በ1992 ዓም ገደማ በጋዜጦችና በመጽሔቶች ይጻፍ ነበር:: ምኒልክ መጽሔት ዶ/ር ሊቅ አባ ፍሥሐ ጽዮን ካሳ ያደረጉት ቃለ ምልልስ አጤ ቴዎድሮስን በሚመለከት የሰጡትን መልስ ከዚህ ዝቅ



ብዬ እጠቅሳለሁ:: የዘጋቢውን ጋዜጠኛ የመጀመሪያ ጥያቄ ካቀረብኩ በኋላ ጥያቄውን ትቼ መልሳቸውን እጽፋለሁ::

ዶ/ር አባ ፍስሐ ጽዮን ካሳ ምኒልክ መጽሔት ሚያዝያ 1993 ዓም ገጽ 19 ጋዜጠኛው 1ኛ ጥያቄ በቅርቡ እርስዎ በፕሬዝዳንትነት እየመሩ ያሉት ኢንተርናሽናል ድርጅት የአጤ ቴዎድሮስን ስም በቤተክርስቲያን በሥርዓተ ጸሎት እንዲነሣ ቅዱስ ሲኖዶሱን ጠይቃችኋል ለዚህ ያገኛችሁት መልስ ምንድነው? መልስ ዶ/ር አባ ፍስሐ ጽዮን ካሳ፤ " አዎን እኛ በበኩላችን የአጤ ቴዎድሮስ ስም በሥርዓተ ጸሎት ፍትሐት እንዲነሣ ወስነናል::"

"በጀርመን በእንግሊዝ፤በቻይና እንዲሁም በእስካንዲኒቫያ ሀገሮችና በአሜሪካ ያሉ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ስለዚህ ጉዳይ በደንብ ከተነጋገርን በኋላ ነው የወሰነው:: የውሳኒያችን ደብዳቤ ለቅዱስ ሲኖዶስ ለሊቃውንት ጉባኤና ለጠቅላይ ቤተ ክህነት እንዲሁም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ለባህል ሚ/ር ለነጻው ፕሬስ ሰጥተናል::"

"በፓትርያርኩ በኩል ግን እስካሁን ያገኘነው መልስ የለም:: 2ኛ እኛም በዚህ ጉዳይ ላይ በሰፊው ተነጋግረናል:: ከኛም አልፎ የውጭ ምሁራን ሁሉ በውይይታችን ተካፍለዋል:: ራሱን ለገደለ ሰው ፍትሐት የማይደረገው በሁሉም ሳይሆን በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ነው:: አጤ ቴዎድሮስ ሰው (ካህናት)ጨፍጭፈዋል ለሚለው ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ሰው የገደለ ሰው መላ ዘመኑን ይጹም ብለዋል:: አጤ ቴዎድሮስ መላ ዘመናቸውን ለመጾም ጊዜ ባያጋጥማቸው ለሀገራቸው ክብርና ታሪክ ራሳቸውን አሳልፈዋል:: ይህ ራሱ እንደ ንስሐ የሚቆጠር ነው:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያለው ትውልድም እያከበራቸው ነው ተቀብሏቸዋል::"

"አጤ ቴዎድሮስ ቤተ ክርስቲያኗ የሰሞነኛ ብቻ ሳትሆን የምእመናንና የሊቃውንት እንድትሆን ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ እንደ ነበር ከመዋዕለ ታሪካቸው እናነባለን:: እና እኛም ይኼን ሁሉ ከተነጋገርን በኋላ አጤ ቴዎድሮስ በሥርዓተ ጸሎት እንዲነሡ ተስማምተናል:: ካነሣናቸው ነገር አንዱ የሁዳዴ ጾም የመጀመሪያው ሳምንት ጾም ጾመ ሕርቃል ይባላል::"

"ሕርቃል ንጉሥ ነው:: ክርስቲያኖች በአረማውያን እየተሰቃዩ በነበረ ጊዜ የክርስቲያን አለቆችና ሊቃውንት ወደርሱ ሂደው የኛ ጠላቶች የሆኑ ወገኖቻችንን ሁሉ ገደሉብን በብርቱም እያሰቃዩን ነውና እባክህ አንተ እርዳን ብለው ለመኑት:: እርሱ ምን ብሎ መለሰላቸው ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ሰው የገደለ ሰው መላ ዘመኑን ይጹም ብለዋል:: እኔ ሰው የገደልኩ እንደሆነ መላ ዘመኔን ለመጸም አልችልም:: ስለዚህ ምን ይመስላችኋል ቢላቸው መቼም የሰው ልጅ ዕድሜ ብዙ አይደለም ቢበዛ መቶ ነው::"

"አንተ እኛን ነጻ ካወጣኸን ጠላቶቻችንን ካጠፋህልን እኛ ተካፍለን ላንተ እንጾምልሃለን ብለው ቃል ገቡለት:: እርሱም በቃላቸው መሠረት ዘምቶ የክርስቲያኖችን ጠላቶች እንዳጠፋቸው በታሪክ ይታወቃል:: እኒያ ክርስቲያኖችም ስለ ሕርቃል 8 ቀን ጾሙለት:: እኛም በሑዳዴ ጾም የመጀመሪያው ሳምንት ዘወረደ ወይም ሕርቃል የምንለው ስለዚህ ነው:: እኛ ኢትዮጵያውያኖች እንደወሰንነው ስለ ቴዎድሮስ በየዓመቱ 8 ቀን እንጾማለን ብለን ወስነናል:: በዚህ ምክንያት ነገሩ ይካሄዳል ብለን አምነናል:: 3 ሲኖዶሱ ይኸን ካልፈቀደ የአጤ ቴዎድሮስን በዓል ለማክበር ለኛ አይከብድም:: ሕዝቡም የዚህ ግንዛቤ ይኖረው ዘንድ በተዋረድ የምንንቀሳቀስበትን መርሐ ግብር ነድፈናል" ሲሉ ጽፈዋል::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የታሪክ ጥቅሶች የሃይማኖት አባቶች ዛሬም ቢሆን አጤ ቴዎድሮስን የሚወዷቸው እንዳሉ ያመለክታል:: እነዚህ የሃይማኖት መምህራን አጤ ቴዎድሮስን የሚወዷቸው ለሃይማኖታቸው ቀናዒ የሆኑ ናቸው:: ሃይማኖታቸው ከፍ እንድትል የሚፈልጉ ከጳጳስ እስከ ካህን የአጤ ቴዎድሮስን መዋቅር ደግፈው ለቤተ ክርስቲያን እድገት የሚጥሩ ናቸው::

የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን መምህራን አሁን አሁን ወንጌልን ፈትፍተው የሚያስተምሩ ልጆች በቅለዋል:: እነዚህ ልጆች ናቸው ዛሬ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ከነጣቂ ተኩላ በመከላከል ላይ ያሉ:: አጤ ቴዎድሮስ ቢኖሩ ኑሮ በቅሎአቸውን እንደሸለሙት ሙሽራ ዲያቆን ይሸልሟቸው ነበር:: በዚሁ ከጠነከሩበት ምድራዊ ሽልማት ቢቀርባቸው ከፍተኛውን ሽልማት የሚሰጣቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይሸልማቸዋል::



# ክፍል ሰባት

## ምዕራፍ 1

### አጤ ቴዎድሮስ "የአሜሪካ ጦርነት አበቃ ወይ?"

የእስራት ዘመኔ በአበሻ አገር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 95 "አጤ ቴዎድሮስ ሳሙኤል፣ጎባትን በየጊዜው እየሳኩ የአሜሪካ ጦርነት አበቃ ወይ?" እያሉ ያስጠይቁ ነበር:: ሲሉ ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ ለምን ስለ አሜሪካ ጉዳይ ሊያውቁ ፈለጉ? ምን ታያቸው? የጥቁሮች መጎሳቆል አስጨንቋቸው ይሆን? ትኩረት ሰጥቶ የተቸበት እስካሁን አላነበብኩም የማርኮስ ጋርቬይ ራእይ ታይቷቸው ይሆን? ዛሬ ያለው የኢትዮጵያ ትውልድ ሊረዳው የሚገባው ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በቅኝ ግዛት ተይዘው ለነበሩ ሕዝቦች ምሳሌ የነበረች መሆንዋን ነው:: ለዚህም ነው የማርቆስ ጋርቬይ ታሪካዊ ንግግሮቹን የምንጠቅሳቸው::

መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት ኑሮ እና ክርስትና በአሜሪካ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ127 "እኔ የማምነው አንድ አምላክ በሆነው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ በኢትዮጵያ አምላክ ነው:: ደግሞም እኔ ከማንኛውም ነጭ ጋር እኩል ነኝ ማርቆስ ጋርቬይ" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን ብሎ የሚናገር ትውልድ አሜሪካ ውስጥ የሚፈጠር መስሎአቸው ይሆን አጤ ቴዎድሮስ፤ አዎ በእርሳቸው ጊዜ ኢትዮጵያ ለሌሎች የአፍሪካ አገሮች አስተዋጽኦ ባታደርግም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለአፍሪካ ሕዝብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጓ አይዘነጋም::

ለዛሬው ለእኛው ትውልድ ሳይሆን ለወደፊቱ ኢትዮጵያውያን ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ ለማሳሰብ ነው:: አሜሪካ የመጣሁት ሚያዝያ 29 ቀን 1979 ዓም ወይም በጎርጎርዮስ ቀመር በ1987 ሲሆን ምርጫን በተመለከተ ብዙም ቦታ ሰጥቻው አላውቅም ነበር:: ምክንያቱም አገር አለኝ የሚለው ስሜቴ ፈንቅሎ ኢትዮጵያ ጎንደር